# የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ልማት
# ፍኖተ-ካርታ

## (2005-2017 ዓ/ም)

በኢፌዲሪ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተዘጋጀ

መስከረም 2005 ዓ/ም
አዲስ አበባ

# ማውጫ

ገጽ

ማጠቃለያ ....................................................................................................................1

1. ክፍል አንድ- መግቢያ ........................................................................................7

1.1 የጥናቱ ተግባር፣ ዓላማ፣ ሂደትና ዘዴዎች .......................................................7
1.1.1 የጥናቱ ተግባር ........................................................................................7
1.1.2 የጥናቱ ዓላማ .........................................................................................8
1.1.3 የጥናቱ ሂደት .........................................................................................8
1.1.4 የጥናቱ ዘዴ.............................................................................................9
1.1.5 የጥናቱ ውጤቶች.....................................................................................10
1.2 ፈጣንና ዘላቂ ልማት በማስፈን ድህነትን የማስወገድ ዕቅድ (PASDEP) ትግበራ የተገኙ ውጤቶችና ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች ..........................................................11
1.3 በመጀመሪያው ሁለት ዓመታት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በኢንዱስትሪ ዕድገት የተገኙ ውጤቶች ...........................................................................12
1.3.1 የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት አፈጻጸም ..............................15
1.3.2 የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ አፈፃፀም ...............................................16

2. ክፍል ሁለት- የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ልማት ዓላማ፣ መነሻ መርሆዎችና መሠረታዊ አቅጣጫዎች (Pillars) .......................................................................20

2.1 የኢንዱስትሪ ልማት ፍኖተ-ካርታ (Road map) ዓላማዎች........................................20
2.2 የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ልማት መነሻ መርሆዎችና መሠረታዊ አቅጣጫዎች .............20

3. ክፍል ሦስት- አገራዊ የልማት ራዕይ፣ግብና ዒላማ..............................................23

3.1 አገራዊ የልማት ግቦች ...................................................................................23
3.2 አገራዊ የልማት ዒላማዎች...............................................................................23
3.2.1 የመካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት ደረጃና የኢንዱስትሪ መዋቅር.........................................................................................................23
3.2.2 የኢትዮጵያ ልማት ዒላማዎች .........................................................................28

4. ክፍል አራት- የኢንዱስትሪ ልማት ራዕይ፣ አቅጣጫ፣የስትራቴጂ ዓላማዎችና የአፈጻጸም ምዕራፎች.................................................................................37

4.1 የኢንዱስትሪ ልማት ራዕይ .............................................................................37
4.2 የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫ ..........................................................................37
4.3 ስትራቴጂያዊ ግቦች፣ ዓላማዎች፣ ቁልፍ ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞች.......................41
4.3.1 የስትራቴጂ ግቦችና ዓላማዎች.........................................................................41
4.3.2 ቁልፍ ስትራቴጂዎች ...................................................................................42
4.3.3 የኢንዱስትሪ ልማት ዋና ዋና ፕሮግራሞች ........................................................42

4.4 የኢንዱስትሪ ልማት ምዕራፎች (phases) ....42
4.5 በልማት ምዕራፎቹ መጨረሻ የሚኖሩ ዋና ዋና ግቦች ....50

5. ክፍል አምስት- የኢንዱስትሪ ልማት ፍኖተ-ካርታው (Road map) እና የስትራቴጂ ዕቅዱ ትስስር ....56

አባሪ 1፡ የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ታሪካዊ አመጣጥ ....57
አባሪ 2፡ የመካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች የማክሮ ኢኮኖሚ፣የዜጎች ኑሮ ደረጃና ማህበራዊ ልማት ደረጃ አመልካች መስፈርቶች (indicators) ....62
አባሪ 3፡ በማክሮና በኢኮኖሚ ዘርፎች ደረጃ ከተለያዩ መ/ቤቶች መረጃ በመስጠት በጥናቱ የተሳተፉ የመንግሥት በለሥልጠናትና ግለሰቦች ዝርዝር ....64

## የሠንጠረዦች ዝርዝር

ሠንጠረዥ 1፡ የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት (Real GDP) የዕድገት መጠን (2003-2004 ዓ/ም) ....13
ሠንጠረዥ 2፡ የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ሥርጭት በዋና ዋና ዘርፎች ....14
ሠንጠረዥ 3፡ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት የተገኘ ውጤት ማጠቃለያ ....16
ሠንጠረዥ 4፡ በ2004 የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ኤክስፖርት አፈጻጸም ....17
ሠንጠረዥ 5፡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች አፈጻጸም ....18
ሠንጠረዥ 6፡ ዋና ዋና የማክሮ የኤክኖሚ ዕድገት ቁልፍ አመልካቾች (key indicators) ....26
ሠንጠረዥ 7፡ የዜጎችና ማህበራዊ ልማት ዕድገት ቁልፍ አመልካቾች (key indicators) ....27
ሠንጠረዥ 8፡ በማክሮ ደረጃ የተመረጡ የዕድገት አመልካቾች (variables) ትንበያ ....28
ሠንጠረዥ 9፡ የዜጎች ነፍስ ወከፍ ዓመታዊ ገቢ መጠን ዕድገት ....31
ሠንጠረዥ 10፡ የኢኮኖሚ ዘርፎች ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የሚኖራቸው ድርሻ ....35
ሠንጠረዥ 11፡ በዕቅድ ዘመኑ መጀመሪያ ምዕራፍ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ዕድገት ግቦች ....43
ሠንጠረዥ 12፡ ነባር የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ከዘርፉ የሚኖራቸው ድርሻ በ% ....45
ሠንጠረዥ 13፡ ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው ነባር የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በሦስተኛው የልማት ምዕራፍ ከዘርፉ የሚኖራቸው ድርሻ ግብ ....47
ሠንጠረዥ 14፡ በእያንዳንዱ የልማት ዕቅድ ምዕራፍ የሚጠበቁ ዋና ዋና የግብ ስኬቶች ....51
ሠንጠረዥ 15፡ ነባርና አዳዲስ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሞች የሚኖራቸው የዕድገትና መዋቅራዊ ለውጥ ሁኔታ ማጠቃለያ ....53

## የቻርቶች ዝርዝር

ቻርት 1፡ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ ሁለት ዓመታት ዋና ዋና ዘርፎች ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የነበራቸው ድርሻ ....15
ቻርት 2፡ በሦስቱ የዕድገት አማራጮች የነፍስ ወከፍ ገቢ ዕድገት ዒላማዎች ....32
ቻርት 3፡ የኢንዱስትሪው ዘርፍና የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የሚኖራቸው ድርሻ ....33

ቻርት 4፡ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ የሚኖረው የኢኮኖሚ ዘርፎች መዋቅር............................34
ቻርት 5፡ ከኢንዱስትሪ ዘርፍ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ድርሻ........................................36
ቻርት 6፡ በቀሪው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው ኢንዱስትሪዎች ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የሚኖራቸው ድርሻ......44
ቻርት 7፡ በሁለተኛው የኢንዱስትሪ ልማት ምዕራፍ ነባር የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ዕድገት..........................................................................46
ቻርት 8፡ በሦስተኛው የልማት ምዕራፍ የነባር ማኑፋክቸሪንግ ኢነዱስትሪዎች ዕድገት .........48
ቻርት 9፡ የኢንዱስትሪ መዋቅራዊ ለውጥ ሂደት..................................................................49

**ማጠቃለያ**

ይህ ጥናት የተካሄደው የኢትዮጵያን ኢንዱስትሪ ልማትና የዘርፉን መዋቅራዊ ለውጥ ሂደት በማፋጠን በ2017 አገሪቷን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለማሰለፍ የተያዘውን ራዕይ እውን ለማድረግ የሚያስችል የኢንዱስትሪ ልማት ፍኖተ-ካርታ (Road map)፣ የስትራቴጂ ዕቅድ እና ተቋማዊ አደረጃጀት ለማዘጋጀት ነው፡፡

በጥናቱ ሂደት አሁን ያለው የአገሪቷ ኢኮኖሚ በግብርና ላይ የተመሠረተ መሆኑ፣ በሌላ በኩል ግን እሴት በመጨመር ኢኮኖሚውን ለማሳደግና ወደ ኢንዱስትሪ -መር ለመለወጥ የሚያስችሉ ሰፊ የተፈጥሮ ሀብትና የገበያ አማራጮች መኖራቸው ግንዛቤ ተወስዷል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ጥናቱ የኢንዱስትሪ ዘርፉ አሁን ያለበትን ደረጃና ክፍተቶችን በመለየት የመፍትሄ ሀሳቦችን ያቀርባል፡፡ በመጨረሻም በ2017 አገሪቷን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለማሰለፍ በተያዘው ራዕይ መሠረት ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው የኢንዱስትሪ ዘርፍ የዕድገት ግቦችን ያስቀምጣል፡፡

የጥናቱ አጠቃላይ ዓላማ የኢትዮጵያን የኢንዱስትሪ ዘርፍ የዕድገት አቅጣጫ የሚጠቁም ፍኖተ-ካርታ (Road map)፣ በ2017 አገሪቷን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለማሰለፍ የተያዘውን ራዕይ እውን ለማድረግ የሚያስችል የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂና የዘርፉን መዋቅራዊ ለውጥ ሂደት ለማፋጠን የሚረዳ ተቋማዊ አደረጃጀት መቅረጽ ነው፡፡

ጥናቱ የተካሄደው መደበኛ የጥናት ስልቶችን ተከትሎ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ተፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የጥናት ቡድኑ አግባብነት ያላቸው ሰነዶችን መርምሯል፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቃለ መጠይቅና ከተመረጡ ቡድኖች ጋር ውይይት (Focus Group Discussion) አድርጓል፣በአካል በመገኘት ያሉትን የኢንዱስትሪ ዞኖች ጎብኝቷል፡፡ በመጨረሻም ሦስት የጥናት ሰነዶች የተዘጋጁ ሲሆን እነሱም፣

- የኢንዱስትሪ ልማት ፍኖተ-ካርታ (Road map)፣
- የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ዕቅድ እና
- የኢንዱስትሪ ልማት ተቋማዊ አደረጃጀት ሰነዶች ናቸው፡፡

የኢንዱስትሪ ልማት ፍኖተ-ካርታ (Road map) ዓላማ በ2017 አገሪቷን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች የዕድገት ደረጃ ላይ ለማድረስ በተያዘው ራዕይ መሠረት የኢንዱስትሪው ዘርፍ ልማት አቅጣጫን ለማሳየት ነው፡፡ ፈጣን፣ ቀጣይና ሰፊ መሠረት ያለውን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት የተያዘውን አገራዊ ራዕይ በማሣካት ረገድ ፍኖተ-ካርታው (Road map) ጉልህ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ተብሎ

ይታመናል፡፡ በዚሁ መሠረት አጠቃላይ አገራዊ የልማት ግቡ ድህነትን ሙሉ በሙሉ በማስወገድ የዜጎቿ መሠረታዊ ፍላጎቶች ሙሉ በሙሉ የተሟሉባት መካከለኛ ገቢ ያላት አገር መገንባት ነው፡፡

የማህበራዊ-ኢኮኖሚ ዕድገትና የሰው ልጅ የኑሮ ደረጃ ዕድገት አመላካች ከሆኑ ቁልፍ መስፈርቶች አንጻር የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በሞዴልነት ከተወሰዱ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ኢኮኖሚ ጋር ሲነጻጸር ግልጽ የሆነ ክፍተት ያሳያል፡፡ ከእነዚህ አገሮች የዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ በሚቀጥሉት 13 ዓመታት እነዚህን ክፍተቶች መዝጋት ያስፈልጋል፡፡

የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ያለው ድርሻ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሞዴል አገሮች (MMIC) አንጻር ሲታይ በ20 ነጥብ ዝቅ ብሎ ይገኛል፡፡ ይህም የሚያሳየው በ2017 መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች ኢኮኖሚ ዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ የኢንዱስትሪ ዘርፉ ዕድገት ከሁለት እጥፍ በላይ መጨመር እንደሚኖርበት ነው፡፡ በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍም ተመሳሳይ ሁኔታ ይታያል፡፡ በ2005 የኢትዮጵያ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የነበረው አስተዋፅኦ 4% ብቻ ሲሆን በተመሳሳይ ጊዜ መካከለኛ ገቢ ባላቸው አገሮች የዚህ ዘርፍ ድርሻ 17% ነበር፡፡ ይህም ማለት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፉ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ጋር ሲነጻጸር በ13% ያንሳል ማለት ነው፡፡

ይህንን ክፍተት በመሙላትና በ2017 የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፉ ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የሚኖረው ደርሻ 17% ለማድረስ ለዘርፉ የላቀ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በዚሁ መሠረት ክፍተቶቹን ለመሙላት የተመረጡ የኢኮኖሚ ዕድገት ግቦች (በማክሮና በኢኮኖሚ ዘርፍ ደረጃ) ተቀምጠዋል፡፡ የኢኮኖሚ ዕድገት ግቦች በሦስት አማራጮች የቀረቡ ሲሆን እነሱም የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከፍተኛ የዕድገት አማራጭ፣ ኢኮኖሚው እያደገ ሲመጣ የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የዕድገት ምጣኔ እየቀነሰ የሚሄድበት አማራጭና የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መነሻ (base case scenario) የዕድገት አማራጭ ናቸው፡፡

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከፍተኛ የዕድገት አማራጭ መሠረት የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት በየዓመቱ በአማካይ በ14.9% ያድጋል፡፡ በዚህ የዕድገት አማራጭ መሠረት የዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢ በ2007 ዓ/ም 746 የአሜሪካን ዶላር፣በ2012 ዓ/ም 1451 የአሜሪካን ዶላርና በ2017 ዓ/ም ደግሞ 2877 የአሜሪካን ዶላር እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡ በሁለተኛው የዕድገት አማራጭ በመጀመሪያዎቹ የዕቅዱ ዘመን እንደማንኛውም ታዳጊ ኢኮኖሚ ከፍተኛ የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ዕድገት መጠን እንደሚኖርና ከዚያም ኢኮኖሚው እያደገ ሲመጣ የዕድገት ምጣኔው እስከ ዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ቀስ በቀስ እየቀነሰ

እንደሚሄድ  ታሳቢ ተደርጓል፡፡ በዚህ የዕድገት አማራጭ መሠረት የዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢ በ2007 ዓ/ም 671.7 የአሜሪካን ዶላር፣በ2012 ዓ/ም 970.6 የአሜሪካን ዶላርና በ2017 ዓ/ም ደግሞ 1,380.1  የአሜሪካን ዶላር እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡ በዚህ ጥናት የተመረጠው የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት በየዓመቱ በአማካይ በ11.2% እንደሚያድግ ታሳቢ ያደረገው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መነሻ (base case scenario) የዕድገት አማራጭ ነው፡፡ በዚህ የዕድገት አማራጭ መሠረት የዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢ በ2007 ዓ/ም 676.5 የአሜሪካን ዶላር፣ በ2012 ዓ/ም 1,116.6 የአሜሪካን ዶላርና በ2017 ዓ/ም ደግሞ 1,880.2 የአሜሪካን ዶላር እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡አገራዊ የዕድገት ግቦችም የተመረጡት ይህን የዕድገት አማራጭ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

በዚሁ መሠረት የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት መጠን  በ2007 ዓ/ም 59.85 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር፣ በ2012 ዓ/ም 110.68 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር፣ በ2017 ዓ/ም መጨረሻ ደግሞ 206.69 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡ ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የኢንዱስትሪ ዘርፍ ድርሻ በተመሳሳይ ሁኔታ ተገምቷል፡፡ በዚሁ መሠረት የኢንዱስትሪው ዘርፍ ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የሚኖረው ድርሻ በ2007 ዓ/ም 11.2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር፣ በ2012 ዓ/ም 24.8 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላርና በ2017 ዓ/ም ደግሞ 56.5 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚደርስ ግብ ተጥሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የኢንዱስትሪው ዘርፍ ንዑስ ዘርፍ የሆነው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ቀስ በቀስ የአንበሳውን ድርሻ እንደሚይዝና በ2007 ዓ/ም ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት 4.2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ይገመታል፡፡ በዕቅዱ ሁለተኛና ሦስተኛ ምዕራፍ ላይ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በሚደረገው የላቀ እንቅስቃሴ ምክንያት ዘርፉ በ2012 ዓ/ም ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የሚኖረው የ13.3 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ድርሻ በ2017 ዓ/ም ወደ 35.2 ቢሊዮን የአሜሪካን  ዶላር ከፍ እንደሚል ተገምቷል፡፡

በ2005 ዓ/ም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ከአጠቃላይ የኢንዱስትሪ ዘርፍ 33% የያዘ ሲሆን ይህም በ2007 ወደ 37% እንደሚያድግና በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ (በ2017) ደግሞ 67% እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡

አሁን ያለውን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የማምረት አቅም በማሳደግ፣ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋምና ዘርፉን በማስፋፋት (diversification) በሚቀጥሉት 13 ዓመታት በሚደረጉት እንቅስቃሴዎች ዘርፉ ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚኖረው አስተዋፅኦ በእጅጉ እንደሚጨምር ይጠበቃል፡፡ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ በ2017 ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት 17% ድርሻ እንደሚኖረው ተገምቷል፡፡ በዚሁ መሠረት ፈጣንና ዘላቂ የኢንዱስትሪ ልማትን ለማረጋገጥና ኢንዱስትሪው በአገር ኢኮኖሚ ውስጥ ቁልፍ ሚና እንዲጫወት ለማድረግ አመቺ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ይደረጋል፡፡

በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት አምስት የልማት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡ እነሱም፣

- ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው ዋና ዋና ኢንዱስትሪዎችን ማሻሻልና የማምረት አቅማቸውን ማሳደግ፣
- የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን ወደ አዳዲስ ዘርፎች ማስፋፋት(diversification to new sectors)፣
- የኢንተርፕራይዝ ልማት ማስፋፋት፣
- የመንግሥትና የግል ኢንቨስትመንት ማስፋፋት እና
- የኢንዱስትሪ ዞኖችን ማልማት ናቸው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ልማት የሚመሠረትባቸው አራት ዋና ዋና የስትራቴጂ አቅጣጫዎች (strategic pillars) የተለዩ ሲሆን እነሱም፣

- የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ለኢንዱስትሪ ልማትና ለአገር ኢኮኖሚ ዕድገት የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ ቀጣይ ማድረግ፣
- በየክልሉ ሚዛናዊ የኢንዱስትሪ ልማት መኖሩን ማረጋገጥ፣
- የአገሪቷን ኢንዱስትሪዎች ከአካባቢው አገሮችና ከዓለም አቀፍ ገበያና ልማት ሁኔታ ጋር ማስተሳሰር እና
- ኤክስፖርት-መርና ገቢ ምርቶችን ተኪ የሆነ የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫን መከተል ናቸው፡፡

ከላይ የተጠቀሱት የኢንዱስትሪ ልማት ግቦችን በሦስት ምዕራፎች ለማሳካት ታቅዷል፡፡

በመጀመሪያው ምዕራፍ ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸውን ነባር ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም ማሳደግ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል፡፡ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጡት የኢንዱስትሪ ልማት ግቦች በዚህ ምዕራፍ የሚሳኩ ቁልፍ ግቦች ይሆናሉ፡፡ በዚህ የዕቅድ ምዕራፍ ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ አብዛኛውን ድርሻ የሚይዙት ቀላል ኢንዱስትሪዎች ሲሆኑ ይህ ግን ደረጃ በደረጃ እየቀነሰ እንደሚሄድ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም በ2007 የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት 7% ድርሻ እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡

በሁለተኛው ምዕራፍ የዕቅድ ዘመኑ ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው ነባር ኢንዱስትሪዎች ማስፋፊያ (diversification) እና ከዚሁ ጎን ለጎን አዳዲስ ቁልፍ የሆኑ ኢንዱስትሪዎች የሚገነቡበት ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ አራት አዳዲስ የኢንዱስትሪ ዓይነቶች እንደሚጀመሩ የታቃደ ሲሆን እነሱም፣

- የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ(ICT)ና ኤሌክትሮኒክስ ኢንዱስትሪዎች፣
- የፔትሮኬሚካል ኢንዱስትሪዎች፣
- የባዮ ቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪዎች እና
- የፓኬጂንግ ኢንዱስትሪዎች ናቸው።

ከዚህም በተጨማሪ እውቀትን መሠረት ባደረጉና የናኖ ቴክኖሎጂ የመሳሳሉት አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችን በተጨማሪ ለመጀመር እንዲቻል በዚህ በሁለተኛው የዕቅድ ምዕራፍ የአቅም ግንባታ ሥራዎች ይሠራሉ፣ እንዲሁም ፈጣን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዕድገት ለማምጣት የላቀ እንቅስቃሴ ይደረጋል። ከባድ የብረታብረትና የኬሚካል ኢንዱስትሪዎችን ከመገንባት ጎን ለጎን በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተለይተው ቅድሚያ ትኩረት ለተሰጣቸው ኢንዱስትሪዎች የሚሰጠው ትኩረትም ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። በዚህ ምዕራፍም ቢሆን

ቀላል ኢንዱስትሪዎች በዘርፉ የሚኖራቸው ድርሻ ከፍተኛ ቢሆንም ከባድ ብረታብረትና ኬሚካል ኢንዱስትሪዎች ድርሻ ደረጃ በደረጃ እየጨመረ እንደሚመጣ ይጠበቃል። በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ድርሻ ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት 12% እንደሚደርስ ይገመታል።

በሦስተኛው ምዕራፍ አዲስ የተገነቡት ከባድ የብረታብረትና ኬሚካል ኢንዱስትሪዎች አቅማቸውን እንዲያሳድጉና የበለጠ እንዲስፋፉ ይደረጋል፣ከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎችም (high-tech industries) ይገነባሉ። በዚህ የዕቅድ ምዕራፍ የሚፈጠረውን አመቺ ሁኔታ በመጠቀም በእውቀት ላይ የተመሠረቱና የናኖ ቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪዎች ልማት ደግሞ ከ2017 በኋላ የሚቀጥል ይሆናል። በዚህ በሦስተኛው ምዕራፍ የዕቅድ ዘመንም ቢሆን በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዙት ቀላል ኢንዱስትሪዎች ይሆናሉ። ይሁን እንጂ እስከ ዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ (2017) የከባድ ብረታብረት፣ የኬሚካል ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም የከፍተኛ ቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪዎች (high-tech industries) ድርሻ ቀስ በቀስ እያደገ ይሄዳል። በዚሁ መሠረት ኢንዱስትሪው ከፍተኛ መዋቅራዊ ለውጥ በማሳየት በ2017 ከዘርፉ ከ50% በላይ የሚሆኑት መካከለኛና ከፍተኛ ቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪዎች እንደሚሆኑና ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ድርሻ 17% እንደሚደርስ ይጠበቃል።

የውጭ ምንዛሪን በማስገኘት የኢንዱስትሪ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረው ድርሻም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ እንደሚሄድ ይጠበቃል። በዚሁ መሠረት በመጀመሪያው ምዕራፍ የዕቅድ ዘመኑ (2007) ከዘርፉ የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ መጠን 2.6 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚደርስ ይገመታል። ይህም በሁለተኛው ምዕራፍ የዕቅድ ዘመኑ (2012 ዓ/ም) በሦስት እጥፍ በማደግ 7.32 ቢሊዮን

የአሜሪካን ዶላር እንደሚደርስ፣ በሦስተኛው ምዕራፍ ማለትም በ2017 በስምንት እጥፍ በማደግ 16.3 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚደርስ ይገመታል፡፡

ዘርፉ አዳዲስ የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር ረገድም የጎላ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡ በ2005 ዓ/ም ዘርፉ የፈጠረው የሥራ ዕድል 204 ሺህ ነበር፡፡ ከዚህም በመነሳት በ2007 ዓ/ም ዘርፉ 236 ሺህ ተጨማሪ አዳዲስ የሥራ ዕድሎችን እንደሚፈጥር፣ በ2012 ዓ/ም ደግሞ 377 ሺህ አዳዲስ የሥራ ዕድሎችን እንደሚፈጥር፣ ይህም እያደገ ሄዶ በ2017 ዓ/ም በዘርፉ የሚፈጠረው የሥራ ዕድል 780 ሺህ እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡ ይህም መጠን በ2007 ዓ/ም ከሚፈጠረው የሥራ ዕድል ጋር ሲነጻጸር የ330% ጭማሪ ያሳያል፡፡ በዕቅድ ዘመኑ የኢንተርፕራይዝ ልማት በተለይም የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት በማስፋፋት ወደ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲያድጉ ይደረጋል፡፡ በዚሁ መሠረት በ2007 ዓ/ም በድምሩ የ25 ሺህ ፣በ2012 ዓ/ም የ40 ሺህ እና በ2017 ዓ/ም የ65 ሺህ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት እንደሚከናወን ግብ ተጥሏል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ግቦች ለማሳካት የተነደፉት ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞችና ዝርዝር የአፈጻጸም መርሃ ግብር በስትራቴጂ ዕቅድ ሰነዱ ቀርበዋል፡፡ የኢንዱስትሪ ልማት ሂደቱን ለመደገፍ የሚያስፈልገው ተቋማዊ አደረጃጀት *"የኢንዱስትሪ ልማት ተቋማዊ አደረጃጀት"* በተሰኘው ሰነድ ቀርቧል፡፡

# 1. ክፍል አንድ- መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ተግባር፣ ዓላማ፣ ሂደትና ዘዴዎች

### 1.1.1 የጥናቱ ተግባር

ይህ ጥናት የተካሄደው የኢትዮጵያን ኢንዱስትሪ ልማትና የዘርፉን መዋቅራዊ ለውጥ ሂደት በማፋጠን በ2017 አገሪቷን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለማሰለፍ የተያዘውን ራዕይ እውን ለማድረግ የሚያስችል የኢንዱስትሪ ልማት ፍኖተ-ካርታ (Road map)፣ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ዕቅድና የኢንዱስትሪ ልማት ተቋማዊ አደረጃጀት ለማዘጋጀት ነው፡፡

በጥናቱ ሂደት አሁን ያለው የአገሪቷ ኢኮኖሚ በግብርና ላይ የተመሠረተ መሆኑ፣ በሌላ በኩል ግን እሴት በመጨመር ኢኮኖሚውን ለማሳደግና ወደ ኢንዱስትሪ -መር ለመለወጥ የሚያስችሉ ሰፊ የተፈጥሮ ሀብትና የገበያ አማራጮች እንዳሉ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የኢንዱስትሪ ዘርፍ መዋቅራዊ ለውጥ በማምጣት በ2017 መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች የዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ የተያዘውን ራዕይ በማሳካት ረገድ አሁን ባለው ሁኔታ የሠለጠነ የሰው ኃይልና የፋይናንስ አቅም ውስንነት መኖሩ ከግምት እንዲገባ ተደርጓል፡፡

እነዚህን ሁኔታዎች ባገናዘበ መልኩ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ያለውን እምቅ ሀብት በመጠቀም ኢኮኖሚውን ሊደግፍና ሊመራ የሚችል መሠረተ ሰፊ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አቅም ለመገንባት ያሉት አማራጮችና ስልቶች በዚህ ሰነድ ተዳሠዋል፡፡

የታቀደውን የኢንዱስትሪ ልማት ለማምጣት መንግሥት፣የግሉ ዘርፍ፣ሲቪል ማህበረሰቡንና የልማት አጋሮችን ጨምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅባቸውን አስተዋፅኦ ለማበርከትና ሚናቸውን በአግባቡ ለመጫወት እንዲችሉ የሚያግዝ የተግባርና የስትራቴጂ ማዕቀፍ በዚህ ሰነድ ተለይቶ ቀርቧል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በናሙናነት የተወሰዱ መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች የኢንዱስትሪ መዋቅር ሁኔታን በመገምገም በቀጣይ የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ምን መምሰል እንዳለበት በዝርዝር በጥናቱ ተመልክቷል፡፡ ለዚህም እንዲረዳ አሁን ያለው የአገሪቷ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ በአደረጃጀት፣ በአፈጻጸም፣ በማምረት አቅም ፣በቅልጥፍና፣ በውጤታማነት፣ በገበያ ሽፋን፣ በተወዳዳሪነት ወ.ዘ.ተ ያለበት ሁኔታና ለዘርፉ ልማት ያሉት መልካም አጋጣሚዎችና ተግዳሮቶች በዝርዝር ተገምግመው ቀርበዋል፡፡ በዚህ ግምገማ ዋና ዋና ክፍተቶችን በመለየት በቀጣይ ሊወሰዱ የሚገቡ የመፍትሔ እርምጃዎች ተጠቁመዋል፡፡

በመጨረሻም በ2017 አገሪቷን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች የዕድገት ደረጃ ላይ ለማድረስ በተያዘው ግብ መሠረት ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው የኢንዱስትሪ ዘርፍ ቀጣይ የልማትና ዕድገት ሁኔታ በዝርዝር ቀርቧል።

### 1.1.2 የጥናቱ ዓላማ

የጥናቱ አጠቃላይ ዓላማ የኢትዮጵያን የኢንዱስትሪ ዘርፍ የዕድገት አቅጣጫ የሚጠቁም ፍኖተ-ካርታ (Road map)፣ በ2017 አገሪቷን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለማሰለፍ የተያዘውን ራዕይ እውን ለማድረግ የሚያስችል የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ዕቅድና የዘርፉን መዋቅራዊ ለውጥ ሂደት ለማፋጠን የሚረዳ ተቋማዊ አደረጃጀት ለመቅረጽ ነው። የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፣

1. የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣትና በ2017 ዓ/ም አገሪቷን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለማሰለፍ የተያዘውን ራዕይ እውን ለማድረግ የሚረዳ የኢንዱስትሪ ልማት ፍኖተ-ካርታ (Road map) ለመቅረጽ፣
2. የኢንዱስትሪ ልማት ፍኖተ-ካርታውን (Road map) ለመተግበር የሚያስፈልገውን የስትራቴጂ ዕቅድ ሰነድ ለማዘጋጀት እና
3. የኢንዱስትሪ መዋቅራዊ ለውጥ ሂደቱን ሊደግፍና ሊመራ የሚችል አስፈላጊውን ተቋማዊ አደረጃጀት ለማዘጋጀት ነው።

### 1.1.3 የጥናቱ ሂደት

የኢትዮጵያን የኢንዱስትሪ ልማት ፍኖተ-ካርታ (Road map) የመቅረጹ ሃሳብ የመነጨው በቀድሞው የኢንጂነሪንግ አቅም ግንባታ ፕሮግራምና በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መካከል በተደረገው ተከታታይ ውይይት ነበር። ይህን ተከትሎ በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ አማካይነት ፕሮፖዛል ተዘጋጀ። ይህም ፕሮፖዛል ለመነሻ በተዘጋጀው አውደ ጥናት ላይ በይፋ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ቀርቦ በፍኖተ-ካርታው (Road map) ሃሳብና አዘገጃጀት ሂደት ላይ አስተያየትና ሃሳብ እንዲቀርብበት ተደረጎ በመነሻው አውደ ጥናት በተገኘው ግብረ-መልስ መሠረት አጠቃላይ የጥናት ሥራው አደረጃጀትና ሂደት እንደገና ተቃኝቶ የፍኖተ-ካርታ (Road map) ጥናት ሥራ ተጀመረ።

የጥናት ቡድኑ የተዋቀረው ከተለያዩ አካላት በተወጣጡ ቡድኖች ሲሆን ይህም የኮሪያ ባለሙያዎችና የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ባለሙያዎችን ያቀፈ አብይ ቡድን እንደዚሁም ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተለያዩ ዘርፎች የተወጣጡ ባለሙያዎችን ያቀፈ ንዑስ ቡድን ነበር።

አጠቃላይ ጥናቱ እነዚህን ቡድኖች በማስተባበር ከተካሄደ በኋላ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በተቋቋመ የቴክኒክ ኮሚቴ ማለትም የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች፣

ባለሙያዎች፣ ዘርፎች፣ የሚኒስቴር መ/ቤቶች እና ታዋቂ ግለሰቦችን ያካታተ ኮሚቴ አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

በመጨረሻም በቴክኒክ ኮሚቴው የተሠጡት አስተያየቶች ከተካተቱ በኋላ በቀጣይ ተጨማሪ አስተያየትና የስትራቴጂ አቅጣጫ አመራር እንዲሰጥበት ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናትን አካትቶ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለተቋቋመው ስቲሪንግ ኮሚቴ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

#### 1.1.4 የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ የተካሄደው መደበኛ የአጠናን ስልቶችን ተከትሎ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ተፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የጥናት ቡድኑ አግባብነት ያላቸው ሰነዶችን መርምሯል፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቃለ መጠይቅና ከተመረጡ ቡድኖች ጋር ውይይት (Focus Group Discussion) አድርጓል፣ የተለያዩ አውደ ጥናቶችን አካሂዷል፣ በአካል በመገኘት ያሉትን የኢንዱስትሪ ዞኖች ጎብኝቷል፣እንዲሁም ከተመረጡ አገሮች ምርጥ ተሞክሮዎች እንዲወሰዱ ተደርጓል፡፡

**የሰነዶች ግምገማ፡-** በጥናቱ ሂደት አግባብነት ያላቸው የፖሊሲ፣ የስትራቴጂ፣ የአገር አቀፍና ዓለም አቀፍ የፕሮግራም ሰነዶች ተለይተው በጥልቀት በመገምገም ጥናቱን ለማዳበር የሚረዱ መረጃዎች እንዲሰበሰቡ ተደርጓል፡፡

***ቃለ መጠይቅ*፡-** በጥንቃቄ ከተመረጡ የስትራቴጂ አመራር ሰጪዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር ጥልቅ ቃለ መጠይቅ ተደርጓል፡፡ ይህም የሚኒስቴር መ/ቤቶችን፣ ኤጀንሲዎችን፣

ኮርፖሬሽኖችን፣ የንግድ ምክር ቤቶችን፣ የዘርፍ ማህበራትን፣ የሙያ ማህበራትን፣ የውጭ የንግድ ፎረሞችን፣ ከእያንዳንዱ ዘርፍ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችንና የግሉን ዘርፍ ጨምሮ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ያካተተ ነበር፡፡ በአጠቃላይ 61 ቃለ መጠይቆች የተደረጉ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 44 በዘርፍ ደረጃ ሲሆኑ የተቀሩት 17 በማክሮ ደረጃ አግባብነት ካላቸው ሚኒስትሮች፣ ሚኒስትር ዴኤታዎች፣ ዳይሬክተሮችና ሌሎች ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት ጋር የተደረጉ ናቸው (አባሪ 3 ይመልከቱ)፡፡

**የቡድን ውይይት**፡- በስትራቴጂ ጉዳዮች ላይ ወሳኝነት ያላቸውና ፍኖተ-ካርታውን (Road map) በመቅረጽ ረገድ የጎላ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል ተብለው የታመኑት ታሳታፊዎችን በመምረጥ የቡድን ውይይት ተደርጓል፡፡ ከእነዚህ ተሳታፊዎች ጋር በተደረገው ውይይት የወቅቱን የቢዝነስ ሁኔታና የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ያለበት ደረጃን አስመልክቶ ቀዳሚ መረጃዎችን (primary data) ለማግኘት ተችሏል፡፡ በዚህ የቡድን ውይይት የተሳተፉት በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሥር

የሚገኙ የዋና ዋና ዘርፍ ዳይሬክተሮችና ባለሙያዎች፣ የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ የኢንዱስትሪ ልማት ተዋናዮች፣ የኢንዱስትሪ ባለቤቶች፣ በየዘርፉ የሚገኙ ሥራ አስኪያጆችና የቴክኒክ ሠራተኞች ናቸው፡፡ በዚሁ መሠረት 114 ግለሰቦች በንቃት የተሳተፉበት በድምሩ 14 የቡድን ውይይቶች ተደርገዋል፡፡

**ዓውደ ጥናቶች፡-** በጥናቱ ሰነድ ላይ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ግብረመልስ ለመሰብሰብ እንዲቻል በሦስት ዓውደ ጥናቶች የተገኙት ግብረ መልሶችና አስተያየቶች በመጠቀም የጥናት ሰነዱ የበለጠ እንዲዳብር ተደርጓል፡፡ ከእነዚህ ዓውደ ጥናቶች ውስጥ አንዱ የተደረገው ከመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተወካዮች ጋር ሲሆን ዓላማውም ስለጥናቱ ግንዛቤ ለመፍጠር ነበር፡፡ በዚህ ዓውደ ጥናትም ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑ ግብአቶች ተገኝተዋል፡፡ የተቀሩት ሁለት ዓውደ ጥናቶች የተካሄዱት አግባብነት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ግብረ መልስ ለማግኘት ሲሆን ታሳታፊዎቹም የተለያዩ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ተወካዮች፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተጠሪ ተቋማትና ዳይሬክቶሬቶችን እና የግሉ ዘርፍ ተወካዮች ነበሩ፡፡

**የመስክ ምልከታና ጉብኝት፡-** ሁለት የተመረጡ አገሮችን (ቻይናና ደቡብ ኮርያ) በመጎብኘት በእነዚህ አገሮች ያሉትን የተለያዩ ኢንዱስትሪዎችና የኢንዱስትሪ ዞኖችን በመመልከት በርካታ ጠቃሚ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ በቻይና የአሥር ቀን ጉብኝት የተደረገ ሲሆን በእነዚህ የቆይታ ጊዜያት የቻይና ኢንዱስትሪ ግዛቶችን (industry provinces) በመጎበኘት ጠቃሚ ልምድ ለመቅሰም ተችሏል፡፡ በዚህ ጉብኝት የጥናት ቡድኑ ስለኢንዱስትሪ ዞን ልማትና አስተዳደር ሥርዓት፣ የኢንዱስትሪ ዞን ለማልማት የሚያስፈልጉ የድጋፍ ሰጪ አገልግሎት ፖኬጆች ጥልቅ ግንዛቤ አገኝቷል፡፡ የተመረጡ የጥናቱ ቡድን አባላት በደቡብ ኮርያ የሰባት ቀን ጉብኝት ያደረጉ ሲሆን በእነዚህ ጊዜያት ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑ በርካታ ልምዶችን ቀስመዋል፡፡

**የዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮ ቅመራ**

በኢንዱስትሪ ልማት ፍኖተ-ካርታ (Road map)፣ ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዲሁም ለፈጣን ኢኮኖሚ ልማት የሚያስፈልገው ተቋማዊ አደረጃጀት አስመልክቶ በፈጣን ልማት ላይ የሚገኙ የሌሎች አገሮችን ልምድ በማጥናት ለኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፈጣን ልማት ጠቃሚ የሚሆኑ ልምዶች እንዲወሰዱ ተደርጓል፡፡

### 1.1.5 የጥናቱ ውጤቶች

በመጨረሻም ሦስት የጥናት ሰነዶች የቀረቡ ሲሆን እነሱም፣

1. የኢንዱስትሪ ልማት ፍኖተ-ካርታ (Road map)፣
2. የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ዕቅድ እና
3. የኢንዱስትሪ ልማት ተቋማዊ አደረጃጀት ሰነዶች ናቸው፡፡

እነዚህ ሰነዶች በሦስት የተለያዩ ጥራዞች የቀረቡ ሲሆን በዚህ ጥራዝ የቀረበው የኢንዱስትሪ ልማት ፍኖተ-ካርታ (Road map) ነው፡፡

### 1.2 ፈጣንና ዘላቂ ልማት በማስፈን ድህነትን የማስወገድ ዕቅድ (PASDEP) ትግበራ የተገኙ ውጤቶችና ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች

ፈጣንና ዘላቂ ልማት በማስፈን ድህነትን የማስወገድ ዕቅድ (PASDEP) መጀመሪያ ላይ የኢንዱስትሪው ዘርፍ ማለትም የማኑፋክቸሪንግ፣ የኮንስትራክሽን፣ የሃይድሮፓዎር እና የማዕድንን ኢንዱስትሪዎች ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የነበረው ድርሻ በአማካይ ከ14% አይበልጥም ነበር፡፡ ከዚህ ውስጥ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ማለትም የጎጆ ኢንዱስትሪ፣ ጥቃቅንና አነስተኛ አንተርፕራይዞች እና መካከለኛና ትላልቅ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በድምሩ የነበራቸው አስተዋፅኦ በአማካይ 5.5% ነበር፡፡ ከአገሪቷ ጠቅላላ የኤክስፖርት ምርቶች የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶች ድርሻ በአማካይ ከ5% አይበልጥም ነበር፡፡

በዕቅዱ (PASDEP) ዘመን (1998-2002) የዕቅዱ ትኩረት ዓላማ ለመካከለኛና ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች መሠረት የሚጥሉ አነስተኛ የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን ማጠናከር ነበር፡፡ አነስተኛ የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በግብርናው ዘርፍ ውስጥ ለተሠማሩት አማራጭ ወይም ተጨማሪ ገቢ ማስገኛ ሥራ ሆነው ከማገልገላቸውም ሌላ በሌሎች ዘርፎች ላልተሠማሩ ሰዎች የሥራ ዕድል ፈጥረዋል፡፡

በዕቅዱ (PASDEP) ዘመን በኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ ድጋፍ ረገድ በአገሪቷ ከተገኙት ስኬቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፣

- የፖሊሲ ድጋፎች ተቀርጸው ተግባራዊ ተደርገዋል፣
- ትላልቅ የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ሆነዋል፣
- ስድስት የቅድሚያ ትኩረት ዘርፎች ተመርጠው በሁሉም ረገድ የላቀ ትኩረት እንዲያገኙ ተደርጓል፣
- ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው ዘርፎች አፈጻጸም ሁኔታን ለመገምገምና የፖሊሲ አቅጣጫ ለመስጠት ብሔራዊ የኤክስፖርት አስተባባሪ ኮሚቴ ተቋቁሟል፣
- ለኢንዱስትሪው ልማት ፖሊሲ ስኬት በመሣሪያነት ሊያገለግሉ የሚችሉ ቤንችማርኪንግ፣ የቁርኝት ፕሮግራም፣ የቢዝነስ ድርጅቶችን የማገናኘት ወ.ዘተ የመሳሳሉ አሠራሮች ተቀርጸዋል፣
- የሠለጠነ የሰው ኃይል አቅርቦት ችግሮችን ለመቅረፍ የከፍተኛ ደረጃ የቴክኒክ ትምህርትና ሥልጠና እንዲሁም የቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ፕሮግራሞች ተቀርጸዋል፣

- ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣ የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና የብረታብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የመሳሳሉት የልማት ማዕከላትና የስልጠና ተቋማት ተቋቁመዋል፡፡

ፈጣንና ዘላቂ ልማት በማስፈን ድህነትን የማስወገድ ዕቅድ (PASDEP) ዘመን የኢንዱስትሪው ዘርፍ ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የነበረው ድርሻ በእጅጉ የጨመረ ቢሆንም በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ጉልህ ዕድገት አልታየም፡፡ በመሆኑም የኢንዱስትሪው ዘርፍ ከአገር ውስጥ

ጠቅላላ ምርት የሚኖረውን ድርሻ ለማሳደግ የበለጠ ጥረት ይጠይቃል፡፡ ፈጣንና ዘላቂ ልማት በማስፈን ድህነትን የማስወገድ ዕቅድ (PASDEP) ዘመን የኢንዱስትሪውን ዘርፍ ካጋጠሙ ችግሮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፣

- የጥሬ ዕቃ እጥረት፣
- የሰው ሀብት ብቃት ማነስ ማለትም የቴክኒክና በአመራር ክህሎት የመሳሳሉ ችግሮች፣
- ተፈላጊ ጥሬ ዕቃዎች፣መለዋወጫዎችና ሌሎች ግብኣቶችን ከውጪ ለማስገባት የውጭ ምንዛሪ እጥረት፣
- የኤሌክትሪክ ሀይል መቆራረጥ እና
- የብድር አቅርቦትና ሌሎች አገልግሎቶች አሰጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማ ሆኖ አለመገኘት፡፡

በፖሊሲ አቅም ግንባታ ረገድ ፈጣንና ዘላቂ ልማት በማስፈን ድህነትን የማስወገድ ዕቅድ (PASDEP) ትግበራ የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችና ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ መንግሥት የቀጣይ አምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የነደፈ ሲሆን ይህ ዕቅድ የኢንዱስትሪ ዘርፍ አስተዋፅኦን በማሳደግ በአገሪቷ ኢኮኖሚ የመሪነት ሚና እንዲኖረው ለማድረግ መሠረት የሚጥል ነው፡፡

### 1.3 በመጀመሪያው ሁለት ዓመታት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን በኢንዱስትሪ ዕድገት የተገኙ ውጤቶች

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የኢንዱስትሪው ዘርፍ በአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ዕድገት፣ በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የውጭ ምንዛሪን በማስገኘትና በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት ይጠበቃል፡፡ በዕቅድ ዘመኑ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ማስፋፊያና ለመካከለኛና ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ድጋፍ የላቀ ትኩረት ተሰጥቷል፡፡ የኢንዱስትሪ ዞን ልማትና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች አመራርና ፕራይቬታይዜሽን በአገሪቷ የኢንዱስትሪ ልማት ለማምጣት ሌላው የዕቅዱ ትኩረት መስኮች ናቸው፡፡ የኢንዱስትሪ ልማቱ ስትራቴጂ አቅጣጫ ጉልበትን በሰፊው

በሚጠቀሙ፣ ሰፊ ገበያና ከሌላው የኢኮኖሚ ዘርፍ ጋር ጠንካራ ትስስር ያላቸው፣ የግብርና ምርቶችን በግብአት የሚጠቀሙ፣ ኤክስፖርት-መርና ገቢ ምርቶችን መተካት የሚችሉና ለፈጣን ቴክኖሎጂ ሽግግር አስተዋፅኦ በሚኖራቸው ኢንዱስትሪዎች ላይ ማተኮር ነው፡፡

በዚህ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ አቅጣጫ መሠረት ባለፉት ሁለት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት (2003 እና 2004) በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በተጠቀሱት ሁለት ዓመታት የነበረው የኢንዱስትሪው ዘርፍ አፈጻጸም ሁኔታ ቀጥሎ በሠንጠረዥ 1 ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 1፡ የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት (Real GDP) የዕድገት መጠን (2003-2004 ዓ/ም)**

| **ዘርፍ** | **መነሻ ዓመት (2002)** | **የ2003 ዕቅድ** | **የ2003 ክንውን** | **የ2004 ዕቅድ** | **የ2004 ክንውን** |
|---|---|---|---|---|---|
| አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (Real GDP) | 10.6 | 11 | 11.4 | 11.4 | 8.5 |
| ግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች | 7.6 | 8.5 | 9 | 8.5 | 4.9 |
| የኢንዱስትሪ ዘርፍ | 10.8 | 14 | 15 | 16 | 13.6 |
| የአገልግሎት ዘርፍ | 13.2 | 11 | 12.5 | 11.1 | 11 |

**ምንጭ፡- የፋይናንስና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የ2004 ሪፖርት**

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የግብርናው ዘርፍ የኢኮኖሚው ዕድገት ዋና አንቀሳቃሽ ሆኖ እንደሚቀጥል ታሳቢ ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ በ2004 የዘርፉ አፈጻጸም እንደተጠበቀው አልነበረም፡፡ ይልቁንም የግብርናው ዘርፍ ዕድገት ከታቀደው 8.5% ወደ 4.9% ቀንሷል፡፡ የግብርናው ዘርፍ ዕድገት መቀነስ በ2004 የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ዕድገት ወደ 8.5% ዝቅ ለማለቱ ዋናው ምክንያት ሆኗል፡፡

የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ መሠረቱ በአንጻራዊ አነጋገር ሰፊ ባይሆንም ባለፉት ሁለት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት በብረታብረት፣በኬሚካልና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪዎች አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችና ፕሮጀክቶች የታቀዱ በመሆኑ ዘርፉን ለማሳደግ ያለው ዕድል ከፍተኛ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በርካታ ፋብሪካዎች በመገንባት ላይ ናቸው፡፡ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ለኢንዱስትሪ ልማት ማለትም ኤክስፖርት ተኮርና ገቢ ምርቶችን ለሚተኩ ኢንዱስትሪዎች ከተሰጠው ቅድሚያ ትኩረት አኳያ ይህ ሂደት ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

በ2003 የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት (Real GDP) ዕድገት መጠን 11.4% ሲሆን ይህም ከዕቅዱ በ0.4% ካለፈው ዓመት አፈጻጸም ደግሞ በ0.8% ብልጫ አለው፡፡

በ2004 የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ዕድገት በ8.5% ቀጥሏል፡፡ ይህም የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ፈጣን ዕድገት የሚያመለክተው ኢትዮጵያ ትክክለኛ የማክሮ ኢኮኖሚና የኢኮኖሚ ዘርፍ ልማት ፖሊሲ መከተሏንና በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተጣሉትን ግቦች ለማሳካት በትክክለኛ ጎዳና ላይ መሆኗን ነው፡፡


በተጠቀሱት ሁለት ዓመታት የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት በዋና ዋና ምርቶች ከፍተኛ ዕድገት ያሳየ ሲሆን ይህም በ2003 15% እንዲሁም በ2004 13.7% ነበር፡፡ በ2004 ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት (Real GDP) የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ድርሻ በአማካይ 4% ነበር፡፡

**ሠንጠረዥ 2፡ የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ሥርጭት በዋና ዋና ዘርፎች**

| ዘርፍ | 2002 (መነሻ ዓመት) | 2003 | 2004 |
|---|---|---|---|
| የግብርና ዘርፍ በ% | 42 | 45.6 | 44 |
| የኢንስትሪ ዘርፍ በ% | 13 | 10.6 | 11.1 |
| የአገልግሎት ዘርፍ በ% | 45 | 44.5 | 45.6 |
| አጠቃላይ የአገር ውሰጥ ምርት | 100 | 100 | 100 |

**ምንጭ፡- የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የ2004 ሪፖርት**

የግብርናና የኢንዱስትሪው ዘርፎች ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የነበራቸው ድርሻ ሲታይ የግብርና ዘርፍ በ2003 ከነበረው የ45.6% ድርሻ በ2004 ወደ 44% የወረደ ሲሆን የኢንዱስትሪ ዘርፍ ድርሻ ከ10.6% ወደ 11.1% አድጓል፡፡ በተመሳሳይ ጊዜ የአገልግሎት ዘርፍ ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የነበረው ድርሻ ከ44.5% ወደ 45.6% አድጓል፡፡ ቀጥሎ ያለው ቻርት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ ሁለት ዓመታት ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት እያንዳንዱ ዘርፍ የነበረውን ድርሻ ያሳያል፡፡




ቻርት 1፡ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መጀመሪያ ሁለት ዓመታት ዋና ዋና ዘርፎች ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የነበራቸው ድርሻ

### 1.3.1 የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት አፈጻጸም

የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ራዕይ ፈጣንና ዘላቂ የኢንዱስትሪ ልማት በማስፈን ዘርፉ ቀስ በቀስ በኢኮኖሚው ውስጥ የመሪነት ሚና እንዲጫወት ማድረግ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ለማስፋፋትና መካከለኛና ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ዕድገት ለመደገፍ የላቀ ትኩረት ተሰጥቷል፡፡

በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በመስፋፋት ላይ ሲሆኑ በአገር ውስጥ ገበያ ተወዳዳሪ የሆኑ የኢንዱስትሪ ምርቶችን በማቅረብ በኢንዱስትሪ ልማቱ ወሳኝ ሚና መጫወት ጀምረዋል፡፡ እነዚህ ኢንተርፕራይዞች ለሥራ አጥ ወጣቶችና ሴቶች በድምሩ 1.15 ሚሊዮን የሥራ ዕድሎችን የፈጠሩ ሲሆን ይህም በ2003 ዓ/ም 18% የነበረው የከተማ ሥራ አጥነት መጠን በ2004 ዓ/ም ወደ 17.2% ዝቅ እንዲል አድርጎታል፡፡

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አቅም ለማጠናከርና የፋይናንስ ችግሮቻቸውን ለመፍታት መንግስት 1.015 ቢሊዮን ብር መድቧል፡፡ በንግድ ሥራ አመራር፣ ኢንተርፕሪኔርሽፕ፣ በቴክኒክና ሙያ ዘርፎች ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ አባላት ሥልጠና እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ 5000 ሄክታር የሚሆን የማምረቻ ቦታ፣ 1757 የማምረቻ ሼዶችና 46 ህንፃዎች ተገንብተው ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተሰጥተዋል፡፡

***ሠንጠረዥ 3፡ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት የተገኘ ውጤት ማጠቃለያ***

| የውጤት አመልካቾች | 2003 | 2004 |
|---|---|---|
| ሥልጠና በሠልጣኞች ብዛት | 453, 511 (ሠራተኞች) | 15, 106 (አሰልጣኞች) |
| የተሰጠ መሬት በሄክታር | 452 | 5,000 |
| የተገነቡ ሼዶች ብዛት በቁጥር | 1463 | 1,757 |
| የተገነቡ ህንፃዎች ብዛት በቁጥር | 71 | 46 |
| የተሰጠ ብድር መጠን በሚሊዮን ብር | 983 | 1,015 |
| የተፈጠሩ ሥራዎች ብዛት | 541,883 | 1,148,000 |
| ከተፈጠሩ ሥራዎች የሴቶች ድርሻ በ% | 53 | 40 |
| የከተማ ሥራ አጥነት መጠን በ% | 18 | 17.5 |

***ምንጭ፡ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የ2003 የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርትና የ2004 ረቂቅ ሪፖርት***

### 1.3.2 የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ አፈፃፀም

ባለፉት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሁለት ዓመታት መካከለኛና ትላልቅ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ፈጣንና አስተማማኝ የቴክኖሎጂ ዕድገት በማምጣት፣የኢኮኖሚውን ተወዳዳሪነት በማሳደግ፣የውጭ ምንዛሪን እጥረትን በመቅረፍ፣የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችና የግብርናውን ዘርፍ ዕድገት በመደገፍ የተፈለገውን ሚና እንዲጫወት ለማድረግ መንግሥት ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡

**ሠንጠረዥ 4፡ በ2004 የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ኤክስፖርት አፈጻጸም**

**(በሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር)**

| ተ.ቁ | ንዑስ ዘርፍ | 2003 አፈፃፀም | 2004 | | ንጽጽር በ% | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | 2003 ዕቅድ | 2004 አፈጻጸም |
| 1 | ስኳር፣ጨርቃጨርቅና አልባሳት | 62.22 | 171.37 | 84.63 | 73.1 | 49.4 |
| 2 | የቆዳና የቆዳ ውጤቶች | 104.34 | 206 | 112.06 | 57.8 | 54.4 |
| 3 | አግሮ ፕሮሰሲንግ | 34.45 | 82 | 51.75 | 42.8 | 63 |
| 4 | ኬሚካልና ፋርማሲዩቲካል | 6.91 | 11.92 | 7.01 | 96 | 58.7 |
| **ደምር** | | **207.9** | **471.3** | **255.4** | **58.8** | **54.2** |

**ምንጭ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የ2004 ሪፖርት**

በ2004 በጀት ዓመት ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ 471.3 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ታቅዶ በበጀት ዓመቱ የተገኘው ጠቅላላ የውጭ ምንዛሪ 255.4 ሚሊዮን ዶላር ብቻ ነበር፡፡ ይህም የዕቅዱ 54.2% ሲሆን ክንውኑ ከ2003 በጀት ዓመት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር የ22.9% ዕድገት አሳይቷል፡፡

የየንዑስ ዘርፉ አፈጻጸም ሁኔታ ሲታይ የጨርቃጨርቅና አልባሳት ንዑስ ዘርፍ ዕቅድ አፈጻጸም በ2004 በጀት ዓመት 49.4% በ2003 በጀት ዓመት 73% ነበር፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የሌሎች ንዑስ ዘርፎች አፈጻጸምም ከዕቅድ አንጻር የመቀነስ አዝማሚያ አሳይቷል፡፡ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች አፈጻጸም የዕቅዱ 54.4%፣የአግሮ ፕሮሰሲንግ 63%፣ እንዲሁም የኬሚካልና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪዎች አፈጻጸም 58.7% ነበር፡፡

በሌላ መልኩ በ2004 በጀት ዓመት የተገኘው የውጭ ምንዛሪ በመጠን ከ2003 በጀት ዓመት የተሻለ መስሎ ይታያል፡፡ ይሁን እንጂ በንዑስ ዘርፍ ደረጃም ሆነ በአጠቃላይ ሲታይ የበጀት ዓመቱ አፈጻጸም ከዕቅድ በታች ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው በ2017 ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ከታቀደው ግብ (17%) ላይ ለማድረስ ለዘርፉ የላቀ ትኩረት መስጠትና ባለፉት ሁለት ዓመታት የነበረውን የአፈጻጸም ክፍተት ለማካካስ ከፍተኛ ጥረትና ቁርጠኝነት የሚጠይቅ መሆኑን ነው፡፡

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እንደተመለከተው ፈጣን የኢንዱስትሪ ልማትና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚኖረው ሚና በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም የዘርፉን አፈጻጸም በእጅጉ በማሻሻል አሁን ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ያለውን የ4% ድርሻ በ2017 ወደ 17% ማድረስ ወሳኝ ይሆናል፡፡

በዚህ ረገድ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለዘርፉ የተቀመጠውን የዕድገት ግብ ለማሳካት ያሉት የቴክኖሎጂ አቅም መዋቅራዊ ችግሮችን መፍታት፣ ተጨማሪ ኢንቨስትመንቶችን መሳብ፣ ገበያ ማስፋፋት፣ የግብኣትና ጥሬ ዕቃ አቅርቦት ማሳደግ፣ የሠራተኛውና የኢንዱስትሪ አመራሩን ክህሎት ማሳደግንና ተገቢውን ተቋማዊ አደረጃጀት መቅረፅ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ባለፉት ሁለት ዓመታት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ወቅት የኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚጠበቅበትን ሚና እንዲጫወት ለማድረግ በርካታ የአቅም ግንባታ ሥራዎች ተሠርተዋል፣ ተቋማዊ አደረጃጀቶች ተፈጥረዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል በ2003 በተደረገው የመንግሥት አስፈጻሚ መ/ቤቶች አደረጃጀት ለውጥ መሠረት ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍን በኃላፊነት የሚከታተል የካቢኔ ሚኒስትሮች ጽ/ቤት ተቋቁሟል፡፡ ተቋማዊ አቅም ግንባታ፣ ቤንችማርኪንግ፣ የቁርኝት ፕሮግራምና የካይዘን ፕሮግራሞች በ2004 እንዲተገበሩ ተደርጓል፡፡ በጨርቃጨርቅ ለአራት አዳዲስና አራት የማስፋፊያ ፕሮጀክቶች፣ በቆዳ ኢንቨስትመንት ለስምንት ፕሮጀክቶች፣በአግሮ ፕሮሰሲንግ ለአሥር ፕሮጀክቶች፣ በፋርማሲዩቲካልና ኬሚካል ኢንዱስትሪዎች ለሦስት ፕሮጀክቶች ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፡፡

የመንግሥት ልማት ድርጅቶች አመራርና የፕራይቬታይዜሽን ሥራዎችን ለመደገፍ፣ አፈጻጸሙን ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል የኮርፖሬት አስተዳደር ሥርዓት እንዲዘረጋ ተደርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ደንቦችና መመሪያዎች ተቀረጸው የአፈጻጸማቸው ክትትል እንዲጠናከር ተደርጓል፡፡ ቀጥሎ ካለው ሠንጠረዥ 5 መረዳት እንደሚቻለው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በአቅም አጠቃቀም፣ በሽያጭ ገቢና ትርፍ እንዲሁም በኤክስፖርት አፈጻጸም መሻሻሎችን አሳይተዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 5፡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች አፈጻጸም**

| ተ.ቁ | ዋና ዋና ሥራዎች | መነሻ ዓመት (2003) | 2004 በጀት ዓመት | | ከመነሻ ዓመት ያለው ልዩነት በመቶኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | 2004 ዕቅድ | 2003 ክንውን |
| 1 | የተጨመረ እሴት በቢሊዮን ብር | 3.2 | 3.97 | 2.4 | 60.5 | (25) |
| 2 | የአቅም አጠቃቀም በመቶኛ | 78.0 | 98.0 | 82 | 83.7 | 5 |
| 3 | ትርፍ ከታክስ በፊት በቢሊዮን ብር | 2.6 | 4.06 | 2.0 | 49.0 | (23) |
| 4 | የኤክስፖርት ገቢ በሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር | 72.4 | 76.7 | 61.5 | 80.7 | (15) |

**ምንጭ፡- የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የ2004 ሪፖርት**

በተለያዩ የአገሪቷ ክፍሎች የኢንዱስትሪ ዞኖችን ለማቋቋም በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ በዚሁ

መሠረት የኢንዱስትሪ ዞን ልማት ዕቅዱ ተዘጋጅቶ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ የገበያ ትስስርን ለመፍጠር መሠረተ ልማቶች ተገንብተዋል፡፡ በዱከም ከተማ የሚገነባው የምሥራቅ ኢንዱስትሪ ዞን ግንባታ ሥራ እየተጠናቀቀ ቢሆንም የኢትዮ-ቱርክ ኢንዱስትሪ ዞንና የኮምቦልቻ ስኳር፣ ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ክላስተር ግንባታ ኢንቨስተሮቹ በቂ ዝግጅት ባለማድረጋቸው ምክንያት ሊጓተት ችሏል፡፡ በመሆኑም የቅርብ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የእነዚህን የኢንዱስትሪ ዞኖች ግንባታ ለማፋጠን ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ አዲስ አበባ፣ ኮምቦልቻ፣ ድሬደዋና አዋሳ ለኢንዱስትሪ ዞን ልማት የተመረጡ አራቱ ዋና ዋና ከተሞች ሲሆኑ በእነዚህ ከተሞች ለኢንዱስትሪ ዞን ልማት የሚሆኑ በድምሩ 3,735 ሄክታር መሬት በከተሞቹ አስተዳደር ተከልሎ ለግንባታ ዝግጁ ሆኗል፡፡

ባለፉት ሁለት ዓመታት የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት አቅም ውስንነት፣ በድጋፍ ሰጪ የመንግሥት ተቋማት መካከል ቅንጅት አለመኖር፣ የኢንዱስትሪ ግብኣቶች እጥረት፣ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ለመሳተፍ የግል ባለሀብቶች ያሳዩት ተነሳሽነት ማነስ፣ በዘርፉ ተጨባጭ የሆነ የኢንቨስትመንት ተሳትፎ አዝጋሚ መሆን ካጋጠሙ ችግሮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የፋብሪካዎች የቴክኖሎጂና የአመራር አቅም ውስንነት፣ የምርታማነት ማነስ፣ የሎጀስቲክስ ሥርዓቱ ቀልጣፋ አለመሆን፣ በምርት ጥራትም ሆነ በዋጋ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጠንካራ ውድድር መቋቋም አለመቻል በዘርፉ ጎልተው የታዩ ችግሮች ነበሩ፡፡

## 2. ክፍል ሁለት- የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ልማት ዓላማ፣ መነሻ መርሆዎችና መሠረታዊ አቅጣጫዎች (Pillars)

### 2.1 የኢንዱስትሪ ልማት ፍኖተ-ካርታ (Road map) ዓላማዎች

የኢንዱስትሪ ልማት ፍኖተ-ካርታ (Road map) ዋና ዓላማ በ2017 አገሪቷን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ዕድገት ደረጃ ላይ ለማድረስ የሚያስችል የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫን ለመጠቆም ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎቹ የሚከተሉት ናቸው፣

- በኢኮኖሚው የኢንዱስትሪ መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት፣
- የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አቅምን በማሳደግ የኢንዱስትሪ መሠረትን ማጠናከርና ማስፋፋት፣
- የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ዘርፍ አስተዋፅኦ የታቀደውን የ10.3% አማካይ የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ዓመታዊ ዕድገት የሚደግፍ መሆኑን ማረጋገጥ እና
- የአገር ውስጥና ከውጪ የሚገቡ ኢንቨስትመንቶችን ለማስፋፋት የሚያስችል የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫ ማስቀመጥ ናቸው።

### 2.2 የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ልማት መነሻ መርሆዎችና መሠረታዊ አቅጣጫዎች

የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ በኢንዱስትሪ ልማት ሂደቱ መንግሥትና የግሉ ዘርፍ በጋራ በሚኖራቸው ሚና ላይ ያተኮረ ቀጥሎ ያሉትን የኢንዱስትሪ ልማት መነሻ መርሆዎችን የሚከተል ነው።

- በመንግሥት የነቃ ተሳትፎና ድጋፍ የነፃ ገበያ ሥርዓት ማስፈን፣
- መንግሥት የአጠቃላይ ኢኮኖሚው የልማት አቅጣጫና ስትራቴጂ በመቅረጽ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ዕድገት ግቦች የተሳኩ መሆናቸውን የሚያረጋግጥበት አሠራር መከተል እና
- የግሉ ዘርፍ ነጻ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ ተገቢው የፖሊሲ፣ የተቋምና የመሠረተ ልማት ድጋፍ አገልግሎቶችን እንዲያገኝ ማድረግ።

### የኢንዱስትሪ ልማት መሠረታዊ አቅጣጫዎች (key pillars)

የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫ የልማት ተነሳሽነት (development initiatives)፣ ለዕድገት ወሳኝ የሆኑ ዘርፎችን ማስፋፋት (promotion of growth areas) እና አመቺ የሥራ ካባቢን መፍጠር (enhancing the enabling environment) የተሰኙ ሰፋፊ መሠረተ ሃሳቦችን የሚያቅፍ ሲሆን ይህም በሚከተሉት አራት የስትራቴጂ አቅጣጫዎች (strategic pillars) ላይ የተመሠረተ ነው።

1. **የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በኢንዱስትሪውና በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ዕድገት ውስጥ የሚኖረውን ሚና ቀጣይ ማድረግ፣**

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው የኢኮኖሚው ዕድገት ዋና መሠረት ሆኖ ይቀጥላል። የኤክስፖርት ምርትና ገቢ ምርቶችን የሚያመርቱ ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው የኢንዱስትሪ ዘርፎች ምርታማነታቸውን እንዲያሳድጉ፣ የምርታቸውንና ገበያቸውን እንዲያሳድጉና እንዲያስፋፉ ድጋፍ ይደረግላቸዋል። በኢንዱስትሪ ልማት ሂደቱ ለሥራ ዕድል ፈጣራና ለአካባቢ ጥበቃ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል። ከፍተኛ እሴት በሚጨምሩ ምርቶችና ሥራዎች፣ ከፍተኛ ካፒታልና ተገቢ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ የኢንቨስትመንት ሥራዎችን የበለጠ በማበረታታት ኢንቨስትመንቱ በፍጥነት ወደ እነዚህ መስኮች እንዲያተኩር ይደረጋል። በ2017 ኢንዱስትሪው በአገር ኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖረውን ድርሻ ለማሳደግና መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ኢኮኖሚ ዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ እንዲቻል የኢንዱስትሪ መዋቅራዊ ለውጥን ለማምጣት የሚያስችል የፖሊሲና የስትራቴጂ ድጋፍ ይደረጋል።

2. **በየክልሉ የተመጣጠነ የኢንዱስትሪ ልማት መኖሩን ማረጋገጥ**

ለኢንዱስትሪ ልማትና ዕድገት የተቀናጀ ድጋፍ እንዲኖር ለማድረግ በፌዴራል መንግሥትና በክልል መንግሥታት መካከል ያለው ጠንካራ ተቋማዊ ትስስር የበለጠ እንዲጎለብት ይደረጋል። በየክልሉ ያለውን እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ሥራ ላይ ለማዋልና የክልሉን ህዝብ ተጠቃሚ ለማድረግ በኢንዱስትሪ ልማቱ አማካይነት ድጋፍ ይደረጋል። በኢንዱስትሪ ልማት አማካይነት የሚመጣው ዕድገት ድህነትን በመቀነስ፣ አነስተኛ ገቢ ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የሥራ ዕድል በመፍጠርና ገቢያቸውን በማሻሻል የተመጣጠነ ክልላዊ ዕድገት እንዲኖር አስተዋፅኦ ያደርጋል።

ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ለአገሪቷ ኢንዱስትሪ ልማት ዋናው ሞተር በመሆናቸው እነዚህን ድርጅቶች ለማጠናከር ለየክልሉ ተገቢው ድጋፍ ይደረጋል። በየክልሉ ለሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች ያለምንም ውጣ ውረድ ተግባራቸውን ማከናወን እንዲችሉ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ይደረጋል።

3. **የአገሪቷን ኢንዱስትሪ ከቀጠናው አገሮችና ከዓለም አቀፍ ገበያና ልማት ጋር ማስተሳሰር**

በቀጠናው አገሮችና በዓለም አቀፍ ደረጃ እያደገ የመጣውን የኢኮኖሚ ትስስር አዝማሚያ ከሚፈጠረው አመቺ ሁኔታዎች የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ እገዛና ድጋፍ ይደረግላቸዋል። በቀጠናው

አገሮችም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚደረጉ የንግድ ስምምነቶች የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችን የመወዳደር አቅም ከማጎልበት አንጻር የሚታዩ ይሆናሉ፡፡

በአገሪቷ ያሉ ኩባንያዎች ባላቸው አቢይ ብቃት (core competence) ላይ እንዲያተኩሩና ተጠናክረው በቀጠናው አገሮችና በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ ሆነው እንዲገኙ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እና በመካከለኛና ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች መካከል የሚኖረው ትብብርና ከውጭ አገር በመልካም ተሞክሮነት ከተወሰዱ ኢንዱስትሪዎች ጋር የሚኖረው ትብብር በተቋም ደረጃ እንዲመቻች ይደረጋል፡፡ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት ገበያን በመፍጠር፣ ቴክኖሎጂን በማሸጋገርና የተወዳዳሪነት ብቃትን በማሻሻል ለአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች እገዛ ያደርጋል፡፡ በዓለም አቀፍ ገበያ ውድድር አሸናፊ ሆነው የወጡ ምርቶችን የበለጠ በማስተዋወቅ አገሪቷ በቀጠናው የምርጥ ምርቶችና አገልግሎቶች አቅራቢ ማዕከል ሆና እንዲትወጣ የተሟላ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

## 4. ኤክስፖርት-መርና ገቢ ምርቶች ተኪ የሆነ ኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫን መከተል

ፈጣን የኢንዱስትሪ ልማት ለማምጣት ኢንዱስትሪዎች የግብርና ልማት አቅጣጫን ተከትለው ለግብርና አመቺ የሆኑ ግብኣቶችና ምርቶችን የሚያመርቱ፣ በግብርና ምርቶች ላይ እሴት ጨምረው ለገበያ የሚያቀርቡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ የማምረቻ መሣሪያዎችን ከውጪ በማስገባት፣ ምርቶችን በብዛት በመላክና የውጭ ምንዛሪን በማስገኘት የኢንዱስትሪ ልማትን ማፋጠን ይቻላል፡፡

እሴት ለተጨመረላቸው የግብርና ምርቶች ሰፊና አስተማማኝ የዓለም ገበያ በመኖሩ እነዚህን ምርቶች በተሳካ ሁኔታ ወደ ውጪ ገበያ መላክ የአገራችንን ኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫና ፈጣን ዕድገት የሚወስን ይሆናል፡፡ የኤክስፖርት ኢንዱስትሪዎችን በማጠናከር በዓለም ገበያ ላይ የሚኖረው የተወዳዳሪነት አቅም በአንዱ ወይም በሌላ መልኩ በሌሎች ዘርፎችም የተወዳዳሪነት አቅም ይፈጥራል፡፡

በአሁኑ ጊዜ አገሪቷ ከውጪ የሚታስገባው የምርት መጠን ወደ ውጪ ከሚትልከው በእጅጉ ይበልጣል፡፡ በሁለቱም መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ ሲሆን የገቢ ምርት መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ በማደግ ላይ ይገኛል፡፡ ይህንን ክፍተት ለመሙላት የገቢ ምርቶችን ለመተካት በሚያስችሉ ስትራቴጂያዊ ዘርፎች ላይ ማተኮርና ከፍተኛ ኢንቨስትመንት መመደብ እንዲሁም በዚህ ዘርፍ ለሚሠሩ ኢንዱስትሪዎች ሁሉን አቀፍ ድጋፍ መስጠት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ገቢ ምርቶችን የመተካት አቅጣጫ ተከትለው የሚሠሩ ኢንዱስትሪዎች ምርታማነትና የመወዳደር አቅም እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡ የአገር ውስጥ ግብኣት አቅርቦት መሠረት እንዲሰፋ በማድረግ እነዚህ ኢንዱስትሪዎች በውጪ ግብኣት ላይ ያላቸውን ጥገኝነት መቀነስ ያስፈልጋል፡፡

## 3. ክፍል ሦስት- አገራዊ የልማት ራዕይ፣ግብና ዒላማ

**አጠቃላይ አገራዊ ራዕይ**

*‹‹በህዝብ ተሳትፎና በህዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር የሰፈነባት፣ ማህበራዊ ፍትህ የነገሰባት፣ ከድህነት ተላቃ መካከለኛ ገቢ ያላት ኢትዮጵያን በ2017 እውን ማድረግ ነው"፡፡*

**በኢኮኖሚ መስክ የአገሪቷ ራዕይ**

*‹‹ከፍተኛ ተክኖሎጂና ምርታማነት ደረጃ ላይ የደረሰ ዘመናዊ ግብርናና በኢኮኖሚው ውስጥ የመሪነት ሚናን መጫወት የሚችልበት ደረጃ ላይ የደረሰ ኢንዱስትሪ መገንባት፣ ፈጣን፣ ቀጣይና ፍትሃዊ ኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት የተረጋገጠበትና የዜጎች የነፍስ ወከፍ ዓመታዊ ገቢ መካከለኛ ዕድገት ያላቸው አገሮች ደረጃ እንዲደርስ ማስቻል ነው"፡፡*

### 3.1 አገራዊ የልማት ግቦች

ይህ የ2005-2017 የኢንዱስትሪ ልማት ፍኖተ-ካርታ (road map) ፈጣንና ሰፊ መሠረት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣትና የአገሪቷን ራዕይ ለማሳካት አስተዋፅኦ የሚያበረክት ነው፡፡ በዚህ የኢንዱስትሪ ልማት ፍኖተ-ካርታ (road map) ዝግጅት መነሻ ተደርጎ የተወሰደው ፈጣንና ዘላቂ ልማት በማስፈን ድህነትን የማስወገድ ዕቅድ (PASDEP) ትግበራ እና በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችን በመፍታት ረገድ የተገኙ ተሞክሮዎች ናቸው፡፡

በዚሁ መሠረት የሁለት አምስት ዓመታት ዕቅድ አጠቃላይ ግብ አስከፊ ድህነትን ጨርሶ በማስወገድ ሁሉም መሠረታዊ የሰው ልጅ ፍላጎቶች የተሟሉበት መካከለኛ ገቢ ያላት አገርና የዕድገት አንቀሳቃሽ ሞተር መገንባት ነው፡፡

### 3.2 አገራዊ የልማት ዒላማዎች

#### 3.2.1 የመካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት ደረጃና የኢንዱስትሪ መዋቅር

የመካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች ትርጉምና መመዘኛ እንደዚሁም መካከለኛ ገቢ ደረጃ ላይ ለመድረስ የሚያስፈልገው የኢኮኖሚ መዋቅር ለውጥ በተመለከተ በርካታ ልዩነቶች አሉ፡፡ በዓለም ባንክ አሠራር መሠረት የዓለም አገሮች ዝቅተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ገቢ ያላቸው አገሮች ተብለው ይከፋፈላሉ፡፡ የአገሮች የገቢ ደረጃ ከሚወሰንባቸው መንገዶች አንዱ አንድ አገር ባለው የነፍስ ወከፍ ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢ መጠን በአሜሪካን ዶላር ሲሆን ይህም የአትላስ ምንዛሪ ለውጥ ዘዴን (Atlas method of currency conversion) በመጠቀም የሚሰላ ነው፡፡

በዚሁ መሠረት 995 የአሜሪካን ዶላር ወይም ከዚያ በታች ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ ያላቸው አገሮች ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው አገሮች ተብለው ይታወቃሉ፡፡ ከ996 የአሜሪካን ዶላር እስከ 3,945 የአሜሪካን ዶላር ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ ያላቸው ታችኛው መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች ሲባሉ ላይኛው መካከለኛ ገቢ አላቸው የሚባሉ አገሮች ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢያቸው ከ3,946 የአሜሪካን ዶላር እስከ 12,195 የአሜሪካን ዶላር ነው፡፡ ከ12,166 የአሜሪካን ዶላር ነፍስ ወከፍ ዓመታዊ ገቢ ያላቸው አገሮች ከፍተኛ ገቢ ያላቸው አገሮች ተብለው ይታወቃሉ፡፡ የአገሮችን የገቢ ደረጃ ለመወሰን ያለው ሌላ ዘዴ ደግሞ በአገሮች መካከል ያለው የዋጋ ልዩነት ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ የህዝቡን የመግዛት አቅም(Purchasing Power Parities) መሠረት ያደረገ ነው፡፡

እ.ኤ.አ በ2012 የዓለም አቀፍ የዕድገት ማዕከል (International Growth Center) ተመራመሪዎች የመካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች ደረጃ ላይ ለመድረስ ለታዳጊ አገሮች የሚያስፈልገውን ዕድገትና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ተጨባጭ ሞዴል (ቀመር) ሠርተው አቅርበዋል፡፡ በዚህ ሞዴል (ቀመር) ታዳጊ አገሮች መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች የኢኮኖሚ መዋቅር ሁኔታ በማጥናት የተገኘውን ልምድ ከአገራቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በተጣጣመ መልኩ ይጠቀሙበታል፡፡

እ.ኤ.አ የ2010 የዓለም ባንክ የልማት ደረጃ አመልካች የመረጃ ቋት (World Bank Development Database Indicator) መሠረት በማድረግ እ.ኤ.አ ከ1960 ጀምሮ ወደ መካከለኛ ገቢ ደረጃ ያለፉ አገሮች ዝርዝር በዚህ ሞዴል ተለይቶ ቀርቧል፡፡ እነዚህ አገሮች ተለይተው መታወቃቸው የኢኮኖሚ መዋቅራቸውን ከኢትዮጵያ የኢኮኖሚ መዋቅር ሁኔታ ጋር ለማነጻጸር አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል፡፡ እነዚህ አገሮች ከታዳጊ የአፍሪካ አገሮች ጋር ያላቸው የባህሪ ተመሳሳይነት፣ የህዝብ ብዛት (ከአንድ ሚሊዮን በላይ መሆኑ)፣ የኢኮኖሚ ዕድገት መዋቅርና የመሳሳሉት መስፈርቶች በመጠቀም የተመረጡ አገሮች ለንጽጽር እንዲወሰዱ ተደርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች በነዳጅ ሀብት ላይ የተመሠረተ ዕድገት ያስመዘገቡና ነዳጅ ሀብት ሳይኖራቸው ዕድገት ያስመዘገቡ አገሮች በማለት ተለይተዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ለንጽጽር የተመረጡ አገሮች ከተለዩ በኋላ የተመረጡ የማህበራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት አመልካች የአሃዝ መረጃዎችን (variables) በመውሰድ አገሮቹ ወደ መካከለኛ ገቢ ደረጃ በተሸጋገሩበት ዘመን ላይ ከእነዚህ የዕድገት አመልካች መረጃዎች (variables) አንጻር የነበራቸው የዕድገት ደረጃ መነሻ ተደርጎ (benchmark) ተወስዷል፡፡ በዚሁ መሠረት የተገኘው አማካይ ውጤት መካከለኛ ገቢ ላላቸው አገሮች የሚያስፈልገው የኢኮኖሚ መዋቅር ሞዴል ዓይነት ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 2 ቀርቧል፡፡

የተመረጡ የኢትዮጵያ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታና የማህበራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት አመልካች አሃዛዊ መረጃ ውጤቶች (variables) በመውሰድ ሞዴል (MMIC)

መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ኢኮኖሚ መዋቅር ጋር የተደረገው ንጽጽር በሠንጠረዥ 6 ቀርቧል፡፡ በሁለቱም መካከል የሚታየው ክፍተት መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች ዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ በ2017 ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋትን የኢኮኖሚ መዋቅር ለውጥ ዓይነት የሚያመለክት ነው፡፡

ሠንጠረዥ 6 በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ መዋቅርና መካከለኛ ገቢ ባላቸው አገሮች ኢኮኖሚ መዋቅር ሞዴል መካከል ሰፊ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡ ለምሳሌ ያህል የኢንዱስትሪ ዘርፍን ብቻ ብንወስድ ዘርፉ ለአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የሚያበረክተው አስተዋፅኦ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ኢኮኖሚ መዋቅር ሞዴል አንጻር ሲታይ በ20 ነጥብ ዝቅ ብሎ ይገኛል፡፡ ይህም የሚያሳየው በ2017 መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች ደረጃ ላይ ለመድረስ የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ዘርፍ አሁን ካለበት ከሁለት እጥፍ በላይ ማደግ እንደሚኖርበት ነው፡፡ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍም ተመሳሳይ ሁኔታ ይታያል፡፡

በ2005 የኢትዮጵያ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የነበረው ድርሻ 4% ብቻ ሲሆን መካከለኛ ገቢ ባላቸው አገሮች ዘርፉ ያለው ድርሻ 17% በመሆኑ የ13% ክፍተት ይታያል፡፡ ይህን ክፍተት ለመዝጋትና በ2017 ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ድርሻን 17% ለማድረስ ሀብት በማንቀሳቀስና ለዘርፉ በመመደብ የላቀ ትኩረት ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ይህም ማለት በ2017 የተቃደው መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች ዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ዕድገት የተለየ ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡

## ሠንጠረዥ 6፡ ዋና ዋና የማክሮ የኤክኖሚ ዕድገት ቁልፍ አመልካቾች (key indicators)

| | ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የግብርና ዘርፍ ድርሻ በ% | ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የኢንዱስትሪ ዘርፍ ድርሻ በ% | ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ድርሻ በ% | ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የአገልግሎት ዘርፍ ድርሻ በ% | ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የኤክስፖርት ድርሻ በ% | ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የገቢ ምርት ድርሻ በ% | ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የጠቅላላ ቋሚ ከፒታል ሀብት ድርሻ በ% | ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የተጣራ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ድርሻ በ% | ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የአገር ውስጥ ቁጠባ ድርሻ በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የመካከለኛገቢ አገሮች የኢኮኖሚ መዋቅር ሞዴል | 20.7 | 30.7 | 17 | 48.6 | 30.5 | 37.4 | 26.6 | 45 | 21.6 |
| የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መዋቅር (2005) | 44 | 11.1 | 4 | 45.6 | 14 | 52.1 | NA | NA | 16.5 |
| ልዩነት | 23.3 | (19.6) | (13) | (3) | (16.5) | 14.5 | - | - | (5.1) |

ምንጭ፡- ዓለማቀፍ የዕድገት ማዕከል (እ.ኤ.አ 2012) እና የዳሰሳ ጥናት

## ሠንጠረዥ 7፡ የዜጎችና ማህበራዊ ልማት ዕድገት ቁልፍ አመልካቾች (key indicators)

| | ከተፈጠረው ጠቅላላ የሥራ ዕድል የግብርና ዘርፍ ድርሻ በ% | ከተፈጠረው ጠቅላላ የሥራ ዕድል የኢንዱስትሪ ዘርፍ ድርሻ በ% | ከጠቅላላው ህዝብ የገጠር ነዋሪ ህዝብ ብዛት በ% | የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ በ% | ነፍስ ወከፍ የኤሌክትሪክ ኃይል ፍጆታ በኪሎዋትአወር) | የሀብት ክፍፍል ሁኔታ አመልካች( GINI Index) | በሀብታምና ደሃ መካከል ያለው የሀብት ክፍተት (በቀን 1.25 የአሜሪካን ዶላር ዝቅተኛ ገቢ መነሻ በማድረግ) በ% | የህዝብ ቀጥር ዕድገት በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች የኢኮኖሚ መዋቅር ሞዴል | 41.2 | 20.5 | 62.3 | 46.5 | 403.7 | 38.9 | 5.3 | 2.2 |
| የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መዋቅር (2005) | 80 | 5 | 85 | 38.4 | 3.63 | 29.8 | NA | 2.4 |
| ልዩነት | 38.8 | (15.5) | 22.7 | (8.1) | (399.3) | (9.1) | - | 0.2 |

ምንጭ፡- ዓለማቀፍ የዕድገት ማዕከል (እ.ኤ.አ 2012) እና የዳሰሳ ጥናት

ካላይ በሠንጠረዥ 8 ከተቀመጠው የዜጎች ኑሮና ማህበራዊ ልማት ዕድገት አመልካቾች ንጽጽር ለመረዳት እንደሚቻለው በኢትዮጵያና መካከለኛ ገቢ ባላቸው አገሮች የኢኮኖሚ መዋቅር መካከል ሰፊ ልዩነት መኖሩን ነው፡፡ በመሆኑም እስከ 2017 የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ በማምጣት እነዚህን ክፍተቶች ለማጥበብ ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍና ከታቀደው የኢንዱስትሪ ዞን ልማት ብዙ ይጠበቃል፡፡

### 3.2.2 የኢትዮጵያ ልማት ዒላማዎች

ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በተገኙ መረጃዎች መሠረት በዚህ ጥናት የተመረጡ አገራዊ የልማት ዒላማዎች ትንበያ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ ተጠቃሎ ቀርበዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 8፡ በማክሮ ደረጃ የተመረጡ የዕድገት አመልካቾች (variables) ትንበያ**

(ከ2005 እስከ 2017)

| የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ዕድገት ምጣኔ እድገት (11.2% አማካይ ዕድገት) | 2005 | 2007 | 2012 | 2017 |
|---|---|---|---|---|
| | 11.2 | 11.5 | 11.3 | 10.8 |
| የነፍስ ወከፍ ዓመታዊ ገቢ መጠን (በአሜሪካን ዶላር) | 568.1 | 676.5 | 1116.6 | 1880.2 |
| የነፍስ ወከፍ ዓመታዊ ገቢ ዕድገት ምጣኔ (በ%) | 9.3 | 9.9 | 10.8 | 11.07 |
| የህዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔ (በ%) | 2.44 | 2.44 | 2.26 | 2.05 |
| ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የግብርና ዘርፍ ድርሻ (በ%) | 38.17 | 36.38 | 34.09 | 32.67 |
| ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የኢንዱስትሪ ዘርፍ ድርሻ (በ%) | 15.25 | 18.73 | 22.37 | 27.33 |
| ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ድርሻ (በ%) | 5 | 7 | 12 | 17 |
| ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የአገልግሎት ዘርፍ ድርሻ (በ%) | 46.58 | 44.85 | 43.54 | 40.01 |
| ከድህነት መስመር በታች የሚኖረው የህዝብ ቁጥር (በ%) | 24.4 | 22.2 | 16.7 | 11.1 |

**ምንጭ፡- ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተገኘ መረጃና የጥናት ቡድኑ ግምት**

በዕቅድ ዘመኑ (2005-2017) የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አማካይ ዓመታዊ ዕድገት 11.2% እንደሚሆን የተገመተ ሲሆን ይህም በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ይኖራል ተብሎ በመንግሥት በተገመተው የ11.2% የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ዕድገት (real GDP) መሠረት ነው፡፡

የኢኮኖሚ ዕድገት ዒላማዎች የተገመቱት በሦስት አማራጮች ነው፡፡ የመጀመሪያው አማራጭ (የተመረጠው አማራጭ) በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጠ መሠረታዊ የዕድገት አማራጭ(Base case scenario) ሲሆን የ11.2% የአገር

ውስጥ ጠቅላላ ምርት (real GDP) ዓመታዊ ዕድገትን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ በዚህ አማራጭ የህዝብ ዕድገት 2.3% እንደሚሆን የተገመተ ሲሆን አገሪቷ በምትከተለው የህዝብ ምጣኔ ፖሊሲ ምክንያት የህዝብ ብዛት ዕድገት ምጣኔ በየዓመቱ በ20% እንደሚቀንስ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ በ2005 የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት 84.3 ሚሊዮን እንደሚሆን ተገምቷል፡፡

ሁለተኛው የዕድገት አማራጭ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጠው ከፍተኛው የዕድገት አማራጭ(High case scenario) ሲሆን በዚህ አማራጭ መሠረት የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት በየዓመቱ በ14.9% እንደሚያድግ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ በዚህ አማራጭ መሠረት የዜጎች የነፍስ ወከፍ ዓመታዊ ገቢ በ2007 ዓ/ም 746 የአሜሪካን ዶላር፣በ2012 ዓ/ም 1,451 የአሜሪካን ዶላር፣ በ2017 ዓ/ም ደግሞ 2,877 የአሜሪካን ዶላር እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡

ሦስተኛው የዕድገት አማራጭ የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ዕድገት ቀስ በቀስ እየቀነሰ የሚሄድበትን ሁኔታ ታሳቢ ያደረገ አማራጭ ነው፡፡ በዚህ አማራጭ እንደማንኛውም ታዳጊ አገር ኢኮኖሚ በመጀመሪያ አካባቢ ከፍተኛ የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት አንጻራዊ ዕድገት እንደሚኖርና ኢኮኖሚው እየሰፋ ሲመጣ የዕድገት መጠኑ ቀስ በቀስ እንደሚቀንስ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ በዚህ አማራጭ መሠረት የዜጎች የነፍስ ወከፍ ዓመታዊ ገቢ በ2007 ዓ/ም 672 የአሜሪካን ዶላር፣በ2012 ዓ/ም 971 የአሜሪካን ዶላር፣ በ2017 ዓ/ም ደግሞ 1,380 የአሜሪካን ዶላር እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡

በዚህ ጥናት የተመረጠው የዕድገት አማራጭ የሚከተሉትን ታሳቢዎችን መሠረት ያደረገ ነው፣

- ፈጣንና ዘላቂ ልማት በማስፈን ድህነትን የማስወገድ ዕቅድ (PASDEP) ትግበራና በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ሂደት የተፈጠሩ አመቺ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታዎች እንደሚቀጥሉና በመጀመሪያው አምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የተመዘገበው ዕድገት ቀጣይ እንደሚሆንና በዚሁ መሠረት በሚቀጥሉት 13 ዓመታት አማካይ የኢኮኖሚው ዕድገት 11.2% እንደሚሆን፣
- የመካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች የኢኮኖሚ መዋቅር ሞዴል መሠረት የኢትዮጵያ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የሚኖረው ድርሻ አሁን ካለው 4% ወደ 17% ማደግ ይኖርበታል፡፡ የተመረጠው የዕድገት አማራጭ በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ይህንን ዕድገት የሚያረጋግጥ መሆኑን፣
- በ2017 የአገሪቷ ራዕይ የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የዜጎች ዝቅተኛው ነፍስ ወከፍ ገቢ 1,000 የአሜሪካን ዶላር እንደሚሆን ዒላማ አድርጓል፡፡ አሁን በተመረጠው የዕድገት አማራጭ ማለትም የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መነሻ የዕድገት አማራጭ መሠረት በ2017 የዜጎች

ነፍስ ወከፍ ገቢ 1,880 የአሜሪካን ዶላር ይደርሳል ተብሎ ይገመታል። ይህም መጠን የመካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች ዝቅተኛው የነፍስ ወከፍ ገቢ መጠን ቢሻሻል ለውጡን ማስተናገድ እንደሚችል ታሳቢ ተደርጓል።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዕድገት ከ2007 በኋላም በተመሳሳይ ሁኔታ እንደሚቀጥል የተወሰደው መሠረታዊ ታሳቢ አሳማኝ በመሆኑ ከ2007 በኋላ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጠውን የዕድገት ምጣኔ መውሰዱ ተገቢ ይሆናል።

በዚሁ መሠረት በዚህ ጥናት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጠው መሠረታዊ የዕድገት አማራጭ (Base case scenario) እንዲወሰድ ተደርጓል። በዚህ አማራጭ መሠረት የዜጎች ነፍስ ወከፍ ዓመታዊ ገቢ በ2007 ዓ/ም 677 የአሜሪካን ዶላር፣ በ2012 ዓ/ም 1,117 የአሜሪካን ዶላር፣ በ2017 ዓ/ም ደግሞ 1,880 የአሜሪካን ዶላር እንደሚደርስ ተገምቷል። ይህን የዕድገት አማራጭ መሠረት በማድረግ የተመረጡ አገራዊ የዕድገት ዒላማዎች ተቀምጠዋል።


በሦስቱም የዕድገት አማራጮች የሚኖረው የዜጎች ነፍሰ ወከፍ ዓመታዊ ገቢ ትንበያ በሠንጠረዥ 9 የተመለከተ ሲሆን ከዚያም በመነሳት የተሠራውና የሦስቱም የዕድገት አማራጮች የዕድገት አቅጣጫ የሚያሳይ ቻርት ቀጥሎ ቀርቧል።

## ሠንጠረዥ 9፡ የዜጎች ነፍስ ወከፍ ዓመታዊ ገቢ መጠን ዕድገት

### (በሦስት የተለያዩ የዕድገት አማራጮች)

| የዕድገት አማራጭ | 2005 | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን መነሻ የዕድገት አማራጭ (11.2%)<br><br>የዜጎች ነፍስ ወከፍ ገቢ በአሜሪካን ዶላር | 561.8 | 615 | 677 | 745 | 823 | 910.4 | 1008 | 1117 | 1238.1 | 1374 | 1525 | 1693 | 1880.2 |
| የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ከፍተኛው የዕድገት አማራጭ (14.9%)<br><br>የዜጎች ነፍስ ወከፍ ገቢ በአሜሪካን ዶላር | 579 | 657 | 746 | 850 | 970 | 1108 | 1267 | 1451 | 1662 | 1905 | 2185 | 2507 | 2877 |
| የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የዕድገት ምጣኔ በአንጻራዊ አነጋገር እየቀነሰ የሚሄድበት የዕድገት አማራጭ (10.3%) | 568. | 617 | 672 | 723 | 779 | 838 | 901 | 971 | 1045 | 1124 | 1207 | 1293 | 1380.1 |


**ምንጭ፡ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር የተገኘ መረጃን መሠረት በማድረግ የተሰላ**




ቻርት 2፡ በሦስቱ የዕድገት አማራጮች የነፍስ ወከፍ ገቢ ዕድገት ዒላማዎች

**አገር አቀፍ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ዕድገት ዒላማ**

በተመረጠው የዕድገት አማራጭ መሠረት የአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት በ2007 ዓ/ም 59.9 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር፣በ2012 ዓ/ም 111 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር፣በ2017 ዓ/ም ደግሞ 207 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ የኢንዱስትሪ ዘርፍ አስተዋፅኦ በ2007 ዓ/ም 11.2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር፣በ2012 ዓ/ም 24.8 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር፣በ2017 ዓ/ም ደግሞ 56.5 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚሆን ይገመታል፡፡ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የኢንዱስትሪው ንዑስ ዘርፍ እንደመሆኑ መጠን ቀስ በቀስ የአንበሳውን ድርሻ እንደሚይዝና በ2007 ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የሚኖረው አስተዋፅኦ 4.2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡ በሁለተኛውና በሦስተኛው የዕቅድ ምዕራፍ ላይ ለዘርፉ በተለይ በሚሰጠው ትኩረትና በሚደረገው የላቀ እንቅስቃሴ ምክንያት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የሚኖረው ድርሻ በ2012 ዓ/ም ወደ 13.3 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚያሻቅብና ከዚያም በ2017 ዓ/ም 35.2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚደርስ ቀጥሎ ካለው ቻርት 3 መረዳት ይቻላል፡፡





ቻርት 3፡ የኢንዱስትሪው ዘርፍና የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የሚኖራቸው ድርሻ

**የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መዋቅር**

አሁን ባለው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መዋቅር የአገልግሎት ዘርፍ ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ትልቁን ድርሻ (45%) የሚይዝ ሲሆን በመቀጠል የግብርናው ዘርፍ 44% ይይዛል፡፡ የኢንዱስትሪው ዘርፍ አስተዋፅኦ ከሁሉም ዘርፎች ያነሰ ሲሆን ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት(real GDP) የዘርፉ ድርሻ 11% ብቻ ነው፡፡ የታቀደውን የኢንዱስትሪ ልማት ግብ ለማሳካትና በ2017 መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ ለኢንዱስትሪው ዘርፍ የተለየ ትኩረትና ድጋፍ ምክንያት በዘርፉ የበለጠ መነቃቃትን በመፍጠር አሁን ያለውን የኢኮኖሚ መዋቅር መለወጥ እንደሚያስፈልግ እሙን ነው፡፡ በዚሁ መሠረት በ2007 የኢንዱስትሪው ዘርፍ ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የሚኖረው ድርሻ ወደ 19% እንደሚያድግ፣ በ2012 የዘርፉ ድርሻ ወደ 22.4% ከፍ እንደሚልና በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ (2017) 27% እንደሚደርስ ግብ ተጥሏል፡፡ የኢንዱስትሪው ዘርፍ ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የሚይዘው ድርሻ በዚህ መልኩ እያደገ ሲመጣ ሌሎች ዘርፎች

የሚኖራቸው አስተዋፅኦ በአንጻሩ እየቀነሰ እንደሚሄድ ቀጥሎ ካለው ቻርት 4 ሁኔታ መረዳት ይቻላል፡፡




ቻርት 4፡ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ የሚኖረው የኢኮኖሚ ዘርፎች መዋቅር

በአጠቃላይ በ2017 የኢንዱስትሪው ዘርፍ ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የሚኖረው ድርሻ 27% ሲሆን የአገልግሎት ዘርፉ 40% ይይዛል፡፡ የግብርናው ዘርፍ ድርሻ ከ33% በታች እንደሚሆን ይገመታል፡፡ ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የኢንዱስትሪ ዘርፍ ድርሻ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 27% እንደሚደርስ በዚህ ጥናት የተገመተው ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው የኢንዱስትሪ ዘርፎች ማሻሻያና ማስፋፊያ (upgrading & expansion) ሥራዎች እንዲሁም ለዘርፉ የሚደረጉ ድጋፎች በስፋት እንደሚኖሩ ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

የግብርና፣የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፎች በሦስቱ የዕድገት አማራጮች ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት ይኖራቸዋል ተብሎ የተገመተው አስተዋፅኦ ቀጥሎ በሠንጠረዥ 10 ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 10፡ የኢኮኖሚ ዘርፎች ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የሚኖራቸው ድርሻ**


**(በሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር)**

| የኢኮኖሚው ዘርፍ ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የሚኖረው ድርሻ | የዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ምዕራፍ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 2005 | 2007 | 2012 | 2017 |
| ግብርና | 18048.43 | 21776.58 | 37730.8 | 67526.15 |
| ኢንዱስትሪ | 7210.862 | 11211.52 | 24759.11 | 56488.81 |
| አገልግሎት | 22025.05 | 26864.56 | 48190.06 | 82697.31 |
| የአገር ውስጥ አጠቃላይ ምርት | 47284.34 | 59852.66 | 110680 | 206712.3 |

***ምንጭ፡ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተገኘ መረጃን መሠረት በማድረግ የተሰላ***

## በኢንዱስትሪ ዘርፍ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አስተዋፅኦ

በ2005 የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ከኢንዱስትሪው ዘርፍ የነበረው ድርሻ 33% ነበር፡፡ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር 2005-2017 ትንበያ መሠረት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ዘርፍ በ2007 ከኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚይዘው ድርሻ 37% እንደሚሆንና በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ (2017) የዘርፉ ድርሻ 67% እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡ በሚቀጥሉት 13 ዓመታት ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋትና የምርት ዓይነቶችን በማሳደግ፣ የነባር ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም በማሻሻል እንዲሁም አዳዲሶችን በማቋቋም በሚደረገው እንቅስቃሴ ዘርፉ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረው አስተዋፅኦ በእጅጉ እንደሚያድግ ይጠበቃል፡፡ ከቻርት 4 መረዳት እንደሚቻለው በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ (2017) የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት 17% ድርሻ እንደሚይዝ ይገመታል፡፡




ቻርት 5፡ ከኢንዱስትሪ ዘርፍ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ድርሻ

## 4. ክፍል አራት- የኢንዱስትሪ ልማት ራዕይ፣ አቅጣጫ፣የስትራቴጂ ዓላማዎችና የአፈጻጸም ምዕራፎች

### 4.1 የኢንዱስትሪ ልማት ራዕይ

የኢንዱስትሪ ዘርፍ በአገር ኢኮኖሚ ዕድገት በሚኖረው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ምክንያት የዘርፉ ልማት ዕቅድ በአገራዊ ራዕይ 2017 ላይ የተመሠረተ አጠቃላይ ራዕይ የያዘና ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ባለድርሻ አካላት የሚጠበቀውን አስተዋፅኦ የሚያንጸባርቅ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ራዕይ፡

> *"በ2017 የኢትዮጵያን ህዝብ የኑሮ ደረጃ በእጅጉ መለወጥ የሚችል፣ በአፍሪካ የላቀ የማኑፋክቸሪንግ አቅም ያለው፣መሠረተ ሰፊና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ፣ ለተፈጥሮ አካባቢ ምቹ የሆነ የኢንዱስትሪ ዘርፍ መገንባት ነው፡፡"*

በዚህ ራዕይ መሠረት የአገሪቷ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ከወቅቱ ሁኔታ ጋር የሚሄድ፣ ገበያ-መርና ከፍተኛ እሴት የጨመሩ ተወዳዳሪ ምርቶችን ማምረት የሚችል መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ዘርፉ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ከፍተኛ ቁርኝት እንዲኖረውና ለተፈጥሮ አካባቢ ምቹ ወደ ሆኑ አዳዲስ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች እንዲስፋፉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### 4.2 የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫ

ፈጣንና ዘላቂ የኢንዱስትሪ ልማት ለማረጋገጥና የኢንዱስትሪው ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ ቁልፍ ሚና እንዲኖረው ለማድረግ ለዘርፉ ዕድገት አመቺ ሁኔታዎችን መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

በኢንዱስትሪው ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ማዕቀፍ መሠረት በዕቅዱ ዘመን መጀመሪያ ላይ ጉልበትን በስፋት የሚጠቀሙ፣ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ሰፊ ትስስር ያላቸው፣ ኤክስፖርት-መርና ገቢ ምርቶች ተኪ የሆኑ ኢንዱስትሪዎች የሚቋቋሙና የሚስፋፉ ሲሆን ወደ ዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች የሚለሙ ይሆናል፡፡ በዚህ የስትራቴጂ አቅጣጫ መሠረት ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በማስፋፋት እንዲሁም መካከለኛና ትላልቅ ኢንዱስትሪዎችን በማልማት ላይ ከፍተኛ ትኩረት ይደረጋል፡፡ በዚሁ መሠረት በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት የሚከተሉት አምስት የልማት አቅጣጫዎች ተቀይሰዋል፡፡

#### 1. ነባር ኢንዱስትሪዎችን ማሻሻልና የማምረት አቅማቸውን ማሳደግ

በዕቅድ ዘመኑ አንዱ ቁልፍ የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫ ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው ነባር መካከለኛና ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም ማሳደግ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ቀጥሎ ባሉት የኢንዱስትሪ ዘርፎች የሚገኙት መካከለኛና

ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቷቸው የተመረጡ ሲሆን በዕቅድ ዘመኑ በየደረጃው የተቀመጠውን የልማት ግብ ለማሳካት ለነዚህ ኢንዱስትሪዎች የተሟላ ድጋፍ ይደረጋል፡፡ እነዚህም፡-

- የጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪዎች፣
- የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች፣
- የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች፣
- የኬሚካልና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪዎች እና
- የብረታብረትና እንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ናቸው፡፡

በአሁኑ ጊዜ እነዚህ ኢንዱስትሪዎች ከአቅማቸው በታች በማምረት ላይ ይገኛሉ፡፡ ሁሉም ባይሆኑ አብዛኞቻቸው ካላቸው የማምረት አቅም 40% ብቻ በመጠቀም ላይ ናቸው፡፡ በዚህ የዕቅድ ዘመን እነዚህ የተመረጡ ኢንዱስትሪዎች ምርትና ገበያን በማስፋፋት የማምረት አቅማቸው እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

## 2. በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችና የምርት ዓይነቶችን ማስፋፋት

በ2017 መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች የዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ የተያዘውን ራዕይ እውን ለማድረግ ሌላው የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫ የሚሆነው በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ አዳዲስ የምርት ዓይነቶችና ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት ነው፡፡ ይህም ቅድሚያ ትኩረት በተሰጣቸው ነባር ኢንዱስትሪዎች አዳዲስ የምርት ዓይነቶችን ማምረትና ሌሎች አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችን በዘርፉ መክፈትን ያካትታል፡፡ በዚሁ መሠረት አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችና የምርት ዓይነቶች የተመረጡት የሚከተሉትን መስፈርቶች በመጠቀም ነው፡፡

- የገበያ ሁኔታ፣
- በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚኖረው የእሴት ጭማሪ (value chain)፣
- እሴት ለመጨመር የሚኖረው አማራጭ እና
- ለኢንዱስትሪው/ምርቱ የሚያስፈልገው እምቅ ሀብት ሁኔታ፡፡ (ለበለጠ ዝርዝረ አባሪ 4 ይመልከቱ)፡፡

በዚሁ መሠረት በዕቅድ ዘመኑ የመጀመሪያና መጨረሻ ምዕራፎች የሚከተሉት ኢንዱስትሪዎች እንዲቋቋሙ ይደረጋል፣

- **አግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች**
  - የእንጨት ውጤቶችን የሚያመርቱ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች፣

- በቀጣይ በሚገነቡ ግድቦች አካባቢ የባህር ምግቦችን የሚያቀነባብሩ ፋብሪካዎች እና
- የቅመማ ቅመም ማምረቻ ፋብሪካዎች፡፡

➢ **ጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪዎች**
  - ሰው ሠራሽ ጭረቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣
  - ቴክኒካል ጨርቃጨርቅ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች (technical textile) እና
  - የተፈጥሮ ጭረቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች (ከበግ ፀጉር፣ከሐርና ቃጫ ተክል)፡፡

➢ **የጫማ፣ቆዳና ቆዳ ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች**
  - የጎማ፣ ፕላስቲክና ሸራ ጫማዎች ማምረቻ ፋብሪካዎች

➢ **የብረታብረትና ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎች**
  - የማሽነሪ፣ የማሽን መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣
  - የብረትና ስቲል ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች እና
  - የአውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪዎች፡፡

➢ **የኬሚካል ኢንዱስትሪዎች**
  - በባዮ ውጤቶች ላይ የተመሠረቱ የፔትሮ ኬሚካል ኢንዱስትሪዎች፣
  - ልዩ ኬሚካሎች (የኮንስትራክሽን ኬሚካሎች፣ ቀለምና የቀለም ውህዶች) ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች እና
  - አልኮል ላይ የተመሠረቱ የኬሚካል ምርቶች (አሴቲክ አሲድ፣ አሲቶን፣ ወዘተ)፡፡

➢ **የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪዎች**
  - የልዩ መድኃኒቶች(speciality medicens)ና በኢንዱስትሪ የተመረቱ አገር በቀል መድኃኒቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣
  - አልሚ ምግቦች ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣
  - የፋርማሲዩቲካል ግብኣቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች እና
  - የኮስሞቲክ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፡፡

➢ **አዳዲስ ኢንዱስትሪዎች**
  - የፓኬጂንግ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣
  - የባዮ ቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪዎች፣
  - የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክስ ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች እና
  - የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሣሪያዎችና ሶፍትዌሮች ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፡፡

## 3. የኢንተርፕራይዝ ልማት

እስከ 2017 ባለው ጊዜ አንዱ የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫ ኢንተርፕራይዝ ልማት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በኢንዱስትሪ

ልማት ውስጥ ባላቸው ከፍተኛ ሚና ምክንያት የላቀ ትኩረት ይሰጣቸዋል፡፡ ለሴቶችና ወጣቶች የሥራ ዕድልን በመፍጠር ድህነትን ለማስወገድ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በመላ አገሪቷ እንዲቋቋሙ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ይደረጋል፡፡ ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው ኢንዱስትሪዎች በየደረጃው የሚኖራቸው የእሴት ጭማሪ ሂደትን (value chain) በመከተል በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እና በመካከለኛና ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች መካከል ትስስር እንዲኖር ይደረጋል፡፡ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች እንዲሸጋገሩ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ኢንተርፕራይዞችን ለማልማትና የኢንተርፕረነር ዝንባሌ በህብረተሰቡ እንዲፈጠር ሰፊ ጥረት ይደረጋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ከበርካታ አገሮችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ስትራቴጂያዊ አጋርነት በመፍጠር የአገር ውስጥ የአመራረት ሥርዓቱ በዓለም ደረጃ ካለው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ እሴት ጭማሪ ሂደት (value chain) ጋር ትስስር እንዲኖረው ማድረግ ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡

## 4. የግልና የመንግስት ኢንቨስትመንት

በአገሪቷ ኢንዱስትሪ ልማት የግሉ ዘርፍ ዋና ተዋናይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ጊዜ የግል ዘርፉ የኢንዱስትሪውን ልማት ለመምራት በሚችልበት የዕድገት ደረጃ ላይ አይገኝም፡፡ በመሆኑም ትላልቅ ኢንቨስትመንት በሚጠይቁና ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ባላቸው ኢንዱስትሪዎች ላይ የመንግሥት ኢንቨስትመንት የሚቀጥል ይሆናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በመንግሥት እጅ የሚገኙትን አንዱስትሪዎች ምርታማነትና ተወዳዳሪነት ለማሳደግ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አመራር አቅም እንዲጎለብት ይደረጋል፡፡ የግሉን ዘርፍ ዕድገት ለመደገፍ መንግሥት ደረጃ በደረጃ ከኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ለመውጣት የሚያደረገው እንቅስቃሴ ግልጽነት ባለው የፕራይቬታይዜሽን ሂደት እንዲደገፍ ይደረጋል፡፡

## 5. የኢንዱስትሪ ዞን ልማት

የኢንዱስትሪ ዞኖችን በማልማት ወደ ኢንዱስትሪ ከተሞች ማሳደግ ቀጣይነት ያለው ሂደት በመሆኑ ረጅም ጊዜና የመንግሥትን ቁርጠኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡ የኢንዱስትሪ ዞኖችን ለማልማት የኢንዱስትሪ ልማት ዕቅድ ማዘጋጀት በራሱ ብቻ በቂ አይሆንም፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን የልማት ዞኖች ተብለው የሚታወቁ የኢንዱስትሪ ከተሞችን ለመገንባት ክልላዊ የንግድ ሥራ ማዕከላት፣ ማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት (ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታሎች፣ መኖሪያ ቤቶች፣ ወ.ዘ.ተ) ግንባታ ዕቅድና የአካባቢ ጥበቃ መስፈርቶችን ያካተተ አጠቃላይ ዕቅድ የሚያስፈልግ ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው በአንድ ወይም በሌላ መልኩ መንግሥት ከኢንዱስትሪ ዞን ልማት ሥራ መውጣት እንደማይችልና ይልቁንም የኢንዱስትሪ ከተሞች ልማት ፕሮግራም አስተዳደርን በበላይነት የሚመራ መሆኑን ነው፡፡

በመሆኑም በዕቅድ ዘመኑ በሁሉም የአገሪቷ ክልሎች የኢንዱስትሪ ከተሞችን ለማልማት መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል፡፡ በኢንዱስትሪ ከተሞች የሚታቀፉት መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች በእሴት ጭምሪ ሂደት (value chain) ትስስር ያላቸው ይሆናሉ፡፡ በኢንዱስትሪ ዞን ልማቱ መጀመሪያ አካባቢ መንግሥት የልማቱ ተዋናዮች የተለያዩ ማበረታቻዎችን እንዲያገኙና አመቺ ሁኔታ እንዲፈጠርላቸው አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን የንግድ ሥራ ማዕከላት ግንባታና ማስፋፊያ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ደረጃ በደረጃ ተግባራዊ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ኢንቨስተሮችንና የበለጠ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የኢንዱስትሪ ዞኖቹ የተሟላ መሠረተ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ ይህም እርምጃ ለከተማ ልማትና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል የኢንዱስትሪ መዋቅራዊ ለውጥ ለማስፈን ወሳኝነት አለው፡፡

## 4.3 ስትራቴጂያዊ ግቦች፣ ዓላማዎች፣ ቁልፍ ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞች

### 4.3.1 የስትራቴጂ ግቦችና ዓላማዎች

የኢንዱስትሪ ልማት ፍኖተ-ካርታው (Road map) እና የስትራቴጂ ዕቅድ ሰነዶች የተዘጋጁበት አጠቃላይ ዓላማ በኢንዱስትሪ ልማት አማካይነት የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት ነው፡፡ በዚሁ መሠረት የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፣

- የኢንዱስትሪው ዘርፍ ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት አሁን ያለውን 13% ድርሻ በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ (2017) ወደ 27% ማሳደግ እና
- የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት አሁን ያለውን 4% ድርሻ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ (2017) ወደ 17% ማሳደግ፡፡

ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ አሁን ያለው የአገሪቷ ኢንዱስትሪ ሁኔታን አስመልክቶ የዳሰሳ ጥናት ተደርጓል፡፡ በተደረገው ጥናት በዘርፉ ያሉት ችግሮችና ምቹ ሁኔታዎች ተለይተው በስምንት የተለያዩ ነገር ግን ተያያዥ በሆኑ ቁልፍ ስትራቴጂ ጉዳዮች ተከፋፍለው እንዲቀርቡ ተደርጓል (ዝርዝሩን ከስትራቴጂ ዕቅድ ሰነዱ ይመልከቱ)፡፡ ከእነዚህ ቁልፍ ስትራቴጂ ጉዳዮች በመነሳት የሚከተሉት አምስት የስትራቴጂ ዓላማዎች ተቀርጸዋል፣

***ስትራቴጂ ዓላማ 1*** - *ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው ነባር ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን የበለጠ ማሳደግና ማስፋፋት*

***ስትራቴጂ ዓላማ 2***- *የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍን ወደ አዳዲስ ዘርፎች ማስፋፋት*

***ስትራቴጂ ዓላማ 3***- *የኢንተርፕራይዝ ልማትና የኢንተርፕሪነር ክህሎት ማሳደግ፣*

***ስትራቴጂ ዓላማ 4***- *በኢንዱስትሪ ልማት የመንግሥት፣ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ባለሀብቶች ኢንቨስትመንትን ማሳደግ እና*

*ስትራቴጂ ዓላማ 5- የኢንዱስትሪ ዞኖችና የኢንዱስትሪ ከተሞችን ማልማትና ማንቀሳቀስ።*

### 4.3.2 ቁልፍ ስትራቴጂዎች

ከላይ የተጠቀሱት ስትራቴጂ ዓላማዎችን ለማሳካት ተገቢውን ስትራቴጂ መምረጥ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም በዚህ ሰነድ የቀረበውን አጠቃላይ የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫን መሠረት በማድረግ የሚከተሉት ስድስት ቁልፍ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂዎች ተቀርጸዋል (ዝርዝሩን ከኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ሰነዱ ይመልከቱ)።

- አመቺ የሆነ የሥራ ከባቢ መኖሩን ማረጋገጥ፣
- ብቃት ያለው የሰው ኃይል ማቅረብ፣
- ጥራታቸው የተጠበቀ የኢንዱስትሪ ግብኣቶችን ማቅረብና እሴት መጨመር፣
- የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶች ገበያን ማስፋፋት (በአገር ውስጥ፣ በአካባቢው የአፍሪካ አገሮችና በዓለም አቀፍ ደረጃ)፣
- የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማጠናከር እና
- ድጋፍ ሰጪ ተቋማትን ማቋቋምና ተቋማዊ ድጋፍ መስጠት።

### 4.3.3 የኢንዱስትሪ ልማት ዋና ዋና ፕሮግራሞች

ለኢንዱስትሪ ልማት ዕቅድ ትግበራ አስፈላጊ የሆኑ ፕሮግራሞች የተመረጡ ሲሆን እነዚህም ፕሮግራሞች የኢንዱስትሪ ልማት የስትራቴጂ ግቦችን ለማሳካት የሚከናወኑ ተግባራትና ፕሮጀክቶችን የሚያንጸባርቁ ናቸው። በዚሁ መሠረት ከላይ የተጠቀሱት አምስቱን የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ዓላማዎች ለማሳካት የሚከተሉት ስድስት ዋና ዋና ፕሮግራሞች ተቀርጸዋል (ዝርዝሩን ከኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ሰነድ መመልከት ይቻላል)።

- ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው ኢንዱስትሪዎች ማስፋፊያ ፕሮግራም፣
- በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የአዳዲስ ኢንዱስትሪዎችና ምርት ዓይነቶች ማስፋፊያ ፕሮግራም፣
- የኢንዱስትሪ ኢንተርፕራይዞችና ኢንተርፕረነር ማስፋፊያ ፕሮግራም፣
- የአገር ውስጥና የውጭ አገር ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ፕሮግራም፣
- የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም እና
- የኢንዱስትሪ ከተማ ልማት ፕሮግራም።

## 4.4 የኢንዱስትሪ ልማት ምዕራፎች (phases)

በ2017 ከታለመው የኢንዱስትሪ ዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ ከላይ የተጠቀሱት አምስቱ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ዓላማዎች በሦስት ምዕራፎች ተለይተው የሚተገበሩ ይሆናሉ። በእነዚህ የኢንዱስትሪ ልማት ምዕራፎች በየደረጃው

የሚደረገው የስትራቴጂ ዓላማ ማሳካት የታሰበውን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ እንደሚያመጣ ይገመታል፡፡

### ምዕራፍ 1- የዋና ዋና ኢንዱስትሪዎች ምርታማነት ማሳደግ (2005-2007)


በዚህ የኢንዱስትሪ ልማት ምዕራፍ ትኩረት የሚደረገው በቀላል ኢንዱስትሪዎች ላይ ሲሆን ይህም ኢንዱስትሪዎቹ የግብርና ዘርፍን ጨምሮ ከሌሎች ዘርፎች ጋር የሚኖራቸው ሰፊ ትስስርን ያጠቃልላል፡፡ በዚሁ መሠረት ከኢንዱስትሪ ዘርፍ ቅድሚያ የተሰጣቸው ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማትና ምርታማነት ዕድገት ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጥ ይሆናል፡፡ በዚህ የልማት ምዕራፍ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጡት የኢንዱስትሪ ልማት ግቦችን ማሳካት ቁልፍ ጉዳይ ይሆናል፡፡ በዚህ የልማት ምዕራፍ ቀላል ኢንዱስትሪዎች ከኢንዱስትሪው ዘርፍ አብዛኛውን ድርሻ እንደያዙ የሚቆዩ ቢሆንም እስከዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ (2017) የሚኖራቸው ድርሻ ቀስ በቀስ እየቀነሰ እንደሚመጣ ይገመታል፡፡

**ሠንጠረዥ 11፡ በዕቅድ ዘመኑ መጀመሪያ ምዕራፍ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ዕድገት ግቦች**

| ዘርፍ | 2005 | 2006 | 2007 |
|---|---|---|---|
| ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የኢንዱስትሪ ዘርፍ ድርሻ በ% | 15.25 | 16.99 | 18.73 |
| ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ድርሻ በ% | 5 | 6 | 7 |
| • የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ድርሻ በ% | 2.8 | 3.1 | 3.8 |
| • የኬሚካልና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ድርሻ በ% | 1.3 | 1.5 | 1.6 |
| • የስኳር፣ጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ ድርሻ በ% | 0.2 | 0.4 | 0.45 |
| • የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ድርሻ በ% | 0.3 | 0.4 | 0.45 |
| • የብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ድርሻ በ% | 0.4 | 0.6 | 0.7 |

**ምንጭ፡በጥናቱ የተገመተ ግብ**

በቀሪው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው የዋና ዋና ኢንዱስትሪዎች ዕድገት አዝማሚያና ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የሚኖራቸው ድርሻ ቀጥሎ ባለው ቻርት 6 ቀርቧል፡፡




ቻርት 6፡ በቀሪው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው ኢንዱስትሪዎች ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የሚኖራቸው ድርሻ

**ምዕራፍ 2- ቁልፍ የሆኑ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋምና ማስፋፋት (2008-2012)**

በዚህ የልማት ምዕራፍ ፈጣን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዕድገት ለማምጣትና በ2017 መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ የላቀ እንቅስቃሴ ይደረጋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ አዳዲስና ቁልፍ የሆኑ ከባድ የብረታብረትና ኬሚካል ኢንዱስትሪዎች ግንባታ ላይ ትኩረት የሚደረግ ሲሆን ቀላል ኢንዱስትሪዎችን ጨምሮ ከሌሎች ዘርፎች ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ ይደረጋል፡፡ ከባድ የብረታብረት፣ ኬሚካልና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪዎችን ከመገንባት ጎን ለጎን በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው ለዋና ዋና ኢንዱስትሪዎች ልማት ተገቢው ትኩረት ይሰጣል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከ2017 በኋላ ለሚኖረው የኢንዱስትሪ መዋቅራዊ ለውጥ መሠረት ለመጣል እውቀት ተኮርና የናኖ ቴክኖሎጂ (Nano-technology) የሚጠቀሙ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችን ለመገንባት የሚያስችል የአቅም ግንባታ ሥራ በስፋት ይከናወናል፡፡ እንደመጀመሪያው የልማት ምዕራፍ ሁሉ በዚህ ምዕራፍም ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ቀላል ኢንዱስትሪዎች ከፍተኛ ድርሻ


የሚኖራቸው ሲሆን በዚህ ምዕራፍ በርካታ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎች ስለሚገነቡ የከባድ ብረታብረትና ኬሚካል ኢንዱስትሪዎች ድርሻ እስከ ዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ድረስ ቀስ በቀስ እያደገ የሚሄድ ይሆናል፡፡

**ሠንጠረዥ 12፡ ነባር የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ከዘርፉ የሚኖራቸው ድርሻ በ%**

| | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
|---|---|---|---|---|---|
| ከኢንዱስትሪ ዘርፍ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ድርሻ በ% | 8% | 9 % | 10% | 11 % | 12% |
| የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ድርሻ በ% | 4 | 4.5 | 4.8 | 5 | 5.5 |
| የኬሚካልና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪዎች ድርሻ በ% | 1.3 | 1.45 | 1.6 | 1.65 | 1.8 |
| • ኬሚካልና ተዛማጅ ኢንዱስትሪዎች | 1.03 | 1.16 | 1.28 | 1.32 | 1.44 |
| • ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ | 0.27 | 0.29 | 0.32 | 0.33 | 0.36 |
| የጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ ድርሻ ድርሻ በ% | 0.55 | 0.65 | 0.76 | 0.8 | 0.9 |
| የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ድርሻ በ% | 0.55 | 0.65 | 0.75 | 0.8 | 0.9 |
| የብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ድርሻ በ% | 1.2 | 1.3 | 1.4 | 1.63 | 1.75 |
| የኢንፎርሜሽን፣ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂና የኤሌክትሮኒክስ ኢንዱስትሪ ድርሻ በ% | 0.16 | 0.18 | 0.3 | 0.4 | 0.43 |
| የፔቲሮ ኬሚካል ኢንዱስትሪ ድርሻ በ% | 0.16 | 0.18 | 0.29 | 0.36 | 0.36 |
| የባዮ ቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪ ድርሻ በ% | 0.08 | 0.09 | 0.1 | 0.36 | 0.36 |

**ምንጭ፡ በጥናቱ የተገመተ ግብ**

ቀጥሎ ካለው ቻርት 7 መረዳት እንደሚቻለው ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው ነባር ኢንዱስትሪዎች ጠቃሚ ሆነው እንደሚቀጥሉና በዚህ በሁለተኛው የኢንዱስትሪ ልማት ምዕራፍም ቢሆን የበለጠ ዕድገት ማሳየታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ እንደሆነ ነው፡፡




ቻርት 7፡ በሁለተኛው የኢንዱስትሪ ልማት ምዕራፍ ነባር የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ዕድገት

በዚህ የኢንዱስትሪ ልማት ምዕራፍ ቅድሚያ ትኩረት በተሰጣቸው ነባር ኢንዱስትሪዎች አዳዲስ የምርት ዓይነቶችን ለማምረት የታቀደ ሲሆን ይህም የነባር ኢንዱስትሪዎች ማስፋፊያ አካል ይሆናል ማለት ነው፡፡፡ ሠንጠረዥ 12 እና ቻርት 8 በነባር ኢንዱስትሪዎች ማስፋፊያ አማካይነት የሚመጡ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችና የምርት ዓይነቶች ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚኖራቸው ድርሻ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

**ምዕራፍ 3፡- ከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙኢንዱስትሪዎችን መገንባት (2013-2017)**


በመጨረሻ የዕቅዱ ምዕራፍ ከ2013 እስከ 2017 ያለው ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ትኩረት የሚደረገው ከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎችን መገንባትና አቅም በማሳደግ ያሉት ቀላል ኢንዱስትሪዎችን ጨምሮ ከሌሎች ዘርፎች ጋር ጠንካራ ትስስር ያላቸው ከባድ የብረታብረትና ኬሚካል ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋት ላይ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ከባድ የብረታብረትና ኬሚካል ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም ከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚኖራቸው ድርሻ ቀስ በቀስ እያደገ መጥቶ

በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ የመካከለኛና ከፍተኛ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ኢንዱስትሪዎች ድርሻ ከ50% በላይ እንደሚሆንና ኢንዱስትሪው ከፍተኛ መዋቅራዊ ለውጥ እንደሚያሳይ ይጠበቃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ዕውቀት ተኮርና የናኖ ቴክኖሎጂ (Nano-technology) ተጠቃሚ ኢንዱስትሪዎችን ለመገንባት ያሉት አማራጮችን ለመጠቀም ዝግጅት የሚደረግ ሲሆን የእነዚህ ኢንዱስትሪዎች ልማት ደግሞ ከ2017 ቀጥሎ የሚከናወን ይሆናል፡፡

**ሠንጠረዥ 13፡ ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው ነባር የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በሦስተኛው የልማት ምዕራፍ ከዘርፉ የሚኖራቸው ድርሻ ግብ**

| ዘርፍ | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
|---|---|---|---|---|---|
| ማኑፋክቸሪንግ | 13 % | 14% | 15% | 16% | 17% |
| አግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ | 5.8 | 6 | 6.1 | 6.2 | 6.3 |
| የኬሚካልና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪዎች | 2 | 2.1 | 2.25 | 2.4 | 2.55 |
| • ኬሚካልና ተዛማጅ ኢንዱስትሪዎች | 1.8 | 1.89 | 2.025 | 2.16 | 2.295 |
| • የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪዎች | 0.2 | 0.21 | 0.225 | 0.24 | 0.255 |
| የስኳር፣ጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ | 1 | 1.1 | 1.2 | 1.3 | 1.4 |
| የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ | 1 | 1.1 | 1.2 | 1.3 | 1.4 |
| ብረታብረትና የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች | 1.9 | 2.1 | 2.2 | 2.4 | 2.55 |
| የኢንፎርሜሽን፣ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂና የኤሌክትሮኒክስ ኢንዱስትሪ | 0.52 | 0.55 | 0.7 | 0.9 | 1.05 |
| የፔትሮ ኬሚካል ኢንዱስትሪ | 0.39 | 0.5 | 0.65 | 0.75 | 0.9 |
| የባዮ ቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪ | 0.39 | 0.55 | 0.7 | 0.75 | 0.85 |


**ምንጭ፡ በጥናቱ የተገመተ ግብ**




ቻርት 8፡ በሦስተኛው የልማት ምዕራፍ የነባር ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ዕድገት

**የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ መዋቅራዊ ለውጥ**

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ዘርፍ መዋቅራዊ ለውጥ ዕቅድ በየልማት ምዕራፉ ለተመረጡ ኢንዱስትሪዎች ቅድሚያ ትኩረት በመስጠት የሚተገበር ይሆናል፡፡ በዚሁ መሠረት በመጀመሪያ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸው ኢንዱስትሪዎች ተለይተው እንዲታወቁ ይደረጋል፡፡ በቀጣይ የልማት ምዕራፍ እነዚህን ኢንዱስትሪዎች ለማልማት ያሉት አማራጮችና አስፈላጊ የሆኑ የመሠረተ ልማቶችና ማህባራዊ ተቋማት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡ በመጨረሻም በቀጣይ የልማት ምዕራፍ ያሉት የኢንዱስትሪ ልማት አማራጮች ለመጠቀም የሚያስችል የአቅም ግንባታ ሥራ ይከናወናል፡፡ ቀጥሎ ያለው ቻርት የኢንዱስትሪው መዋቅራዊ ለውጥ ሂደቱን የሚያሳይ ነው፡፡



ቻርት 9፡ የኢንዱስትሪ መዋቅራዊ ለውጥ ሂደት

### 4.5 በልማት ምዕራፎቹ መጨረሻ የሚኖሩ ዋና ዋና ግቦች

በእያንዳንዱ ልማት ምዕራፍ መጨረሻ ሊደረስባቸው የተቃዱ ግቦች ቁልፍ ከሆኑ የዕድገት አመልካቾች (growth indicators) አንጻር በማጠቃለል ቀጥሎ ባሉት ሠንጠረዦች ቀርቧል፡፡ ከሠንጠረዦቹ መረዳት እንደሚቻለው የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በ2007 ዓ/ም 4.2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ጠቅላላ ዋጋ ያላቸው ምርቶች እንደሚያመርት፣ ይህም በ2012 ዓ/ም ወደ 13.3 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚያድግና በ2017 ዓ/ም ደግሞ 35.2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የውጭ ምንዛሪን በማስገኘት በኩል በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረው ሚና በተመሳሳይ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ እንደሚሄድ ይጠበቃል፡፡ በዚሁ መሠረት በ2007 ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ 2,618 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሪ እንደሚገኝ ግብ ተጥሏል፡፡ ይህም በሦስት እጥፍ አድጎ በሁለተኛው የልማት ዕቅዱ ምዕራፍ ወደ 2,264.2 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚያድግና በልማት ዕቅዱ ሦስተኛው ምዕራፍ(2017) ላይ በስምንት እጥፍ በማደግ 16,228.6 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚደርስ ይጠበቃል፡፡

አገሪቷ አዳዲስ የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር ለሚታደርገው ጥረት ዘርፉ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡ በ2005 ዓ/ም በዘርፉ የተፈጠሩት አዳዲስ ሥራዎች 204 ሺህ ነበሩ፡፡ ይህም በ2007 ዓ/ም መጨረሻ ላይ ወደ 236 ሺህ እንደሚያድግ፣ በ2012 ወደ 377 ሺህ ከፍ እንደሚልና በ2017 ዓ/ም ደግሞ 780 ሺህ እንደሚደርስ ይገመታል፡፡ ይህም በ2007 ከነበረው መጠን ጋር ሲነጻጸር የ330% ዕድገት የሚያሳይ ነው፡፡ በዕቅድ ዘመኑ ኢንተርፕራይዞች እንዲያብቡ የሚደረግ ሲሆን በተለይም ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ደረጃ በደረጃ ወደ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲሸጋገሩ ይደረጋል፡፡ በዚሁ መሠረት በ2007 ዓ/ም የ25,000 ኢንተርፕራይዞች፣ በ2012 ዓ/ም የ40,000 ኢንተርፕራይዞች በ2017 ዓ/ም ደግሞ 65,000 ኢንተርፕራይዞች ልማት ይካሄዳል፡፡

በዕቅድ ዘመኑ የሚኖረው ዋና ዋና የኢንዱስትሪ ልማት ግቦች ማጠቃለያ በሠንጠረዥ 14 የቀረበ ሲሆን ዝርዝሩ በኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ዕቅድ (2005-2017) ሰነድ ተመልክቷል፡፡

**ሠንጠረዥ 14፡ በእያንዳንዱ የልማት ዕቅድ ምዕራፍ የሚጠበቁ ዋና ዋና የግብ ስኬቶች**

| ተ.ቁ | የዕድገት አመልካቾች | መነሻ ዓመት | በልማት ዕቅዱ ምዕራፍ መጨረሻ የሚጠበቀው የግብ ስኬት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 2004 | 2007 | 2012 | **2017** |
| 1 | የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ጠቅላላ ምርት መጠን በሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር | | 4190 | 132816 | 351376 |
| 1.1. | የብረታብረት እሴት ጭማሪ መጠን በሚሊዮን ብር | 26 | 101.4 | 376.4911 | 1397.885 |
| 1.2 | የእሴት ጭማሪ የዕድገት ምጣኔ (የ30% ዝቅተኛ የዕድገት ምጣኔ እንደሚቀጥልና ታሪካዊ መረጃን በመጠቀም የተገመተ) | 0.3 | 1 | 0.3 | 0.3 |
| 1.3. | የብረታብረት ነፍስ ወከፍ ፍጆታ በኪ.ግ | 17.78 | 34.72 | 81.41 | 190.91 |
| 2 | የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ጠቅላላ ምርት ዋጋ በሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር | 1074 | 2545 | 3043 | 3853.5 |
| 3 | የውጭ ምንዛሪ ገቢ በሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር | 255.4 | 2618 | 7264.161 | 16228.6 |
| 3.1. | የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች | 51.75 | 300 | 832 | **1859.7** |
| 3.2. | ኬሚካል ኢንዱስትሪዎች | 7.01 | 20 | 55.5 | **123.9** |
| 3.3. | የቆዳ ኢንዱስትሪዎች | 112.06 | 496.9 | 1378.7 | **3080.2** |
| 3.4. | የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪዎች | 84.63 | 1000 | 2773.63 | **6196.5** |
| 3.5 | ብረታብረትን ጨምሮ ሌሎች አዳዲስ ኢንዱስትሪዎች | | 802 | 2225.5 | **4971.8** |
| 4 | የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የዕድገት ምጣኔ በ% | 4.5 | 30 | 20 | **15.7** |
| 5 | የሥራ ዕድል ፈጠራ ዕድገት ምጣኔ በ% | | 5.36 | 12 | 18.29 |
| 5.1. | በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ በየዓመቱ የተፈጠሩ አዳዲስ ሥራዎች መጠን በሺህ | 204 | 236 | 377 | 780 |
| 6 | የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች አቅም አጠቃቀም በ% | 61.2 | 78 | 82 | 87 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 7 | በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት መጠን በቢሊዮን ብር | 32 | 97 | 587.322 | 3556.156 |
| 8 | የተገነቡ የኢንዱስትሪ ዞኖች ብዛት | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 9 | የኢንተርፕራይዝ ልማት | | | | |
| 9.1 | በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የተፈጠሩ አዳዲስ ሥራዎች በሺ.ህ | 554 | 740 | 1199 | 1943 |
| 9.2 | የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ዕድገት መጠንበ%(ከ2005-2007 የ15% አማካይ የዕድገት ምጣኔ መሠረት በማድረግ) | | 10.13 | 10.13 | 10.13 |
| 9.3 | የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ብዛት በሺ.ህ (እያንዳንዱ ኢንተርፕራይዝ በአማካይ 30 ሠራተኞች እንደሚኖረው ታሳቢ ተደርጓል) | 18 | 25 | 40 | 65 |

## ሠንጠረዥ 15፡ ነባርና አዳዲስ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትዎች የሚኖራቸው የዕድገትና መዋቅራዊ ለውጥ ሁኔታ ማጠቃለያ

| የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ዓይነት | የኢንዱስትሪ ልማት ዕቅድ ዘመን (2005-2017 ) | | | ቁልፍ አብቂዎች |
|---|---|---|---|---|
| | የኢንዱስትሪ ልማት ምዕራፍ 1<br>2005 — 2007[1] | የኢንዱስትሪ ልማት ምዕራፍ 2<br>2008 — 2012[2] | የኢንዱስትሪ ልማት ምዕራፍ 3<br>2013 — 2017 | |
| አግሮ ፕሮሰሲንግ | • የአግሮ ኢንዱስትሪዎችን ምርታማነት ማሳደግ፣<br>• የምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎችን ማስፋፋት፣<br>• ከውጭ የሚገቡ የምግብ ዘይቶችን ለመተካት የዘይት ማጣሪያ ፋብሪካዎችን ማቋቋም | • የቅመማቅመም ማምረቻ፣<br>• የታሸጉ ምግቦችና የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ<br>• እንጨት ተኮር የማኑፋክቸሪንግ<br>• አጥንት የወጣለትና በልዩ ሁኔታ ተቆርጦ የተዘጋጀ የከብትና ፍያል ሥጋ | • እውቀትና ካፒታል ተኮር የሆኑ አግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች፣<br>• ለኤክስፖ`ርት የሚሆን የባዮና የተፈጥሮ ምግብና መጠጥ ማምረቻ ፋብሪካዎች፣<br>• የዓሣ ሀብት ልማት<br>• በዚህ የልማት ምዕራፍ የተሠሩት የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች መሠረት የበለጠ ማጠናከር | • ማህበራዊ መሠረተ ልማቶች<br>• አመቺ የቢዝነስ ከባቢና ለኢንተርፕራይዞች የተዘጋጀ ማበረታቻ<br>• የሰው ሀብት ልማት<br>• የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ<br>• የሪሶርስ አቅርቦት |
| የኬሚካልና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪዎች | • የተፈጥሮ ያልሆኑ (Inorganic) መሠረታዊ ኬሚካል ውጤቶች (ማዳበሪያ፣ኮስቲክ ሶዳ ናሶዳ አሽ) ኢንዱስትሪዎች፣<br>• የፋርማሲዩቲካል ኢነዱስትሪዎች፣<br>• የፕሽሲና ፖ`ሊቲሊን ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች | • መሠረታዊ የኬሚካል ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች (ማዳበሪያ፣የተፈጥሮና ሰው-ሠራሽ ኬሚካሎች),<br>• የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪዎች<br>• የአግሮ ኬሚካል ኢንዱስትሪዎች ,<br>• ባዮ ተኮር ኬሚካል ኢንዱስትሪዎች<br>• የላስቲክና ሽራ ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች | • የባዮ ተኮር ኬሚካል ኢንዱስትሪዎች መሠረት ማጠናከር<br>• ልዩ የኬሚካል ኢንዱስትሪዎች(Specialty chemicals)<br>• የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪዎች | |
| የጫማ፣የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች | • የቆዳ ውጤት ምርት ዓይነቶች ማስፋፋት፣<br>• የጫማ ኢንዱስትሪ ከተሞች ልማት፣<br>• የተጠናቃቁ ቆዳዎች ማምረቻ ቴክኖሎጂን ማሻሻል፣<br>• የጥሬ ቆዳና ሌጦ ዓይነቶች ማበራከት፣ የግመል፣ የሳጎን፣ የአዞ፣ የአሳማ ወ.ዘ.ተ ቆዳዎችን | • የምርምርና ሥርፀት አቅም ማሳደግ፣<br>• በገበያ ውድድር አሸናፍ ሆነው በወጡ ምርቶች ላይ ማተኮር፣ ;<br>• ልዩ የዲዛይን ስቱድዮችና የምርት ማበልፀጊያ ማዕከላትን ማቋቋም፣<br>• የሽራ፣ የላስቲክና የጨርቅ | • ከሽራ የሚሠሩ የስፖ`ርትና መደበኛ ጫማዎች ምርት በማሻሻልና ማስፋፋት ለኤክስፖ`ርት የሚያቀርቡ ኢንዱስትሪዎች፣<br>• የላስቲክና ጨርቅ ጫማ ኢንዱስትሪዎች፣<br>• በገበያ ውድድር አሸናፍ ሆነው የወጡ ምርቶችን የበለጠ ማሻሻልና ማስፋፋት<br>• | • ማህበራዊ መሠረተ ልማቶች |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | መጠቀም | ጫማዎችን በማካተት የጫማ ምርት ዓይነቶችን ማስፋፋት<br>• | | • አመቺ የቢዝነስ ከባቢና ለኢንተርፕራይዞች የተዘጋጀ ማበረታቻ<br>• የሰው ሀብት ልማት<br>• የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ<br>• የሪሶርስ አቅርቦት |
| **የብረታብረት ዘርፍ- የብረትና ስቲል ኢንዱስትሪ** | • የብረትና ስቲል ኢንዱስትሪዎች የምርት ስብጥር ማሻሻል | • የብረት ማቅለጫና ሌሎች ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም፣<br>• የብረትና ስቲል ማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን የበለጠ ማስፋፋት | • የድንጋይ ከሰል የሚጠቀሙ የኢንዱስትሪዎችን ማልማት፣<br>• የብረት ኢንዱስትሪዎች ልማት ማጠናከር፣<br>• ያልጠራ ስቲል (crude steel) ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣<br>• የጠራ ስትል (finished steel ) ኢንዱስትሪዎች | |
| **የብረታብረት ዘርፍ- ብረት ብረት ያልሆኑ የማዕድን ውጤቶቸ** | • የኢንዱስትሪ ግብአቱ (መዳብ፣ኒኬል) በሚገኝባቸው አካባቢ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም | • ብረታብረት ያልሆኑ የማዕድን ውጤቶች እሴትና የምርት ስብጥር ማሻሻል | • ብረታብረት ያልሆኑ የማዕድን ውጤቶች እሴትና የምርት ሰብጥር የበለጠ በማሻሻል ማስፋፋት | |
| **የሜታል ኢንጂኔሪንግ ዘርፍ-የትራንስፖርት መሣሪያዎች ማምረቻ ኢንዱስትሪ** | • የሞተር ተሽከርካሪ መለዋዋጫ፣ አካልና ተሳቢዎች ማምረቻ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎች ማቋቋም | • የሞተር ተሽከርካሪ መለዋዋጫ፣ አካል፣ ተሳቢዎችና አጠቃላይ የአውቶሞቲብ ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም ማሻሻልና ማጠናከር | • የተለየ ገበያ ባለቸው ልዩ የአውቶሞቲብ ኢንዱስትሪዎች ላይ ልዩ ክህሎትን ማዳበር(specialization) | |
| **የሜታል ኢንጂነሪንግ ዘርፍ-የማሽነሪዎችና መሣሪያዎች ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች** | • የግብርና መሣሪያዎች ማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት፣<br>• የእጅ መሣሪያዎች/መለዋዋጫዎች/አካላት ማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም | • የግብርና መሣሪያዎች ማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት፣<br>• የእጅ መሣሪያዎች/መለዋዋጫዎች/አካላት ማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም<br>• መደበኛ ማሽነሪዎችና መሣሪያዎች ማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም፣<br>• የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም | • የጨርቃጨርቅ፣ የአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ የቆዳና የኬሚካል ኢንዱስትሪዎች ማሽነሪና መሣሪያዎች ማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም፣<br>• የኢንዱስትሪ ካፒታል ዕቃዎች የማምረት አቅምን ማሳደግ፣ | • **ማህበራዊ መሠረተ ልማቶች**<br>• **አመቺ የቢዝነስ ከባቢና ለኢንተርፕራይዞች የተዘጋጀ ማበረታቻ**<br>• **የሰው ሀብት ልማት**<br>• የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ<br>• የሪሶርስ አቅርቦት |
| **ጨርቃጨርቅና** | • የጥጥ አቅርቦት ሂደትን (supply | • ሰው-ሠራሽ ቃጫ (ናይለን) | • ከሰው ሠራሽ ቃጫ የተሠሩ ጨርቆችና | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **አልባሳት** | chain) ማሻሻል፣<br>• የታቀደውን የኤክስፖርት ግብ ለማሳካት የጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪዎች ምርታማነት ማሻሻል፣<br>• በጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪዎች የአዳዲስ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም አቅም መገንባት | ማምረት<br>• ከሰው ሠራሽ ቃጫ የተሠሩ ጨርቆችና አልባሳት ማምረት፣;<br>• ሰው-ሠራሽ ቃጫ ለማምረት የሚያስፈልገው ቴክኒካዊ አቅም መገንባት | አልባሳትን ኤክስፖርት ማድረግ፣<br>• ከሰው ሠራሽ ቃጫ የሚሠሩ ጨርቆችን ማምረት<br>• ከሰው ሠራሽ ቃጫ የሚሠሩ የጨርቅ ምርት ስብጥርን ማብዛት | |
| **የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂና ኤሌክትሮኒክስ ኢንዱስትሪዎች y** | • በሶፍትዌርና ሃርድዌር ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሰው ሀብት ልማት፣<br>• ከዓለም አቀፍ ደረጃ አምራቾች ጋር ትስስር መፍጠር | • የሰው ሀብት ልማት፣<br>• ጠንካራ የምርምርናሥርፀት ፋሲሊቲዎችን መገንባት፣<br>• ለግል ተጠቃሚዎች የሚሆኑ የኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎችና ማሽኖች ማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን ማቋቋም | • የተራቀቁ የኤሌክቶሮኒክስ መሣሪያዎችና ማሽኖች ለማምረት የሚያስችል አቅም ማሳደግ | |
| **የፔትሮኬሚካል ኢንዱስትሪዎች** | • የማዕድን፣ የግብርናና የድንጋይ ከሰል ሪሶርስ መሠረት ማስፋት | • የሰው ሀብት ልማት<br>• ጠንካራ የምርምርናሥርፀት ፋሲሊቲዎችን መገንባት፣<br>• ከፍተኛ ክህሎት መገንባት<br>• የሪሶርስ መሰረት ማስፋት | • የፔትሮኬሚካል ኢንዱስትሪዎችና ምርቶች | |
| **የባዮ ቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪ** | • የምርምርናሥርፀት አቅም መገንባት፣ | • አገሪቷ ተወዳዳሪ በሆነችባቸው የተመረጡ ዘርፎች የምርምርናሥርፀት አቅም መገንባት፣ | • ባዮ ቴክኖሎጂ ተኮር ምርቶች (የአግሮ፣ የፋርማሲና የባዮ ኢንዱስትሪ) | |

*[1]በመዋቅራዊ ለውጡ ምክንያት በሚኖረው ከፍተኛ ምርታማነት 2007 መጨረሻ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ከፍተኛ የዕድገት መጠን የሚመዘገብበት ዘመን ይሆናል፡፡*

*[2]በ2012 በርካታ መሠረት ልማት ፕሮጀክቶች (የትራንስፖርት፣የኃይል፣የውሃ ወ.ዘ.ተ) ስለሚጠናቀቁ ለሁለተኛ ጊዜ ከፍተኛ የዕድገት መጠን የሚመዘገብበት ዘመን ይሆናል፡፡*

## 5. ክፍል አምስት- የኢንዱስትሪ ልማት ፍኖተ-ካርታው (Road map) እና የስትራቴጂ ዕቅዱ ትስስር

የቀጣይ 13 *ዓመታት* የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ የተዘጋጀው በዚህ ሰነድ የቀረበው የኢንዱስትሪ ልማት ፍኖታ-ካርታን (Road map) *መሠረት* በማድረግ ነው፡፡ የስትራቴጂ ዕቅድ ሰነዱ በ2017 *መካከለኛ* ገቢ ካላቸው አገሮች የዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ የተያዘውን ራዕይ እውን ለማድረግ የሚያስፈልጉ ስትራቴጂዎች፣ፕሮግራሞችና የሚከናወኑ ተግባራትን በዝርዝር የሚያቀርብ ነው፡፡ በዚህ የኢንዱስትሪ ልማት ፍኖተ-ካርታ (Road map) *መሠረት* የኢንዱስትሪ *መዋቅራዊ* ለውጥ ሂደቱን የሚደግፍ ተቋማዊ አደረጃጀት *"የኢንዱስትሪ ልማት ተቋማዊ" አደረጃጀት* በተሰኘው ሰነድ ተለይቶ ቀርቧል፡፡

በመሆኑም የዚህ የኢንዱስትሪ ልማት ፍኖተ-ካርታ (Road map) የተሟላ እይታ *ማግኘት* የሚቻለው ከሁለቱ ሰነዶች ማለትም *ከኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂውና ከኢንዱስትሪ ልማት ተቋማዊ አደረጃጀት ሰነዶች ጋር አብሮ በማየት ይሆናል፡፡*

# አባሪዎች

## አባሪ 1፡ የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ታሪካዊ አመጣጥ

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ በኢትዮጵያ መታየት የጀመረው ከሰሃራ በረሃ በታች ካሉት አገሮች ቀደም ብሎ እ.ኤ.አ በ1950ዎቹ ነበር፡፡ ዘመናዊ ኢንዱስትሪዎች ብቅ ብቅ ማለት የጀመሩት እ.ኤ.አ በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ ሲሆን በወቅቱ የነበረው ዓላማ ገቢ ምርቶችን መተካት ነበር፡፡ እ.ኤ.አ በ1970ዎቹ መጀመሪያ ላይ መንግሥት በማዕካላዊ ዕቅድ ላይ የተመሠረተ የኢኮኖሚ ሥርዓት ሥራ ላይ እንዲውል አደረገ፡፡ ይህም እርምጃ በመጀመሪያ አካባቢ ይነስም ይብዛ ተነሳሽነት የነበራቸው የግል ባለሀብቶችን ተስፋ ያስቆረጠ ነበር፡፡ በዚህን ጊዜ መንግሥት ሁሉንም የኢንዱስትሪ ተቋማት በመውረስና በኢኮኖሚው ውስጥ የወሳኝነት ሚና መጫዋት ጀመረ፡፡ መንግሥት ሆን ብሎ የግሉን ዘርፍ ዕድገት የሚገታ ፖሊሲ በማውጣት ሥራ ላይ እንዲውል አደረገ፡፡

ከ1950 ቀደም ብሎ በነበረው የአገሪቷ ተከታታይ የአምስት ዓመት የልማት ዕቅድ ወቅት እንደ ልብስ፣ የሴራሚክ ውጤቶች፣ የማሽን መሣሪያዎችና የቆዳ ውጤቶች የመሳሰሉ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶች ፍላጎት የሚያሟሉት የዕደ ጥበባትና የጎጆ ኢንዱስትሪዎች ነበሩ፡፡ የመጀመሪያው የአምስት ዓመት የልማት ዕቅድ (1950-1954) አንዱ ዓላማ ጠንካራ መሠረተ ልማት በተለይም የትራንስፖርት፣የኮንስትራክሽንና የኮሙኒኬሽን አውታሮች በመገንባት ተራርቀው የሚገኙትን ክልሎች ማገናኘት ነበር፡፡ አገሪቷን ከገቢ ምርቶች ጥገኝነት ለማላቀቅ በፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ለመሥራት በቂ ክህሎት ያለው የሰው ኃይል ማፍራት ደግሞ የዕቅዱ ሌላው ግብ ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሰፋፊ የእርሻ ፕሮጀክቶችን በማስፋፋት የግብርናውን ዕድገት ማፋጠን የመጀመሪያው አምስት ዓመት ዕቅድ ሌላው ዓላማ ነበር፡፡

ሁለተኛው የአምስት ዓመት ዕቅድ (1955-1960) የአገሪቷን ኢኮኖሚ ከግብርና ወደ አግሮ ኢንዱስትሪ ለመለወጥ የታቀደ የ20 ዓመት የልማት ፕሮግራም የተጀመረበት ጊዜ ነበር፡፡ የዕቅዱ ዓላማዎች የምርት ዓይነቶችን ማበራከት፣ ዘመናዊ የፕሮሰሲንግ ዘዴዎችን ሥራ ላይ ማዋል፣የማምረት አቅም ማሳደግና የአገሪቷን ኢኮኖሚ ዕድገት መጠን ከፍ ማድረግ ያካተተ ነበር፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የሦስተኛው የአምስት ዓመት ዕቅድ (1961-1966) የማኑፋክቸሪንግና የአግሮ ኢንዱስትሪዎች አፈጻጸምን በማሻሻል የአገሪቷን ኢኮኖሚ ዕድገት ማፈጠን ነበር፡፡ የሦስተኛው የአምስት ዓመት ዕቅድ ከቀደሙት ዓመታት ዕቅዶች በተለየ መልኩ መንግሥት ትምህርትን ለማስፋፋትና የአርሶ አደሩን ኑሮ ለማሻሻል ፍላጎት ያሳየበት ነበር፡፣

ለመጀመሪያው አምስት ዓመት ዕቅድ ማስፈጸሚያ የዋለው ጠቅላላ ኢንቨስትመንት ወጪ ብር 839.6 ሚሊዮን ሲሆን ይህም ከታቀደው ብር 674 ሚሊዮን በ25% በልጦ ይታያል፡፡ የሁለተኛው አምስት ዓመት ኢንቨስትመንት ወጪ መጠን

ከታቀደው ብር 1,694 ሚሊዮን በ13% ይበልጣል፡፡ ለሦስተኛው አምስት ዓመት ዕቅድ ማስፈጸሚያ የተመደበው በጀት ብር 3,115 ሚሊዮን ነበር፡፡

ከ1943-1953 ባሉት ጊዜያት የንጉሡ መንግሥት ህግ በማውጣት የውጭ አገር ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የሚረዳ ፖሊሲ ቀርጾ ሥራ ላይ አውሎ ነበር፡፡ አዲሱ ፖሊሲ የውጭ አገር ኢንቨስተሮች ከቀረጥ ነጻ መብት፣ የውጭ ምንዛሪን ወደ አገራቸው መውሰድ፣ ከቀረጥ ነጻ ምርቶችን ማስገባትና ወደ ውጪ መላክ፣ ያለ ታክስ ክፍያ የትርፍ ድርሻን መውሰድ፣ ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮርፖሬሽንና ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ የፋይናንስ አገልግሎት ማግኘት የመሳሰሉትን ማበረታቻዎች የሚሰጥ ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከውጭ በሚገቡ ተመሳሳይ ምርቶች ላይ ከፍተኛ ታሪፍ በመጣልና በአገር ውስጥ ምርቶች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ገቢ ምርቶችን በማገድ መንግሥት የኢንዱስትሪ ድርጅቶች ከለላ እንዲያገኙ አድረጓል፡፡ በዚሁ መሠረት ከለላ የተደረገላቸው የኢንዱስትሪ ምርቶች ስኳር፣ ጨርቃጨርቅ፣ የቤትና የቢሮ ቁሳቁሶችና ብረታብረት ነበሩ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት በሚጠይቁ እንደ ነዳጅ ማጣሪያ፣ የወረቀትና ፐልፕ ኢንዱስትሪ፣ የጎማና የሲሚንቶ ኢንዱስትሪ በመሳሳሉት መስኮች መንግሥት በራሱ ኢንቨስትመንት በመመደብ ተሳተፏል፡፡ በ1956 የሁለተኛው አምስት ዓመት ዕቅድ በሂደት ላይ እያለ መንግሥት አዋጅ ቁጥር 51 አወጣ፡፡ የአዋጁ ዓላማ ቀደም ሲል የነበሩትን የኢንቨስትመንት ፖሊሲዎችን የበለጠ ለማጠናከር፣ ለውጭ አገር ባለሀብቶች ብቻ ይሰጥ ከነበረው የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የአገር ውስጥ ባለሀብቶችም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግና የኢንቨስትመንት ፕሮግራሙን የሚከታተል የኢንቨስትመንት ኮሚቴ ለማቋቋም ነበር፡፡ የኢንቨስትመንት ኮሚቴውን ወደ አማካሪ ካውንስል ደረጃ በማሳደግ የኢንቨስትመንት ውሳኔዎችን የማስተላለፍ ሥልጣን ለካውንስሉ የሰጠው አዋጅ ቁጥር 242 እንዲወጣ ተደረገ፡፡ በዚሁ መሠረት እ.ኤ.አ በ1970ዎቹ መጀመሪያ ላይ የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ የተለያዩ የበጀት ማበረታቻዎች፣ መንግሥት በራሱና ከግል ባለሀብቶች ጋር በመሆን የሚያደርገው ኢንቨስትመንቶችን ያካተተ ነበር፡፡

ይህም የመንግሥት ፖሊሲ በኢንዱስትሪው ዘርፍ በርካታ የውጭ አገር ኢንቨስትመንቶች ለመሳብ አስችሏል፡፡ ለምሳሌ ያህል በ1964 ከጠቅላላው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የተከፈለ ካፒታል ውስጥ የውጭ አገር ካፒታል 41% ነበር፡፡ ብዙዎቹ የውጭ አገር ድርጅቶች ሲሰሩ የነበረው ኃላፊነቱ በተወሰነ የግል ማህበር መልክ ሲሆን አብዛኞቹ የዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ቅርንጫፍ ወይም አካል ነበሩ፡፡ የኔዘርላንድ ባለሀብቶች በስኳር ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ዋናውን ድርሻ (ወደ 80% የሚጠጋ) የያዙ ሲሆን የጣሊያንና የጃፖን ባለሀብቶች በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ መስክ ተሳትፈዋል፡፡ የግሪክ ባለሀብቶች በጫማና መጠጥ ኢንዱስትሪዎች የነበራቸውን ኢንቨስትመንት የቀጠሉበት ሲሆን የጣሊያን

ባለሀብቶች በህንጻ ግንባታ፣ በኮንስትራክሽንና በግብርና ኢንዱስትሪዎች መስክም ሠርተዋል።

በመሆኑም በ1968 አብዮቱ የወረሳቸው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በውጭ አገር ባለሀብቶች ባለቤትነት የተያዙ፣ የአመራርም ሆነ የቴክኒክና ሙያ ሥራዎች በውጭ አገር ዜጎች የሚከናወኑበት፣ በአገር ውስጥ ገበያ ላይ ያተኮሩ ቀላል ኢንዱስትሪዎች የሚበዙበት፣ ከፍተኛ ካፒታል የሚጠይቁና ከአቅም በታች የሚሠሩ፣ ከሌሎች ዘርፎች ጋር የነበራቸው ትስስር አናሳ የሆነና በአዲስ አበባ አካባቢ ብቻ የተከማቹ ነበሩ። በኤርትራ በነበረው ጦርነትና በሠራተኞች አመጽና ሥራ ማቆም ምክንያት ወደ 30% የሚሆኑና ኤርትራ ውስጥ የነበሩ ፋብሪካዎች ተዘግተው ነበር።

የ1966ቱን አብዮት ተከትሎ የተከሰተው የኢኮኖሚ ምስቅልቅል ሁኔታ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ነበረው። የግል ኢንቨስትመንት እንዲቆም ተደረገ፣ የሠራተኛ ምርታማነትም መቀነስ ጀመረ። ከ1968 በኋላ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ዕድገት ባለበት የሚሄድ ነበር። ከ1958 እስከ 1966 በነበሩት ጊዜያት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዕድገት 6.1% ነበር። ከ1967 እስከ 1970 ዕድገቱ የቀነሰ ሲሆን ከ1971 እስከ 1972 የ18.9% ዕድገት የተመዘገበበት ጊዜ ነበር። ከዚያ በኋላ ግን ዕድገቱ እየቀነሰ ሄዶ ከ1973 እስከ 1977 የነበረው ዓመታዊ አማካይ የዕድገት መጠን 3.1% ሲሆን ከ1978 እስከ 1981 የነበረው የዕድገት መጠን 3.8% ነበር።

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አፈጻጸም በወቅቱ የነበረውን የአገሪቷን ሁኔታ የተከተለ ነበር። በአብዮቱ የመጀመሪያ ዓመታት የነበረው የግል ንብረት መውረስ፣ የፋብሪካ አመራሮች ስደት፣ በኤርትራና ኦጋዴን አካባቢ የነበረው ጦርነትና በየአከባቢው የተደረጉ ግጭት ፋብሪካዎች የማምረት ተግባራቸውን እንዲያቆሙ ያስገደደ ነበር። እ.ኤ.አ በ1970 መጨረሻ አካባቢ የማምረት አቅም ማሳደግ ላይ ያተኮረ የምርት ዕድገት ዘመቻ የተካሄደበት ጊዜ ነበር። በዚህ ዘመቻ ምክንያት በ1971 አገሪቷ 27.3% የኢኮኖሚ ዕድገት አስመዝግባ ነበር። በ1978 አብዛኞቹ ፋብሪካዎች ከ70-100% የሚደርስ የማምረት አቅማቸውን የተጠቀሙ ሲሆን ብዙዎች በሦስት ፈረቃ ሠርተዋል። ይህም በአፍሪካ ደረጃ ሲታይ ከፍተኛ ዕድገት ነበር።

በየካቲት ወር 1968 አገሪቷ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ፖሊሲን የሚትከተል መሆኑን የሚገልጽ የፖሊሲ ሰነድ መንግሥት አወጣ። በዚህ ፖሊሲ ሰነድ መሠረት መንግሥት የሚሳተፍባቸው ሦስት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ መስኮች ተለይተው የቀረቡ ሲሆን እነሱም፣ ለሌሎች ኢንዱስትሪዎች የሚያገለግሉ ምርቶችን የሚያመርቱና በኢኮኖሚው ትስስር መፍጠር የሚችሉ መሠረታዊ ኢንዱስትሪዎች፣ መሠረታዊ የፍጆታ ዕቃዎችን የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች እና የመድኃኒት፣ የትንባሆና የመጠጥ ኢንዱስትሪዎች ነበሩ። ከዚህም በተጨማሪ

መንግሥትና የግሉ ዘርፍ የሚሳተፉባቸው የሥራ መስኮች ተለይተው ቀርበዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ለመንግሥት ብቻ የተከለሉ፣ ለግሉ ዘርፍ የተፈቀዱና መንግሥትና የግሉ ዘርፍ በጋራ የሚሳተፉባቸው የሥራ መስኮች እንዲለዩ ተደርጓል፡፡

በ1973 የግብርና ምርት በመቀነሱና ጥሬ ዕቃ ከውጭ አገር ለማስገባት የውጭ ምንዛሪ እጥረት በመከሰቱ ምክንያት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ምርታማነት ማሽቆልቆል ጀመረ፡፡ በማምረቻ መሣሪያዎች እርጅና እና በመለዋወጫ ዕቃዎች እጥረት ምክንያት ሁኔታው እንደተባባሰና እ.ኤ.አ በ1990ዎቹ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርታማነት በእጅጉ እንደቀነሰ ተንታኞች ይገምታሉ፡፡ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የማምረት አቅም በማሳደግ ችግሩን ለመቅረፍ መንግሥት በ1980 ለዘርፉ ብር 342 ሚሊዮን ኢንቨስትመንት ዕቅድ ይዞ ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የውጭ አገር ኢንቨስትመንት ለመሳብ ሲባል መንግሥት በ1982 አዋጅ ቁጥር 2 አወጥቶ ነበር፡፡ በመጨረሻም የአገሪቷ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ሥርዓት በቅይጥ ኢኮኖሚ ሥርዓት መተካቱን መንግሥት በ1983 አወጀ፡፡ በዚህ አዋጅ መሠረት የግል ባለሀብቶች ያለምንም ካፒታል ጣራ ገደብ በማንኛውም የኢኮኖሚ ዘርፍ ኢንቨስትመንት መሳተፍ እንደሚችሉ ነው፡፡

በ1976 በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ያወጣው አዋጅ ቁጥር 235 (የሽርክና ኢንቨስትመንት አዋጅ) አገሪቷ የውጭ አገር ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ፍላጎት ያላት መሆኑን ያመላከተ ነበር፡፡ አዋጁ ለአዳዲስ ፕሮጀክቶች የአምስት ዓመት የታክስ እፎይታ ጊዜ፣ ገቢና ወጪ ምርቶችን ከቀረጥ ነጻ ማድረግ፣ የታሪፍ ከለላ፣ ለውጭ ባለሀብቶች ትርፍና ካፒታልን መልሰው ወደ አገራቸው የመውሰድ መብት የመሳሰሉ ማበረታቻዎችን ያካተተ ነበር፡፡ በሽርክና ኢንቨስትመንት የውጭ ባለሀብት ድርሻ ብበዛ 49% እንደሚደርስና የሽርክናው ጊዜ ከ25 ዓመት እንደማይበልጥ በአዋጁ ተደንግጓል፡፡ አዋጁ ንብረታቸው እንደማይወረስ ለኢንቨስተሮች ዋስትና የሰጠ ቢሆንም “የአገር ጥቅም ለማስጠበቅ” በሚል ምክንያት በሽርክና የተያዙ ኢንቨስትመንቶችን የመግዛት ሙሉ መብት ለመንግሥት ሰጥቷል፡፡ የውጭ ድርጅቶችም በአገሪቷ መዋዕለ ንዋይ ለማፍሰስ ያሳዩት ፍላጎት እምብዛም ስለነበር አዋጁ እንደታሰበው የውጭ ኢንቨስትመንት የሚስብ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ቀደም ሲል በ1976 ወጥቶ የነበረው አዋጅ በማሻሻል መንግሥት የማሻሻያ ልዩ አዋጅ ቀጥር 2 አወጣ፡፡ ይህም ማሻሻያ ለህዝብ ጥቅም ሲባል ለውጭ ባለሀብቶች ያልተፈቀዱ እንደ ባንክና ፋይናንስ፣ ንግድ፣ ትራንስፖርትና ኮሙኒኬሽን ከመሳሰሉት ውጪ ባሉት ዘርፎች የውጭ ባለሀብቶች አብዘኛውን ድርሻ ይዘው በሽርክና መሳተፍ እንደሚችሉ ያመለክታል፡፡ ማሻሻያው ትርፍን ወደ አገር በመውሰድ ረገድ የነበረውን እገዳ ሁሉ በማንሳት ከቀድሞው አዋጅ በተሻለ ሁኔታ ለባለሀብቶች ጥበቃ ያደርጋል፡፡

በ1983 የሶሻሊስት ሥርዓቱ መውደቅ አይቀሬ እየሆነ ሲመጣ ደርግ የቅይጥ ኢኮኖሚ ፖሊሲን አዋጀ፡፡ በዚህ ፖሊሲ መሠረት የግሉ ዘርፍ ያለምንም ካፒታል ጣራ በማንኛውም ዘርፍ ኢንቨስትመንት መሳተፍ እንደሚችል፣ መንግሥት በሊዝ በሚሰጣቸው መሬት ላይ የመኖሪያ ቤት፣ አፓርትመንትና የቢሮ ህንጻዎችን መገንባት ማከራየትና መሸጥ፣ የንግድ ድርጅቶች፣ ኢንዱስትሪዎችና ሆቴሎችን ማቋቋም እንደሚቻል ተመልክቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አትራፊ የመንግሥት ኢንዱስትሪዎች እንደሚቀጥሉና ሌሎች በኪሳራ የሚንቀሳቀሱ ደግሞ እንደሚዘጉ ወይም እንደሚሸጡ ይገልፃል፡፡ ገበሬዎች ለያዙት መሬት የይዞታ ማረጋገጫ እንደሚሰጣቸውና ያመረቱትን ምርት በነጻ ገበያ መሸጥ እንዲችሉ መብት ይሰጣቸዋል፡፡ ምንም እንኳን የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ፕራይቬታይዜሽን፣ የመሬት ይዞታና የንብረት ካሣ ክፍያ የመሳሳሉ ጉዳዮች ሊስተናገዱ የሚገቡ ጉዳዮች የነበሩ ቢሆኑም በደርግ መንግሥት  የቀረቡት ፕሮፖዛሎች ለቀጣይ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ተስፋ ሰጪ  ሁኔታዎች እንደነበሩ  አንዳንድ የኢኮኖሚ ጥናት ባለሙያዎች በወቅቱ አመልክተው ነበር፡፡ በሌላ በኩል ግን ደርግ ያቀረበው የማሻሻያ ሃሳቦች በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ መቋቋም ስለተሳነው ብቻ ነው የሚሉትም ነበሩ፡፡

በ1996 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ያወጣው የኢንዱስትሪ ፓሊሲ ለኢንዱስትሪው ዘርፍ ልማት በአጠቃላይና ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት በተለይ የላቀ ትኩረት የሰጠ ነው፡፡ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂው የተነደፈው የዓለም አቀፍ ሁኔታና የነጻ ገበያ ፍልስፍናን መነሻ ያደረገና በሚከተሉት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ነበር፣

- የኢንዱስትሪው ልማት ስትራቴጂው ሞተር የግል ባለሀብት መሆኑን መቀበል፣
- የግብርና-መር የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫን መከተል፣
- ኤክስፖርት-መር የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫን መከተል፣
- ጉልበትን በሰፊው በሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች ላይ ያተኮረ የልማት አቅጣጫን መከተል፣
- የአገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶችን አቀናጅቶ የመጠቀም አቅጣጫን መከተል፣
- መንግሥት ጠንካራ የአመራር ሚና የሚጨወትበትን አቅጣጫ መከተል እና
- መላው ኅብረተሰብ ለኢንዱስትሪ ልማት በጋራ የሚሰለፍበትን አቅጣጫ መከተል ናቸው፡፡

ኢንዱስትሪው በኢኮኖሚው ውስጥ የመሪነት ሚና እንዲጫወት መሠረት ለመጣል የሚያስችሉና ቅድሚያ ትኩረት የሚሹ የኢንዱስትሪ ዓይነቶች በኢንዱስትሪው ልማት ፖሊሲው ተለይተው ቀርበዋል፡፡ እነዚህም የጨርቃጨርቅና አልባሳት፣ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች፣ የኬሚካል፣ የብረታብረት፣ የአግሮ ፕሮሰሲንግና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪዎች ናቸው፡፡ የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲው ለቀጣይ የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ዕድገትም የማዕዘን ድንጋይ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## አባሪ 2፡ የመካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች የማክሮ ኢኮኖሚ፣የዜጎች ኑሮ ደረጃና ማህበራዊ ልማት ደረጃ አመልካች መስፈርቶች (indicators)

### ሰንጠረዥ 5.1፡ የማክሮ ኢኮኖሚ ዕድገት ደረጃ ቁልፍ አመልካቾች indicators)

| የአገር | ዓመት (እ.ኤ.አ) | ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የግብርና ድርሻ በ% | ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የኢንዱስትሪ ዘርፍ ድርሻ በ% | ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ ድርሻ በ% | ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የአገልግሎት ዘርፍ ድርሻ በ% | ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የኤክስፖርት ድርሻ በ% | ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የገቢ ምርት ድርሻ በ% | ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የካፒታል ድርሻ በ% | ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የተጣራ የውጭ ኢንቨስትመንት ፍሰት ድርሻ በ% | ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የአገር ውስጥ ቁጠባ ድርሻ በ% | ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ገቢ የተጣራ የአገር ውስጥ ምርት ድርሻ በ%) | ከአገር ውስጥ ጠቅላላ ምርት የአገር ውስጥ ገቢ ድርሻ በ% (እርዳታ ሳይጨምር) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብራዝል | 1969 | 13.22 | 37.36 | 28.85 | 49.42 | 6.62 | 6.55 | | 2.53 | 22.42 | 0.52 | |
| ቻይና | 2004 | 13.39 | 46.23 | 32.37 | 40.38 | 33.95 | 31.40 | 40.73 | 3.96 | 45.81 | 0.09 | |
| ኮሎምብያ | 1970 | 25.69 | 28.30 | 21.15 | 46.02 | 14.31 | 15.82 | 18.08 | 4.36 | 18.66 | 2.29 | |
| ኮስታሪካ | 1965 | 24.57 | 21.72 | | 53.71 | 25.26 | 28.75 | 16.38 | 7.22 | 12.50 | 2.63 | |
| ግብጽ | 1998 | 17.11 | 30.86 | 18.29 | 52.02 | 16.21 | 25.71 | 21.33 | 8.87 | 12.00 | 2.28 | |
| ኤልሳልቫዶር | 1992 | 14.56 | 30.28 | 24.40 | 55.16 | 16.09 | 32.43 | 17.18 | 7.40 | 2.18 | 6.78 | |
| ጓትማላ | 1998 | 23.44 | 19.99 | 13.57 | 56.57 | 18.17 | 26.25 | 16.65 | 2.18 | 9.31 | 1.21 | 9.53 |
| ኮሪያ. | 1973 | 26.74 | 29.21 | 22.23 | 44.04 | 28.68 | 31.85 | 24.18 | | 22.44 | 2.06 | |
| ማሌዥያ | 1976 | 27.64 | 35.05 | 18.52 | 37.31 | 48.95 | 39.03 | 22.52 | 4.53 | 31.18 | 0.56 | |
| ሞሮኮ | 2007 | 13.73 | 27.31 | 15.04 | 58.95 | 35.75 | 44.86 | 31.25 | 3.73 | 23.37 | 1.44 | 34.75 |
| ኡራጋይ | 1980 | 28.62 | 27.44 | 16.01 | 43.93 | 15.31 | 28.70 | 30.17 | 1.69 | 18.26 | 0.66 | |
| ስሪላንካ | 2006 | 11.34 | 30.64 | 19.23 | 58.02 | 30.13 | 41.13 | 24.87 | 1.86 | 16.98 | 2.82 | 16.32 |
| ሶርያ | 2004 | 21.86 | 34.64 | 9.75 | 43.50 | 40.57 | 37.78 | 23.83 | 3.06 | 20.20 | 0.43 | |
| ታይላንድ | 1990 | 12.50 | 37.22 | 27.20 | 50.28 | 34.13 | 41.65 | 40.38 | 4.58 | 33.84 | 0.94 | |
| ቱኒዝያ | 1990 | 15.72 | 29.79 | 16.89 | 54.49 | 43.56 | 50.60 | 24.36 | 4.30 | 20.02 | 3.29 | 30.71 |
| አማካይ | የመካከለኛ ገቢ አገሮች ሞዴል (MMIC)-0 | 19.34 | 31.07 | 20.25 | 49.59 | 27.18 | 32.17 | 25.14 | 4.31 | 20.61 | 1.87 | 22.80 |
| መካከለኛ (Median) | MMIC-0 | 17.11 | 30.28 | 18.87 | 50.28 | 28.68 | 31.85 | 24.00 | 4.13 | 20.02 | 1.44 | 23.47 |
| አማካይ | የመካከለኛ ገቢ አገሮች ሞዴል (MMIC) | 20.7 | 30.7 | 17.8 | 48.6 | 30.5 | 37.4 | 26.6 | 4.5 | 21.6 | 4.5 | 20.7 |
| መካከለኛ (Median) | (የመካከለኛ ገቢ አገሮች ሞዴል(MMIC) | 19.6 | 29.1 | 16.4 | 50.4 | 28.9 | 32.2 | 26.3 | 3.7 | 22.6 | 2.7 | 18.5 |

**(ምንጭ International Growth Centre) IGC, 2012)**

## ሰንጠረዥ 5.2፡ የመካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች የዜጎች ኑሮና የማህበራዊ ልማት ደረጃ አማልካች ሞዴል

| አገር | ዓመ | ከጠቅላላ የሠራተኛ ኃይል | ከጠቅላላ የሠራተኛ ኃይል በኢንዱስትሪ | ከጠቅላላው ህዝብ በገጠር | ከአጠቃላይ የትምህርት ተሳትፎ | ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት | ነፍስ ወከፍ የኤሌክትሪክ ኃይል | ከድህነት ወለል በታች ያለው | በቀን በ51.25 መስፈርት | ዓመታዊ የህዝብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|

| | (እ፣ኤ.አ) | በግብርና ዘርፍ የተሰማራ በ% | ዘርፍ የተሰማራ በ% | የሚኖር ህዝብ መጠን በ% | የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ መጠን በ% | ገንዘብና ገንዘብ ነክ ንብረቶች ያላቸው ድርሻ በ% | ፍጆታ በኪሎዋት አወር) | የህዝብ መጠን በ% | የGINI ኢንዴክስ | በሀብታምና ደሀ መካከል ያለው ልዩነት መጠን በ% | ዕድገት ምጣኔ በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብራዝል | 1969 | | | 45.30 | | 17.92 | | | | | 2.52 |
| ቻይና | 2004 | 44.10 | 17.70 | 60.52 | 66.97 | 141.81 | 1586.25 | | | | 0.59 |
| ኮሎምቢያ | 1970 | | | 45.20 | 23.98 | 19.84 | | | | | 2.60 |
| ኮስታሪካ | 1965 | | | 64.50 | | 19.61 | | | | | 3.38 |
| ግብጽ | 1998 | 29.80 | 22.30 | 57.32 | 70.07 | 73.28 | 867.32 | | | | 1.88 |
| ኤልሳልቫዶር | 1992 | 35.80 | 22.70 | 48.88 | 40.85 | 30.10 | 385.01 | | | | 1.55 |
| ጓትማላ | 1998 | 37.60 | 23.20 | 55.70 | 31.27 | 19.53 | 344.44 | 29.85 | 55.65 | 15.65 | 2.29 |
| ኮርያ | 1973 | | | 54.92 | | 31.47 | 399.06 | | | | 1.99 |
| ማሌዥያ | 1976 | | | 61.44 | | 60.15 | 463.90 | | | | 2.30 |
| ሞሮኮ | 2007 | 43.30 | 20.30 | 44.32 | 55.85 | 97.40 | 707.05 | 13.97 | 40.88 | 2.50 | 1.20 |
| ኡራጋይ | 1980 | | | 58.30 | 26.52 | 19.43 | 240.40 | | | | 2.78 |
| ስሪላንካ | 2006 | 32.20 | 26.60 | 84.90 | 87.00 | 37.93 | 399.23 | | | | 1.10 |
| ሶርያ | 2004 | 27.00 | 25.60 | 47.12 | 63.11 | 74.18 | 1322.46 | | | | 3.07 |
| ታይላንድ | 1990 | 63.30 | 13.60 | 70.60 | 29.06 | 68.42 | 708.13 | | | | 1.36 |
| ቱኒዝያ | 1990 | 25.80 | 33.60 | 42.10 | 44.03 | 49.67 | 638.43 | 19.04 | 40.24 | 5.87 | 2.43 |
| አማካይ | የመካከለኛ ገቢ.አገሮች ሞዴል (MMIC)-0 | 37.66 | 22.84 | 56.07 | 43.97 | 50.72 | 671.81 | 20.95 | 45.59 | 8.01 | 2.07 |
| መካከለኛ (Median) | MMIC-0 | 35.80 | 22.70 | 55.70 | 44.03 | 37.93 | 551.17 | 19.04 | 40.88 | 5.87 | 2.29 |
| | | | | | 46.5 | | | | | | |
| አማካይ | የመካከለኛ ገቢ.አገሮች ሞዴል( (MMIC) | 42.2 | 20.5 | 62.3 | 46.5 | 51.5 | 403.7 | 48.4 | 38.9 | 5.3 | 2.2 |
| መካከለኛ (Median) | (የመካከለኛ ገቢ.አገሮች ሞዴል (MMIC) | 43.3 | 18 | 64 | 47.6 | 43.1 | 323.6 | 48.4 | 38.5 | 4.6 | 1.9 |

(ምንጭ International Growth Centre) IGC, 2012)

**አባሪ 3፡ በማክሮና በኢኮኖሚ ዘርፎች ደረጃ ከተለያዩ መ/ቤቶች መረጃ በመስጠት በጥናቱ የተሳተፉ የመንግሥት በለሥልጣናትና ግለሰቦች ዝርዝር**

**1 በማክሮ ደረጃ መረጃ በመስጠት የተሳተፉ(በቃለ መጠይቅ)**

| ተ.ቁ | ስም | መሥሪያ ቤት | ኃላፊነት |
|---|---|---|---|
| 1 | የተከበሩ አቶ መኮንን ማንያዘዋል | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | ሚኒስትር |
| 2 | የተከበሩ አቶ ታደሰ ሃይሌ | ኢንዱስት ሚኒስቴር | ሚኒስትር ዴኤታ |
| 3 | የተከበሩ አቶ አለማየሁ ተገኑ | ውሃና ኢነርጅ ሚኒስቴር | ሚኒስትር |
| 4 | የተከበሩ ወ/ሮ ስንቅነሽ እጅጉ | ማዕድን ሚኒስቴር | ሚኒስትር |
| 5 | የተከበሩ አቶ ወንድራድ ማንደፍሮ | እርሻ ሚኒስቴር | ሚኒስትር ዴኤታ |
| 6 | የተከበሩ ዶ/ር አብርሃም ተከስተ | ፋይናንስና ኢኮኖሚ ዕድገት ሚኒስቴር | ሚኒስትር ዴኤታ |
| 7 | የተከበሩ አቶ ወንድወሰን ክፍሉ | ትምህርት ሚኒስቴር | ሚኒስትር ዴኤታ |
| 8 | የተከበሩ ዶ/ር ካባ ኡርጌሳ | ትምህርት ሚኒስቴር | ሚኒስትር ዴኤታ |
| 9 | የተከበሩ አቶ ዮሐንስ አያለው ብሩ | ብሔራዊ በንክ | ምክትል ገዥ |
| 10 | አቶ ፍቅሩ ገዛኸኝ | ብሔራዊ ባንክ | ተጠባባቂ ዳይሬክተር |
| 11 | አቶ ተስፋዬ ገዛኸኝ | ብሔራዊ ባንክ | ተጠባባቂ ዳይሬክትር |
| 12 | አቶ ኤልያስ ሎላ | ብሔራዊ ባንክ | ዳይሬክተር |
| 13 | አቶ ገብረመስቀል ጫላ | ፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ኤጀንሲ | ዳይሬክተር |
| 14 | አቶ መኩሪያ | ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮሮፓሬሽን | የዕቅድ ኃላፊ |
| 15 | የተከበሩ አቶ መሐመድ ሰይድ | የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ | ተጠባባቂ ዋና ዳይሬክተር |
| 16 | የተከበሩ አቶ ኢሳያስ በርሄ | ኢትዮጵያ ልማት ባንክ | ፕሬዚዳንት |
| 17 | አቶ ዮሐንስ መለሰ | ገቢና ጉምሩክ ባለሥልጣን | ዳይሬክተር |

## 2 በኢኮኖሚ ዘርፎች ደረጃ መረጃ በመስጠት የተሳተፉ

### 2.1 የአግሮ ፕሮሰሲንግ ዘርፍ (ቃለመጠይቅ)

| ተ.ቁ | ስም | መሥሪያ ቤት | ኃላፊነት |
|---|---|---|---|
| 1 | ዶ/ር ሰይፉ | እርሻ ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ | ዳይሬክተር |
| 2 | አቶ ወንድሙ በለጠ | ኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ | የአግሮ ዘርፍ ቡድን መሪ |
| 3 | አቶ አማኑኤል | ኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ | ኤክስፐርት |
| 4 | ወ/ሮ ራሔለ ፍፁም | ኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ | ኤክስፐርት |
| 5 | አቶ ደንደና ጨመዳ | አግሮ ፕሮሰሲንግ | ዳይሬክተር |
| 6 | አቶ ፈቀደ ወንድማገኝ | ማስፋፋት ቡድን (እርሻ ሚኒስቴር) | ዳይሬክተር |
| 7 | ወ/ሮ ቀኖ አባቴ | ማስፋፋት ቡድን (እርሻ ሚኒስቴር) | ኤክስፐርት |
| 8 | አቶ ስዩም አባቴ | ማስፋፋት ቡድን (እርሻ ሚኒስቴር) | ኤክስፐርት |
| 9 | አቶ መሐመድ | ማስፋፋት ቡድን (እርሻ ሚኒስቴር) | ኤክስፐርት |
| 10 | ግደይ ገ/መድህን | እርሻ ሚኒስቴር | የወተትና ሥጋ ልማት ዳይሬክተር |
| 11 | አቶ ኢሳያስ | እርሻ ሚኒስቴር | አግሮ ፕሮሰሲንግ ዳይሬክተር |
| 12 | አቶ አሰፋ | ንግድ ሚኒስቴር | አማካሪ |

**የቡድን ውይይት (1)**

| ተ.ቁ | ስም | መሥሪያ ቤት/ድርጅት | ኃላፊነት |
|---|---|---|---|
| 1 | ሞገስ አዝምቴ | የጤና ምግብ ማኑፋክቸሪንግ | ፕሮጀክት ማናጀር |
| 2 | አበቴ መንገሻ | አስቴር ቡና | ዋና ሥራ አስኪያጅ |
| 3 | ካለዩ ተሰማ | ኢትዮጵያ መርከብና ሎጂስቲክ ኢንተርፕራይዝ | ሽፕንግ ዳይሬክተር |
| 4 | ኤልያስ ገነቲ | ድያስፓራ አግሮ ኢንዱስትሪ | ማነጅንግ ዳይሬክተር |
| 5 | ቤን ቫን አምትንግ | ስሌት ህልንግ የተወሰነ የግል ማህበር | ዋና ሥራ አስኪያጅ |
| 6 | ተስፋዬ ተ/ሃይማኖት | ካለብ የተወሰነ የግል ማህበር | ዋና ሥራ አስኪያጅ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 7 | ተዎድሮስ አሰፋ | ህልና ቡና | ዋና ሥራ አስኪያጅ |
| 8 | ሰለሞን አባቴ | ኢትዮጵያ እርሻ ምርምር ኢንስትቲዩት | ዳይሬክተር |
| 9 | ዳዊት አለም | ኢትዮጵያ እርሻ ምርምር ኢንስትቲዩት | አስተባባሪ |
| 10 | አማረ ሰይፉ | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | ቡድን መሪ |
| 11 | ዘርጋው ፈለቀ | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | ቡድን መሪ |
| 12 | መንገሻ ታደሰ | ኢትዮጵያ እርሻ ልማት ፕሮግራም | ቡድን መሪ |
| 13 | ይበል ሃ/ስላሴ | አፍሪካ ጁስ | ፋይናንስ ማናጀር |
| 14 | በለጠ በየነ | ህልና ምግብ | ዋና ሥራ አስኪያጅ |
| 15 | ሃይሌ ወ/ጊዮርጊስ | ፋፋ ምግብ ሃላፍነቱ የተወሰነ የግል ማህበር | ም/ሥራ አስኪያጅ |
| 16 | መስፍን አባቴ | ብሔራዊ አልኮልና አረቄ ፋብሪካ | ም/ዋና ሥራ አስኪያጅ |

**የቡድን ውይይት**

| ተ.ቁ | ስም | መሥሪያ ቤት/ድርጅት | ሃላፊነት |
|---|---|---|---|
| 1 | ዮሐንስ ባሸህ | ማሪና ሰም ማህበር | ዋና ሥራ አስኪያጅ |
| 2 | አቡ ነገሶ | ኤኤችቢፕኤ | ፕሬዚዳንት |
| 3 | ታምራት እጅጉ | ኢትዮጵያ ሥጋ ላኪዎች ማህበር | ተጠባባቂ ዋና ፀሐፊ |
| 4 | በድሉ አሰፋው | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | ቡድን መሪ |
| 5 | ሰለሞን አባቴ | ኤኤኤአር | ዋና ዳሬክተር |
| 6 | ተድላ ዘገዬ | ኤኤችቢፕኤ | አስተዳደር እና ፋይናንስ |
| 7 | አሰግድ አደነ | ኡኤንኣይዲኮ | ፕሮግራም ኦፊሰር |
| 8 | ሙሉጌታ ተገኝ | የምግብ ዘይት አምራቾች ማህበር | ዋና ፀሐፊ |
| 9 | ደሴ አበጀ | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | ቡድን መሪ |

## 2.2 ቆዳና ጫማ

### ቃለ መጠይቅ (1)

| ተ.ቁ | ስም | መሥሪያ ቤት/ድርጅት | ሃላፊነት |
|---|---|---|---|
| 1 | ወንዱ ለገሠ | ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት | ዋና ዳይሬክተር |
| 2 | ብርሃኑ ሰርጀቦ | ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት | የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር |
| 3 | አቶ ማርዮ | ኤአርኤ ጫማ ፋብሪካ | ዋና ሥራ አስኪያጅ |
| 4 | ወ/ሮ ራሉካ | ኤአርኤ ጫማ ፋብሪካ | ም/ዋና ሥራ አስኪያጅ |

### ከቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት (የቡድን ውይይት 1)

| ተ.ቁ | ስም | መሥሪያ ቤት/ድርጅት | ኃላፊነት |
|---|---|---|---|
| 1 | ጡጂአንግ | ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት | ዋና ሥራ አስኪያጅ |
| 2 | ፀጋዬ ተፈራ | ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት | ሬጅስትራር |
| 3 | ሬድዋን በዳዳ | ሞጆ ቆዳ ፋብሪካ | ሥራ አስኪያጅ |
| 4 | ሚሻም ዋከሶ | ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት | ቴክኖሎጅስት |
| 5 | ያለው አለማየሁ | ዋልያ ቆዳ ፋብሪካ | ም/ሥራ አስኪያጅ |
| 6 | አድገኝ ከበደ | ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት | ኢኮኖሚስት |
| 7 | ቤቴልሔም ጥላሁን | ቦኤስቴክ የተወሰነ የግል | ዋና ሥራ አስኪያጅ |
| 8 | ወንድሙ ኩመራ | ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት | የሰው ሃብት ዳይሬክተር |
| 9 | ተሰፋዬ በየነ | ጀማይካ ጫማ | ም/ሥራ አስኪያጅ |
| 10 | ቢንያም በዳዳ | ድሬ | ዋና ሥራ አስኪያጅ |
| 11 | ወንዱ ለገሠ | ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት | ዋና ዳይሬክተር |
| 12 | ያህቆብ ታደሰ | ኢትዮ-አፍሪካ ቆዳ ፋብሪካ | አስተዳዳር ሥራ አስኪያጅ |

## የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት (የቡድን ውይይት 2)

| ተ.ቁ | ስም | የመሥሪያ ቤት/ድርጅት | ሃላፍነት |
|---|---|---|---|
| 1 | ዳኛቸው ደመላሽ | ኢትዮጵያ ታነሪ ሼር ካምፓኒ | የፋይናንስ ዳይሬክተር |
| 2 | አምባሳደር ብሩክ ደበበ | ኢትዮ-ቆዳ ኢንዱስትሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር | ዋና ሥራ አስኪያጅ |
| 3 | ብርሃኑ ሰርጆቦ | ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት | ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት |
| 4 | እስመኤል ፊይሣ | ኤችኤኤፍኤዲኢ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር | ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ |
| 5 | ሰለሞን ጌቱ | ክሪስታል ታነሪዎች | ማኔጅንግ ዳይሬክተር |
| 6 | ተስፋዬ ቤኛ | ኮልባ ታነሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ | አጠቃላይ አገልግሎት ሃላፊ |
| 7 | አብዲሳ አዱኛ | ኢትዮ ሌዘር ኢንዱስትሪዎች ማህበር | ዋና ፀሐፊ |
| 8 | ሰለሞን ታደለ | ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት | ዳይሬክተር |
| 9 | ካሉ ከበደ | ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት | ዳይሬክተር |
| 10 | ብርሃኑ ንጉሥ | ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት | ዳይሬክተር |

## 2.3 ኬሚካልና ፋርማሲዩቲካል ቃለ መጠይቅ 1)

| ተ.ቁ | ስም | መሥሪያ ቤት/ድርጅት | ሃላፊነት |
|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ሽመልስ | አዳሚ ቱሉ ፔስትሳይድ | ዋና ሥራ አስኪያጅ |
| 2 | አቶ ተስፋዬ | ፋርማክውር ኢትዮጵያ | ዋና ሥራ አስኪጅ |
| 3 | ወ/ት እቴነሽ አብርሃ | መድኃኒት ማኑፋክቸረሮች ማህበር | ፕሬዚዳንትና የምርት ኤክስፖርት |
| 4 | አቶ በቀለ | ኮስትክ ሶዳ ሼር ካምፓኒ | ዋና ሥራ አስኪያጅ |
| 5 | አቶ ወልደአረጋይ | ኮስትክ ሶዳ ሼር ካምፓኒ | ዋና ሥራ አስኪያጅ |
| 6 | ኢንጂነር ሌሊሳ ዳባ | ኪልኔር ፕሮዳክሽን ማዕከል | ዳይሬክተር |
| 7 | ኢንጅነር አስራት ቡልቡላ | ሚድሮክ ኢትዮጵያ | አማካሪ |
| 8 | አቶ አስመላሽ ሃይሉ | ኤኤስኤምአይ መድኃኒት አቅራቢዎችና ኢንዱስትሪ | ዳይሬክተርና የፋርማ ማህበር ፀሐፊ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 9 | አቶ ሰለሞን ዮሐንስ | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | ዳሬክቶሬት ዳይሬክተር |
| 10 | አቶ ተስፋዬ ኃ/ሚካኤል | ካድላክ መድኃኒት ኢትዮጵያ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር | ፕሬዚዳንት |

## የቡድን ውይይት (ፋርማሲዩቲካል ዘርፍ) (1)

| ተ.ቁ | ስም | መሥሪያ ቤት /ድርጅት |
|---|---|---|
| 1 | የማነብርሃን ታደለ | መድኃኒት ፈንድና አቅራብ ኤጀንሲ |
| 2 | ሽመልስ አየለ | ኢትዮጵያ መድኃኒት ማኑፋክቸሪንግ ሼር ካምፓኒ |
| 3 | ያሲን አህመድ | ኢትዮጵያ ምግብ መድኃኒትና ጤና ጥበቃ አስተዳደር |
| 4 | መንግስተአብ ወልደ አረጋይ | ኢትዮጵያ ምግብ መድኃኒትና ጤና ጥበቃ አስተዳደር |

## የቡድን ውይይት (ኬሚካል ዘርፍ)

| ተ.ቁ | ስም | መሥሪያ ቤት/ድርጅት |
|---|---|---|
| 1 | አቶ ፀጋ | አፍሮ ጀርመን |
| 2 | አቶ ዳንኤል ፀጋዬ | ኢትዮጵያ ኬሚካል ሶሳይቲ |
| 3 | አቶ ግርማ ንዋይ | አጅካ (ኢትዮጵያ) ካምፓን |
| 4 | አቶ ሰይፉ ደርቤ | ፕላስቲክ ኢንዱስትሪ |
| 5 | አቶ ዳንኤል ፀሐይ | ኦርዞን አድስ ጎማ ሼር ካምፓን |
| 6 | ኢኒጅነር ሰይፌድን ካልድ | ካድስኮ ኬሚካል ኢንዱስትሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር |
| 7 | አቶ ሐብታሙ ካሳዬ | ጮራ ጋዝና የኬሚካል ምርቶች |
| 8 | አቶ ብርሃኑ አሰፋ | አዲስ አበባ ቴክኖሎጅ ኢንስትቲዩት (አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ) |

## 2.4 ብረታብረትና ኢንጅነሪንግ ዘርፍ

**የብረታብረት ኢንዱስትሪዎች ልማት ኢንስትቲዩትና ሌሎች ኢንዱስትሪዎች (ቃለ መጠይቅ)**

| ተ.ቁ | ስም | መሥሪያ ቤት/ድርጅት |
|---|---|---|
| 1 | ወንድማገኝ ደግነቱ | ጦሳ ብረታብረት ፋብሪካ |
| 2 | ሳሙኤል ሙሉነህ | ካስማ ኢንጅኔሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር |
| 3 | ዳንኤል ገብረ | መስፍን ኢንዱስትሪያል ኢንጅኔሪንግ ኃላፊነቱ ተወሰነ የግል ማህበር |
| 4 | የሱፍ አደምኑር | መስፍን ኢንዱስትሪያል ኢንጅኔሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር |
| 5 | አቶ ሀብቴ ወልዴ | ብረታብረት ሃይላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር |
| 6 | መሐመድ አብዱ | ሐዲድ ትሬዲንግ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር |
| 7 | አባድ ሳሊ | ሐድዲ ትሬዲንግ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር |
| 8 | ደምረው መታፈሪያ | ስንቴክ ኢትዮጵያ ሃላፊነቱ ተወሰነ የግል ማህበር |
| 9 | አቶ መላኩ መሰሉ | ዋልታ ብረታብረት ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር |
| 10 | አቶ ሥዩም ተሸመ | ፌደራል አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ |
| 11 | ማቲዎስ አሰሌ | ቃልቲ ብረታብረት ውጤቶች ፋብሪካ |
| 12 | አሰግድ ማሞ | ኢትዮጵያ ብረታብረት ውጤቶች ማኑፋክቸሪንግ ማህበር |
| 13 | ወርቅነህ ደለሌኝ | የብረት ኢንዱስትሪዎች ልማት ኢንስትቲዩት |
| 14 | መስፍን ላቀው | የብረት ኢንዱስትሪዎች ልማት ኢንስትቲዩት |
| 15 | ግርማ አለሙ | የብረት ኢንዱስትሪዎች ልማት ኢንስትቲዩት |

## ብረታብረት ኢንዱስትሪዎች ልማት ኢንስትተዩት (የቡድን ውይይት (1)

| ተ.ቁ | ስም | መሥሪያ ቤት/ ድርጅት |
|---|---|---|
| 1 | ወርቅነህ ደሳለኝ | ብረት ኢንዱስትሪዎች ልማት ኢንስትቲዩት |
| 2 | መስፍን ላቀው | ብረት ኢንዱስትሪዎች ልማት ኢንስትቲዩት |
| 3 | ግርማ አለሙ | ብረት ኢንዱስትሪዎች ልማት ኢንስትቲዩት |
| 4 | ደረጀ አስፋው | ብረት ኢንዱስትሪዎች ልማት ኢንስትቲዩት |
| 5 | ሹሙ ተፈራ | ብረት ኢንዱስትሪዎች ልማት ኢንስትቲዩት |
| 6 | መብሩ ሃብቴማሪያም | ብረት ኢንዱስትሪዎች ልማት ኢንስትቲዩት |
| 7 | ደርቤው ኂ/ማሪያም | ብረት ኢንዱስትሪዎች ልማት ኢንስትቲዩት |
| 8 | ካሳ አለማየሁ | አስኮ ብረታብረት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር |
| 9 | ወንድሙ ደግነቱ | ቶሳ ብረታብረት ፋብሪካ |
| 10 | ሽመልስ እሸቴ | ጦሳ ብረታብረት ፋብሪካ |
| 11 | ደምሬው መታፈሪያ | ስንቴትክ ኢትዮጵያ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር |
| 12 | ሰሃድ ኢብራሁም | ኢውሮ ከብል |
| 13 | በላይ አለምነህ | አለም ብረታብረት ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር |
| 14 | ይስሐቅ አለምነህ | አስኮ ብረታብረት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር |
| 15 | አደም | አለም ብረታብረት ኀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር |
| 16 | መሰረት አለምነህ | አስኮ ብረታብረት ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር |
| 17 | አለምነህ በየነ | አለም ብረታብረት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር |
| 18 | ካፒቴን ተሰማ ግደይ | ኢትዮጵያ ብረታብረትና ኢንጅነሪንግ ኮሮፓሬሽን |
| 19 | በቀለ በቃና | ኢትዮጵያ ብረታብረትና ኢንጅነሪንግ ኮሮፓሬሽን |
| 20 | ሞሳ ይማም | ኢትዮጵያ ብረታብረትና ኢንጅነሪንግ ኮሮፓሬሽን |
| 21 | አቡሃይ ምህረቴ | ኢትዮጵያ ስታንዳርድስ ኤጀንሲ |
| 22 | ዮናታን መንገሻ | ኢትዮጵያ ኮንፎርምት አሰስመንት ኢንተርፕራይዝ |
| 23 | ብርሃኑ በቸሬ | ኢትዮጵያ መካኒካል ኢንጅነሮች ማህበር |
| 24 | መንግስቱ ባዬልኝ | ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ማህበር |

## 2.5 ጨርቃጨርቅና አልባሳት ዘርፍ (ቃለ መጠይቅ)

| ተ.ቁ | ስም | መሥሪያ ቤት/ ድርጅት |
|---|---|---|
| 1 | አቶ ሰለሞን | የኬሚካል ኢንዱስትሪ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር |
| 2 | አቶ ደያንግ ሊህ | የኮሪያ ትሬድንግ ኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ኤጀንሲ ዳይሬክተር |
| 3 | ፓርክ ዮንክዩ | የኮሪያ ኢንተርናሽናል ደቨሎፕመንት ዳይሬክተር |
| 4 | አቶ አሰፋ አጋ | ኢትዮጵያ ጥጥ አምራቾች ማህበር ፕሬዚዳንት |
| 5 | አቶ ስለሺ ለማ | ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት ዳይሬክተር |

## የኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲቲዩት( ቡድን ውይት (1)

| ተ.ቁ | ስም | መሥሪያ ቤት/ ድርጅት |
|---|---|---|
| 1 | ኤፍሬም በቀለ | የኢንጅነሪንግ አገልግሎት ዳይሬክተር |
| 2 | አናጋው ንጉሤ | የጥልፍና ሽመና ቴክኖሎጅ ዳይሬክተር |
| 3 | አምሃ በቀለ | የጥናትና ቤቴ ሙከራ ዳይክሬተር |
| 4 | ፍቅሩ ተስፋ | የፍንሽንግ ቴክኖሎጅ ዳይሬክተር |
| 5 | ስዩም ተክለአብ | ጋርመንት ቴክኖሎጅ ዳይሬክቴር |
| 6 | ያሬድ መስፍን | የማርኬቲንግ ዳይሬክተር |

## በኢንተርፐራይዝ ልማት የቡድን ውይይት ላይ የተሳተፉ

| ተ.ቁ | ስም | መሥሪያ ቤት/ ድርጅት |
|---|---|---|
| 1 | ምንተስኖት አስፋው | ፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዞች ልማት ኤጀንሲ |
| 2 | አልማዝ አይችሉህም | ፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዞች ልማት ኤጀንሲ |
| 3 | አስማይት ጌታቸው | ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዝ ተወካይ |
| 4 | አዝመራው ብርሃኑ | ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲቲዮት |
| 5 | ደመላሽ እንሰርሙ | ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲቲዮት |
| 6 | አረዳ ባቱ | ጨርቃጨርቅና ዲዛይን ዴቬሎፐመንት ኢንስቲቲዩት (ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ) |
| 7 | አሸናፊ ታዬ | ጨርቃጨርቅና ዲዛይን ዴቬሎፐመንት ኢንስቲቲዩት (ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ) |
| 8 | በሱፍቃድ ጠጄ | ባህላዊ የአምራቾች |
| 9 | ብሩክ ውብእሸት | ፌደራል የቴክንክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ |

## ከግል ዘርፍ  የቡደን ውይይት ተሳታፍዎች

| ተ.ቁ | ስም | መሥሪያ ቤት/ ድርጅት |
|---|---|---|
| 1 | አረደ ባቱ | ጨርቃጨርቅና ዲዛይን ዴቬሎፐመንት ኢንስትቲዩት (ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ) |
| 2 | አሸናፊ ታዬ | ጨርቃጨርቅና ዲዛይን ዴቬሎፐመንት ኢንስትቲዩት (ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ) |
| 3 | ጌታቸው ቢራቱ | የአቃቂ ጋርመንት ባለቤት |
| 4 | ቢንያም አብርሃም | ኣይካ አዲስ ጋርመንት |
| 5 | ምህሁት ሰለሞ አክማን | ኣይካ አዲስ ጋርመንት |
| 6 | ብርሃኑ ደገፋ | ዕድገት ጋርመንት ባለቤት |
| 7 | ይልቃል ቢሰንብት | ኦሊስ ኢትዮጵያ ባለቤት |
| 8 | መሐመድ ዑመር | የኖቨ እስታር ጋርመነት ባለቤት |
| 9 | ምነዳ ታፈሰ | ጋርሜነት ማኑፋክቸር |
| 10 | በላይነህ በካ | የቤካ ባለቤት |
| 11 | አብይ ግደይ | ጋርመንት አክሰሰርስ ማኑፋክቸሪንግ |
| 12 | ኤልያስ ሙሉጌታ | የኤድኤም ጋርመነት ባለቤት |

## ከጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት የቡድን ውይይት ተሳታፍዎች

| ተ.ቁ | ስም | ሃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | ሃይሌ ስሜ | ሲኒዬር የኢንዱስትሪ ኢንጅነር |
| 2 | ወንጌል አድስ | መሪ የመካኒካል ኢንጅነር |
| 3 | ደላቤ ንካ | ሰኒዬር የጨረቃ ጨርቅ ኢንጅነር |
| 4 | ሄኖክ አዳሙ | የእንስፔክሽን ኤክስፔርት |
| 5 | ውድወሰን ሽህፈራው | የማርከቲንግ ኤክስፔርት |
| 6 | መሣይ አለማየሁ | የጨርቃጨርቅ ኢንጅነር |

| | | |
|---|---|---|
| 7 | ይትባረክ ጥላሁን | ሲኒዬር ጨርቃጨርቅ ኢንጅነር |
| 8 | ሙሉ ጫሌ | ረዳት የጨርቃጨርቅ ኢንጅነር |
| 9 | አቡበከር መሐመድ | የጨርቃጨርቅ ኢንጅነር |

## 3 ከውጪ ኢንቪስተሮች ፎሬም ጋር የቡድን ውይይት ተሳታፍዎች (5)

| ተ.ቁ | ተሳታፊዎች | ድርጅት |
|---|---|---|
| 1 | የቻይና ንግድ (ቢዝነስ) አባላት | የቻይና ንግድ (ቢዝነስ ፎረም |
| 2 | የአውሮፓ አንድነት ንግድ (ቢዝነስ) አባላት) | የአውሮፓ ንግድ (ቢዝነስ) ፎረም |

## የአውደ ጥናት ተሳታፊዎች

| ተ.ቁ | ስም | መሥሪያ ቤት/ድርጅት | ኃላፊነት |
|---|---|---|---|
| 1 | ተከበሩ አቶ አህመድ አብተው | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | ሚኒስትር |
| 2 | የተከበሩ ዶ/ር መብራቱ መለሰ | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | ሚኒስትር ዴኤታ |
| 3 | የተከበሩ አቶ ሲሳይ ገመቹ | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | ሚኒስትር ዴኤታ |
| 4 | የተከበሩ አቶ መኮንን ማንያዘዋል | ብሔራዊ ፕላን ኮሚሽን | ሚኒስትር |
| 5 | የተከበሩ አቶ ሽሀፈራው ሽጉጤ | ትምህርት ሚኒስቴር | ሚኒስትር |
| 6 | የተከበሩ አቶ ወንደወሰን ክፍሉ | ትምህርት ሚኒስቴር | ሚኒስትር ደኤታ |
| 7 | አህመድ ኑሩ | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | አማካሪ |
| 8 | ፋሲል ታደሰ | ኢትኤጅኤኤምኤ | ፕሬዚዳንት |
| 9 | በላይ ወልዬ | አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ | ረዳት ፕሮፌሰር |
| 10 | ታምሩ ሃብቴ | እርሻ ሚኒስቴር | ረ/ዳይሬክቴር |
| 11 | ሄኖክ እሸቱ | ኢትዮጵያ ኮምፕተትቨ ፋስልቲ | አክስፔርት |
| 12 | ያለው አለማየሁ | ኢትዮጵያ የቆዳ ኢንዱስትሪዎች ማህበር | የቦርድ አባል |
| 13 | አድሱ ፈረዴ | ቢዲቪ-አልኦቴክ | ዳይሬክተር |
| 14 | ዘውዱ ካሳ | ትምህርት ሚኒስቴር | ሥራ አስኪያጅ |
| 15 | ዶ/ር ዘነበ ክፍሌ | አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ | ተባባሪ ፕሮፌሰር |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 16 | አለሙ አምባዬ | ኢትዮጵያ መርከብና ሎጀስትክ | ዋና ሥራ አስኪያጅ |
| 17 | ንጉሤ ገ/ማሪያ | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | አማካሪ |
| 18 | ተመስገን ዋለልኝ | ገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር | ዳይሬክተር |
| 19 | አስፋው አበበ | ፌደራል አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ኤጀንሲ | ዳይሬክተር |
| 20 | ያረጋል ምስክር | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | ዳይሬክተር |
| 21 | ጌታሁን ታደሰ | ኢትዮ ካይዘን ኢንስትቲዩት | ዋና ዳይሬክተር |
| 22 | በቀለ ተመስገን | ኢትዮጰያ ሬድዮና ቴሌቪዥን | አዲስ አበባ |
| 23 | ስለሽ ለማ | ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት | ዳይሬክተር |
| 24 | ተሰማ ላቀው | እርሻ ሚኒስቴር | ዳይሬክተር |
| 25 | ሐብታሙ ካሳ | ኬሚካል ማህበር | ቦርድ አባል |
| 26 | ኑሬዲን ሙስጠፋ | ውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር | ስኒዩር ኤክስፔርት |
| 27 | ተዎድሮስ አሳፌ | የተቆላ ቡና አዘጋጆች | ም/ፕሪዚዳንት |
| 28 | አሰሬስ ወ/ጊዮርጊስ | ውሃና ኢኔርጅ ሚኒስቴር | ዳይሬክተር |
| 29 | ፈለቀ ለማ | ሥጋና ወተት | አማካሪ |
| 30 | ተሸመ መገርሣ | ኢትዮጵያ ካይዘን ኢንሲትቲዩት | ም/ሥራ አስኪያጅ |
| 31 | ሳይሉ አንተነህ | አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ | ረዳት ፕሮፌሰር |
| 32 | ተስፋዬ ብርሃኑ | ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት | ዳይሬክተር |
| 33 | ካሳዬ ወልደ | ፋና ብሮድካስትንግ ኮሮፓሬሽን | |
| 34 | ገ/ህወት ኃ/እግዝአብሔር | ኢትዮጵያ ንግድ ዘርፍ ማህበራት | ፕሬዝዳንት |
| 35 | ነብዩልዑል ፋንታሁን | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | አማካሪ |
| 36 | ሰኡሩ ተሸለ | ኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት | ዳይሬክተር |
| 37 | ዮስፍ አፈወርቅ | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | |
| 38 | ዶር ደምስ አለማየሁ | አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ | ገምጋሚ |
| 39 | ታደለ ፋረደ | አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ | ገምጋሚ |
| 40 | ግርማ ዳምጤ | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | ኤክፔርት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 41 | ፍፁም አረጋ | ገንዘብና ኢኮኖሚ ዕድገት ሚኒስቴር | ኤክስፐርት |
| 42 | ምንልክ ሀብቱ | ኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን | ዳይሬክተር |
| 43 | ሰይድ መሐመድ | ማዕድን ሚኒስቴር | ጅኦሎጅስት |
| 44 | ውድነህ ዘነበ | ሪፓርተር | ጋዜጤኛ |
| 45 | ተ/ሃይማኖት ገስሲ | ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮሮፓሬሽን | ቺፍ ኦፊሰር |
| 46 | አባድ ለገሠ | ቲኤም | ቺፍ ኦፊሰር |
| 47 | ጌታሁን ኂይሌ | ኢትዮጵያ እንሰሳት ምግብ | ቦርድ አባል |
| 48 | ዮሐንስ ጥላሁን | እርሻ ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ | ዳይሬክተር |
| 49 | እንዳለ ሸዋግዛው | ትምህርት ሚኒስቴር | አማካሪ |
| 50 | ሁነኛው አበባው | ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት | ሲኒዮር ኤኮኖሚስት |
| 51 | ወርቅነህ ደሳለኝ | ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት | ም/ሥራ አስኪያጅ |
| 52 | ዶ/ር ግሩም አበበ | ኢትዮጵያ ልማት ጥናት ኢንስትቲዩት | ተመራማሪ |
| 53 | ዶ/ር ገ/እግዝአብሔር ገ/የሱስ | እርሻ ሚኒስቴር | ሚኒስቴር ዴኤታ |
| 54 | መሐመድ የኑስ | ውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር | ሲኒዮር አክስፐርት |
| 55 | ዘመን ዮሐንስ | ዳሽን ኮመርሻል | አርታኢ |
| 56 | ሙሉጌታ ተፈሪ | ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት | ኮሚቴ |
| 57 | መስፍን ውብሸት | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | |
| 58 | ናኦም ተስፋዬ | ኤምሲሲ | ፎቶ |
| 59 | ገብረሕወት ገ/ታትዎስ | ኢትዮጵያ ኮምፕተትሽ ፋስሊቲ | ኤክስፔርት |
| 60 | ሰለሞን ዮሐንስ | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | ዳይሬክተር |
| 61 | መዝገቡ አምሃ | ገንዘብና ኢኮኖሚ ዕድገት ሚኒስቴር | ዳይሬክተር |
| 62 | ሰለሞን ገ/መድህን | ፕሬስ ኤጀንሲ | አርታኢ |
| 63 | ለምለም መንግሥቱ | ፕሬስ አጀንሲ | ሪፓርተር |
| 64 | ትዕግስት ጌታነት | ፕሬስ ኤጀንሲ | ሪፓርተር |
| 65 | ቤተልሔም ለገሠ | ፕሬስ ኤጀንሲ | ዘሚል |
| 66 | ብሩክ እንዳለ | ፕሬስ ኤጀንሲ | ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 67 | አብርሃም ምንአሉ | ኢትዮጵያ ጨረቃ ጨርቅ ልማት ኢንዱስትሪ ኢንስቲትዩት | ኤክፔርት |
| 68 | ዶ/ር ዳኛቸው በየነ | እርሻ ሚኒስቴር | ዳይሬክተር |
| 69 | ይርዳው ወ/ሰማየት | አኤችኤፍአይኤች | ዋና ሥራ አስኪያጅ |
| 70 | ሃጎስ ስቃር | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | ቡድን መሪ |
| 71 | ደንደና ጨመዳ | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | ዳይሬክተር |
| 72 | ዶ/ር ዳንኤል ቅጣው | አዲስ አበባ ቴክኖሎጅ ኢነስቲትዩት | ረ/ፕሮፌሰር |
| 73 | ዶ/ር ተመስገን ጋሮማ | ወለጋ ዩኒቨርሲቲ | የጥናት ዳይሬክተር |
| 74 | አብዲሳ ህልማ | ሳይንስና ቴክኖሎጅ ሚኒስቴር | አማካሪ |
| 75 | ቅርበት ፋንታሁን | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | አማካሪ |
| 76 | ገሠሠ ተሸመ | አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር | ም/ፕሬዚዳንት |
| 77 | ሳሙኤል ሙሉጌታ | ኤምአይዲአር | ቦርድ አባል |
| 78 | መታሠቢያ ሃይሉ | ሚድሮክ ኢትዮጵያ | ህግ አማካሪ |